አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል

በ
አዲስ ይትባረክ

ሰኔ 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል

በ

አዲስ ይትባረክ

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አዲስ ይትባረክ

ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል

በ

አዲስ ይትባረክ

2005 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | ፊርማ |
|---|---|
| አማካሪ | |
| ቴዎድሮስ ገብሬ (ረዳት ፕሮፌሰር) | 25/10/05 |
| የውስጥ ፈታኝ | |
| ዳሳሁን ተሊላ | 25/10/05 |
| የውጭ ፈታኝ | |
| ተክለፃድቅ ገ/ማርያም ሃ | |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል በሚል ርእስ የተሠራ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ላይ የሚከወኑ ቃል ግጥሞችን በመመርመር በዋቄፈታ እምነት እና በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት መካከል የተፈጠረውን የእምነት ውህደት በማህበረ ባህላዊ አውድ ውስጥ አስገብቶ መተንተን ነው፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት አካሂጃለሁ፡፡ ዓላማዬን ከግብ ለማድረስ አውዳዊ ንድፈ ሀሳብ፣ የከበራ ስርዓት እና የእምነት ውህደት የተሰኙ ንድፈ ሀሳቦችን የተገለገልኩ ሲሆን አውድ ተኮር ሥነ ዘዴን በመጠቀም ትንተናዬን አካሂጃለሁ፡፡ እነዚህን የንድፈ ሀሳብ እና የስነ ዘዴ ማእቀፎች ተገልግዬ በመመርመር መረዳት እንደቻልኩት የዋቄፈታ እምነትን እና የክርስትና ሃይማኖትን አዋህደው የሚከተሉት የማህበረሰብ ክፍሎች ሁለቱንም እምነቶች በሚጋሩት የአምልኮ ስፍራ ተገኝተው ከሁለቱም እምነቶች ተውጣጥቶ በተገኘ ልዩ ስርአት ልእለ ተፈጥሮን ይማጸናሉ፡፡ ልእለ ተፈጥሮውም ከሁለቱ እምነቶች በተውጣጡ መልእክተኞቹ አማካይነት ምላሹን ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ተማጽኖ እና ወድያውኑ ምላሽ እንደተሰጣቸው በእርግጠኝነት ማመናቸው በመስዋእቱ አይነት እና አቀራረብ መካከል ያለው ልዩነት ልእለ ተፈጥሮው መስዋእቱን ከመቀበል እያግደውም፣ ምላሽ እንዳይሰጥም እያደርገውም ከሚል ጥልቅ እምነት የመነጨ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## አበርክቶ

እህቴ ክብሬ ዛሬም እንደ ትላንቱ **እናት** ሆነሽልኛል፡፡ እኔ ልከውናቸው ይገቡ የነበሩ ተግባራትን እየከወንሽ ከጎኔ ባትሆኚ ኖሮ ይህ ጥናት ለዚህ ባልበቃ ነበር፡፡ ኧረ ትምህርቱም ባልተጀመረ! ስለዚህ ይህ አበርክቶ ካንቺ ውጭ ለማን ይገባል?

# ምስጋና

በመጀመርያ ለዚህ ያደረሰከኝ ልዑል እግዚአብሔር ሆይ ለዘለዓለም የተመሰገንህ ሁን፡፡

አማካሪዬ አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ የእርስዎ ሂሳዊ አስተያየት ባይታከልበት ኖሮ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ መረን ለቆ ይቀር ነበር ብዬ አስባለሁ እና በጣም አመሰግናለሁ፡፡

የዚህን ጥናታዊ ጽሑፍ ወጪ ለሸፈነልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ተጀምሮ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ ያበረከቱልኝ አስተዋጽኦ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው፡፡ በትብብርዎ የጥናት አካባቢውን ተወልጄ ያደግሁበት ያህል እንዲሰማኝ ስላደረጉ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

እኔን እና የመስክ ረዳቶቼን በእንግድነት ተቀብላችሁ በቤታችሁ ያሳደራችሁን፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት አማካይነት የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት የተባበራችሁኝ የአድሉላ ከተማ እና አካባቢዋ ነዋሪዎች "የእግዚአብሄር ሰዎች እንግዳ መቀበል ልምዳቸው ነው" ("Warri waaqayyo hee noorrdhaan bulahee") ብያችኋለሁ፡፡

ስለ ማህበረሰቡ ባህል ጥሩ እውቀት እንዲኖረኝ ያደረጉት እና ከኦሮምኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ የተተረጎመውን መረጃ አውዳዊ በማድረግ ቅርጽ ያስያዙልኝ አቦ ዋቅ ቤካ ኤርፓ (ዲያቆን ብርሀኑ ታደሰ) ላደረጉልኝ ሁሉ ምስጋናዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡

ለጥናቱ የረዱኝን መጽሐፎች በማዋስ እና ጠቃሚ ሀሳቦችን በመንገር የተባበራችሁኝ የበፊት እና የአሁን መምህሮቼ እንዲሁም የጥናት አካባቢው ድረስ በመሄድም ሆነ እዚሁ ሆናችሁ የረዳችሁኝ ጓደኞቼ ያለ እናንተ ትብብር ጥናቱ እዚህ ደረጃ ይደርስ ነበር ብሎ ማሰብ ይከብደኛል፡፡ እባካችሁ ምስጋናዬን ተቀበሉኝ!

በመጨረሻም ከልጅነቴ ጀምሮ ድጋፋችሁ ያልተለየኝ ቤተሰቦቼ ዛሬም በዚህ እድሜዬ ሳልከብዳችሁ አስተምራችሁ ለዚህ ቀን አድርሳችሁኛል እና ብድር መላሽ ያርገኝ ከማለት ውጭ ምን ማለት እችላለሁ?

# ማውጫ

ርእስ ገጽ


አጠቃሎ ................................................................ i

አበርክቶ ................................................................ ii

ምስጋና ................................................................ iii

ማውጫ ................................................................ iv

ምእራፍ አንድ

1. መግቢያ ................................................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ................................................................ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................................ 3

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ................................................................ 3

1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ................................................................ 3

1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ................................................................ 3

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ................................................................ 4

1.5. የጥናቱ ወሰን ................................................................ 5

1.6. የአጠናን ዘዴዎች ................................................................ 5

1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ................................................................ 5

1.6.1.1. ምልከታ ................................................................ 6

1.6.1.2. ቃለ መጠይቅ ................................................................ 7

1.6.1.3. የተተኳረ ቡድን ውይይት ................................................................ 8

1.6.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ................................................................ 8

1.7. የመስክ ተሞክሮ ................................................................ 8

1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠመ ችግር እና የተወሰደ መፍትሔ ................................................................ 12

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳን ................................................................ 13

2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ................................................................ 13

2.1.1. አውዳዊ ንድፈ ሀሳብ ....................................................13
2.1.2. ስርዓት ...................................................................15
2.1.3. የእምነት ውህደት ......................................................17
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ......................................................20
ምእራፍ ሦስት
3. የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ..............29
3.1. የሊበን "ጩቃላ" ወረዳ መልካምድራዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ...................................................................29
3.1.1.መልካምድራዊ እና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች ....................................29
3.1.2. ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ............................................30
3.2. የቃል ግጥም ክዋኔ በዝቋላ አቦ ክብረ በአል ....................................32
3.2.1. የአምልኮ ስፍራ ..........................................................32
3.2.2. ከቃል ግጥሙ ጋር የሚፈጸሙ ስርአቶች .......................................35
3.3. ትንታኔ .....................................................................46
3.3.1. የመባያ ጉዳዮች .........................................................46
3.3.1.1. ፈጣሪን በፍጥረቱ አማካይነት ማመስገን ..................................46
3.3.1.2. ቀዳሚዎችን መዘከር ....................................................53
3.3.1.3. እንግዳን በመቀበል እንዳች በረከት ማግኘት ...............................57
3.3.1.4. የልዕለ ተፈጥሮ ገጽታዎች ..............................................61
3.3.2. የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ...................................64
3.3.2.1. የአምልኮ ስፍራንና ዕለትን መጋራት ......................................64
3.3.2.2. የመሥዋዕት አይነት እና አቀራረብ ........................................66
3.3.2.3. የልእለ ሰብእ እና የመላእክት ረድኤት ....................................68
ምእራፍ አራት
4. ማጠቃለያ ......................................................................72
ዋቢ ጽሑፎች
አባሪዎች

# ምእራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

ይህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው ዝቋላ አካባቢ ከሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች መካከል የሀገር በቀል (ዋቄፈታ) እምነትን እና የክርስትና ሃይማኖትን አዋህደው እየኖሩ ባሉት ፎክ ቡድኖች ላይ ነው፡፡ እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች መጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዓመታዊ ክብረ በዓል ሲከበር ከከወኗቸው ቃል ግጥሞች በመነሳት የማኅበረሰቡን የክበራ ስርዓት ብሎም ለእያንዳንዱ የክበራ ስርዓት መነሻ የሆኑትን ቃላዊ ዝርው ታሪኮች መርምሬያለሁ፡፡ በመጨረሻም በሀገር በቀል እምነት እና በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት መካከል ያለው የእምነት ውህደት ምን እንደሚመስል አሳይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት አራት ምእራፎች አሉት፡፡ ምእራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ምርምሩ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመስክ ተሞክሮ፣ በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች ተካተውበታል፡፡ ምእራፍ ሁለት ንድፈ ሐሳባዊ ዳራን እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን የያዘ ሲሆን ምእራፍ ሦስት የሊበን ጨቃላ (ዝቋላ) ወረዳ መልካምድራዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት ትንታኔ ክፍሎች ተርበውበታል፡፡ ምእራፍ አራት የጥናቱ ማጠቃለያ ሲሆን የጥናቱን ዓላማ መሠረት ያደረገውን ግኝት ይዟል፡፡ በጥናቱ መጨረሻ ደግሞ ዋቢ ጽሑፎች እና አባሪዎች ተካተዋል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ 34 ዓ.ም እንደሆነ የሚጠቁሙ አንዳንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ብጹእ አቡነ ገሪማ እና ሌሎች 2000 ዓ.ም፣ ዘላለም ቻላቸው 2001 ዓ.ም የጻፏቸውን መጻሕፍት ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህንን እስተሳሰብ የሚያራምዱት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ክርስትናን እንደተቀበለ የሚያሳየውንና የሐዋርያት ሥራ 8፡ 26- 40 ላይ

የሚገኘውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዋቢ በማድረግ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ Ernest Suttner (1993) ያሉ ተመራማሪዎች ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ጊዜ ወደ አራተኛው ክፍለ ዘመን ያርቁታል፡፡ ነገር ግን እነኚህ ሐሳቦች ፍጹም ተቃራኒ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በወቅቱ ክርስትናን ይቀበል እንጂ ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት የሆነው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በ 34 ዓ.ም ክርስቲያን ሆኖ ቢመጣም ኢትዮጵያ በይፋ ክርስትናን የተቀበለችው በ 4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ማለት እንችላለን፡፡

ኃሮ ቢያንሳ (1985) የኦሮሞ ህዝብ በ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በደቡብ ምሥራቅ የሀገራችን ክፍል በኩል ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጌታቸው ኃይሌ (1997) 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦሮሞ ህዝብ ወደ መሀል ኢትዮጵያ የተጠጋበት እንጂ የገባበት አይደለም ይላሉ፡፡ ይህንን ሐሳብ የበለጠ የሚያጠናክሩት ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1961) ናቸው፡፡ ተክለ ጻድቅ የሴም ዘር የሆኑት ነገደ ዮቅጣን (አግዓዝያን) ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት የካም (ኩሽ) ዘር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደነበር ይገልጻሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች የሚመሩባቸው የተለያዩ እምነቶች እና ስርዓቶች አሏቸው፡፡ ከስርዓቶቻቸው መካከልም የበዓል አከባበር እና የመስዋእት አቀራረብ ይጠቀሳሉ፡፡ የእነዚህ ሁለት የተለያዩ እምነት ተከታይ ማኅበረሰብ አባላት የሆኑ የተወሰኑ ፎከ ቡድኖች እምነት ግን ተዋህዶ እናገኘዋለን፡፡ የእምነት ውህደት ሊመጣ የሚችለው ጥቂት በማይባሉ ዓመታት ውስጥ ከሚታዩ የመቀላቀል እና የመዳቀል ሂደቶች በኋላ ነው፡፡ ከቤተ መጻሕፍት ፍለጋዬ እንደ ተረዳሁት በጥናቱ አካባቢ ፎክ ቡድኖቹ ወደ ውህደት የመጡባቸው ደረጃዎችም ሆኑ አሁን ያሉበት ሁኔታ ጥናት አልተደረገባቸውም፡፡

ይህን ማለት ግን ሌላ ጉዳይን መነሻ በማድረግ በአካባቢው ዙርያ ጥናት አልተደረገም ማለት አይደለም፡፡ ሙሉጌታ ነጋሳ (1997)፣ ታደሰ አይችሉህም (1999) እና ሰሎሞን ደርቤ (2002) የአካባቢውን የግጭት አፈታት፣ የምንኩስና ስርአት እና የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል መከበር ያለውን ፋይዳ የሚገልጹ ምርምሮች አካሂደዋል፡፡ ዳሩ ግን፣ እነዚህ ምርምሮች ከላይ የገለጽሁትን ሐሳብ አያነሱም፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንድ ተመራማሪ ጥናታዊ ጽሑፍ ለመሥራት በሚነሳበት ጊዜ ሊሠራበት ስላሰበው ጉዳይ ፍላጎት ያለው መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በሀገራችን ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች በጠዋት ቤተ ክርስቲያን ተሳልመው አልያም አስቀድሰው መጥተው "ለቆሌ" የሚበላውን የቡና ቁርስ የሚበትኑ፣ የሚጠጣውን ቡና እና ጠላ የሚረጩ ሰዎች አሉ፡፡ እኔ ባደግሁበት አካባቢም ድርጊቱ ሲፈጸም አያለሁ፡፡ ይህ ክዋኔ ከክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ በእጅጉ የተለየ በመሆኑ ትኩረቴን ይስበው ነበር፡፡ ይህንን የክርስትና ሃይማኖትና የሀገር በቀል እምነቶች ውህደት ሊያሳዩ ከሚችሉ እና ጎልተው ከሚታዩ ክዋኔዎች መካከል አንዱ ይህ በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ላይ የሚታየው የቃል ግጥም ክዋኔ ስርዓት ነው፡፡

ከዚህ ቀደም ይህንን ሐሳብ ይዞ/ይዛ በመነሳት በአካባቢው ላይ ጥናት ያደረገ/ች ተመራማሪ ባለመኖሩ/ሯ የተፈጠረውን ክፍተት የእኔ ጥናት ያጠባል፣ መጠናቱም የማኅበረሰቡን ዕውቀትና የሕይወት ፍልስፍና ለመረዳት ይጠቅማል፣ ብዬ ስላመንኩ ይህንን ምርምር ለማካሄድ ተነሣሥቻለሁ፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

#### 1.3.1. ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ የዋቄፈታ እምነትን እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን አዋህደው የሚከተሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ላይ የከወኗቸውን ቃል ግጥሞች በመመርመር በሁለቱ እምነቶች መካከል የተፈጠረውን የእምነት ውህደት በማኅበረ ባህላዊ አውድ ውስጥ አስገብቶ መተንተን ነው፡፡

#### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ጥናት ከላይ ከተገለጸው ዓቢይ ዓላማ በተጨማሪ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡-

- በክብረ በዓሉ ላይ ከሚከወኑት ቃል ግጥሞች በመነሳት ማኅበረሰቡ ለእምነቱ ያለውን አመለካከት ማሳየት፣

- ማኅበረሰቡ እምነቱን በቃል ግጥሞቹ አማካይነት እንዴት እንደሚገልጽ መመርመር፣
- በክብረ በዓሉ ላይ የሚከወኑት ቃል ግጥሞች እና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚተረኩ ዝርው ታሪኮች የማኅበረሰቡን ዕውቀትና የሕይወት ፍልስፍና የመግለጽ አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ መመርመር፣

### ምርምሩ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በዋናነት የዋቄፈታ እምነትን እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን አዋህደው የሚከተሉት የማኅበረሰብ ክፍሎች የእምነት ውህደት ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሲሆን ለሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎችም መልስ ይሰጣል፡፡

- የማኅበረሰቡ አባላት በስርዓቱ ላይ የሚከውኗቸው ቃል ግጥሞች እምነታቸውን ለማጽናት ምን ያህል ጠቅመዋቸዋል?
- በሀገር በቀል እምነቱ እና በክርስትና ሃይማኖቱ መካከል የተፈጠረው የእምነት ውህደት በቃል ግጥሞቹ አማካይነት እንዴት ይገለጻል?
- የቃል ግጥሞቹ ከዋኔ ፍቺ ላይ ለመድረስ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚተረኩት ቃላዊ ዝርው ታሪኮች ምን ያህል አስተዋጾ ያበረክታሉ?

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

በዚህ ጥናት ትኩረቴን ዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ላይ በሚከወኑ ቃል ግጥሞች እና በሀገር በቀል እምነትና በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት መካከል የተፈጠረውን የእምነት ውህደት መመርመር ላይ አድርጌያለሁ፡፡ ጥናቱ አንባብያን ከዝቋላ ማኅበረሰብ የእምነት ሁኔታ ጋር ዕውቂያ እንዲኖራቸው እድል ይፈጥራል፡፡ በዚህም መሠረት ምርምሩ ማኅበረሰቡ ቃል ግጥሞችን በመጠቀም እምነቱን እንዴት እንደሚያጸና ተንትኛለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ከዚህ ቀደም በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ከቃል ግጥም ከዋኔ በመነሣት ስለ እምነት ውህደት የተሠራ ጥናት ባለመኖሩ ተፈጥሮ የነበረውን ክፍተት በመጠኑ ያጠባል፤ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢው ተዛማጅ ሥራ ለሚያከናውኑ ተመራማሪዎች እንደመነሻ በመሆን ያገለግላል፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ዝቋላ አቦ አካባቢ የሚገኙ የዋቄፈታ እምነትን እና የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አዋህደው የሚከተሉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ ፎክ ቡድኖቹ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ ከከወኗቸው ቃል ግጥሞች በመነሣት የማኅበረሰቡን የከበራ ስርዓት እና ለስርዓቱ መንስኤ የሆኑትን ቃላዊ ዝርው ታሪኮች መርምሬያለሁ፡፡ ይህም በሀገር በቀል እምነቱ እና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መካከል ያለውን የእምነት ውህደት ለመተንተን አስችሎኛል፡፡

ከዚህ ባሻገር የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች በበዓሉ ዋዜማ እና ዕለት የከወኗቸውን ልዩ ልዩ ስርዓቶች እና እንደ "አጣብቂኝ"፣ "የሰይጣን መቃብር"፣ "የአቡዬ ወንበር" እና "የእርብ እሮብ ዳገት" በተባሉ ስፍራዎች ላይ የተካሄዱ ክዋኔዎች በሌላ አጥኚ ስለተዳሰሱ እንደዋና ጉዳይ አድርጌ አልተመለከትኳቸውም፡፡ በአካባቢው ከክርስትና በተጨማሪ የእስልምና እና የሌሎች ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ሃይማኖት ተከታዮች በዕለቱ ክዋኔ ስለማያቀርቡ እና ሃይማኖቱ ከሃገር በቀል እምነቱ ጋር ውህደት መፍጠር አለመፍጠሩ ራሱን ችሎ ሊጠና የሚችል በመሆኑ በዚህ ጥናቴ አላተኮርኩባቸውም፡፡

## 1.6. የአጠናን ዘዴዎች

አንድ የፎክሎር ምርምር ለማካሄድ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳኳሪ ቡድን ውይይትን እንደ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ ምንጮች እና የጥናቱን መተንተኛ ስልት እንደሚከተለው አብራርቻለሁ፡፡

### 1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጮችን ተገልግያለሁ፡፡ ስለ አካባቢው እና ስለ ማኅበረሰቡ የሚገልጹ ዳራዊ መረጃዎችን ከቤተ መጻሕፍት ሰብስቤያለሁ፡፡ በካልአይ የመረጃ ምንጮች በሰበሰብኳቸው መረጃዎች አማካይነት የቅድመ መስክ ዝግጅቴን አጠናቅቄለሁ፡፡ ከዚያም ወደ መስክ በመሄድ ሦስቱንም የመረጃ

መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመገልገል መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭን ተጠቅሜ ቃል ግጥሞቹን የሰበሰብኩት መጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም በቦታው ተገኝቼ በመመልከት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስለ ቃል ግጥሞቹ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለሚተረኩት ቃላዊ ዝርው ታሪኮች እና ስለ ማኅበረሰቡ እምነት ተጨማሪ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት አማካኝነት ለማግኘት ካልአይ የመረጃ ምንጭን ተጠቅሜያለሁ፡፡

### 1.6.1.1. ምልከታ

ጎልድስቴን (Goldsten. 1964፡77) ምልከታ የሚለው ቃል በዐይን ማየት ብቻ ማለት እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡ ጥልቀት ባለው መልኩ ማስተዋልን የሚጠይቅ መሆኑን እና የምንመለከተውን ነገር ተረድተን መተርጎም መቻል እንዳለብን ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፡፡

> *The term "observation," as used in this context, is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting, whenever these may be appropriate.*

ከዚህ ሐሳብ መረዳት እንደሚቻለው ምልከታ እንደ አስፈላጊነቱ ሙሉ የስሜት ህዋሳቶቻችንን ተጠቅመን የምንገነዘበው እንጂ በዐይናችን ብቻ አይተን የምንረዳው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ቫንደርስቴፕ እና ጆንስተን (Vanderstep and Johnston. 2009፡ 239) የተባሉ ምሁራን ምልከታ ሰዎች የራሳቸውን ጉዳይ ሲከውኑ በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በዚህም መሠረት በገዳላ አቦ ክብረ በዓል ላይ የተከወኑትን ቃል ግጥሞች እና ከቃል ግጥሞቹ ከዋኔ ጋር የተደረገውን ስርዓት ስመለከት ይህን እሳቤ ከግምት ውስጥ አስገብቼ ነበር፡፡

በመስክ ሥራችን ወቅት የምናካሂደው ምልከታ የተሳትፎ ምልከታ ወይም ደግሞ ያለተሳትፎ ምልከታ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለቱም አይነት ምልከታዎች ሲካሄዱ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በሚከናወንበት አውድ እና ሁኔታ ውስጥ መገኘትን ይጠይቃሉ፡፡ የተሳትፎ ምልከታ አጥኚው የከዋኔው ንቁ ተሳታፊ በመሆን (ማኅበረሰቡ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ አብሮ እያደረገ) የሚከናወን ስለሆነ ፎክሎሩን በተፈጥሯዊ አውዱ ውስጥ አስገብቶ ለማጥናት እንዲሁም የከዋኞቹን ስሜት በቀላሉ ለመረዳት ያስችለዋል፡፡ አጥኚው የማኅበረሰቡ አባል

ወይም ደግሞ ለረጅም ጊዜ አብሯቸው የቆየ ካልሆነ ግን ከዋኞቹ ሌላ ተመልካች እንዳላቸው ይገነዘባሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የክዋኔው ተፈጥሯዊነት መደብዘዙ እንደ ውስንነት ይታያል፡፡ ያለተሳትፎ ምልከታ በሚካሄድበት ጊዜ ደግሞ አጥኝው አጫጭር ማስታዎሻዎችን የመያዝ፣ እያንዳንዱን ክዋኔ የመቃኘት እና መቅረጸ ድምጽ የመጠቀም እድል ይኖረዋል በማለት ጎልድስቴይን (79-80) ያብራራሉ፡፡

ከዚህ ሐሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሁለቱም አይነት ምልከታዎች የራሳቸው የሆነ ድክመትና ጥንካሬ አላቸው፡፡ እኔም የዚህን ጥናት መረጃ ከመስክ በምሰበስብበት ጊዜ የተሳትፎ ምልከታ ለማካሄድ አስቤ የነበረ ቢሆንም የማኅበረሰቡን ባህልም ሆነ ቋንቋ ስለማልረዳ እና በአካባቢው ለረጅም ጊዜ ስላልቆየሁ ይህንን ማድረግ አልቻልኩም፡፡ ያለተሳትፎ ምልከታ ባካሄድኩበት ወቅት መቅረጸ ድምጽና ቪዲዮ ካሜራ ተጠቅሜያለሁ፡፡ ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት ወቅት በመመልከት ብቻ በዋቄፈታ እምነት እና በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች መካከል የተፈጠረውን የእምነት ውህደት ሙሉ በሙሉ መገንዘብ አስቸጋሪ ሆኖብኝ ነበር፡፡ይህንን ችግር የፈታሁት የምልከታ ደጋፊ የሆነውን እና በሁለተኛነት የሚጠቀሰውን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ (ቃለ መጠይቅ) በመጠቀም ነው፡፡

### 1.6.1.2. ቃለ መጠይቅ

ጎልድስቴን (104) ቃለ መጠይቅ ማድረግ በፎክሎር ባለሙያዎች ዘንድ በጣም የተለመደ እና ተግባራዊ የሚደረግ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እንደሆነ ከገለጹ በኋላ በቃለ መጠይቅ የሚገኙት መረጃዎች ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያብራሩ *“Interview data may include information on what the informant knows, believes, expects, feels, wants, does or has done, or which explains or gives reasons for any of the preceding.”* በማለት ያስረዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ በቃለ መጠይቅ አማካይነት መረጃ ሰጭዎቻችን ስለ ክዋኔያቸው የሚያውቁትን፣ የሚያምኑትን፣ የሚፈልጉትን እና የሚሰማቸውን ለመገንዘብ ያስችለናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዘዴ በመጠቀም የተሳታፊዎቹን ዕውቀት፣ እምነት፣ ስሜት፣ ፍላጎት፣ ያደረጉትን እንዲሁም ላከናወኗቸው ድርጊቶች ሰበብ የሆኗቸውን ቃላዊ ዝርው ታሪኮች ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ቃለ መጠይቁን ያደረግሁት በዋናነት በክብረ በዓሉ ላይ የቃል ግጥሞቹ ከዋኝ ከነበሩት መካከል ምርቃቱን ሲመሩ፣ ቃል ግጥሞቹን ሲያወርዱ ከነበሩት የቀድሞው አባ ገዳ፣ የገዳ አባላት እና የሀገር ሽማግሌዎች ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

ከሌሎች የበዓሉ ተሳታፊዎች እና የገዳሙ አባቶች ጋር ቃለ ምልልስ አድርጌያለሁ፡፡ በበዓሉ እለት (መጋቢት 5/2005 ዓ.ም)፣ መጋቢት 8/2005 ዓ.ም እና መጋቢት 15/2005 ዓ.ም ከአስራ አራት ወንዶች እና ከሁለት ሴቶች ጋር ቃለ ምልልሶችን አካሂጃለሁ፡፡ ይህ ደግሞ የእምነት ውህደቱን ለመተንተን የረዱኝን መረጃዎች እንዳገኝ ረድቶኛል፡፡

መጋቢት 5 ቀን 2005ዓ.ም በዝቋላ ተራራ ላይ የተካሄደውን ቃል ግጥም ከዋኔ ለመረዳት ማን፣ ምን እና ለምን የተሰኙ ጥያቄዎችን በማንሳት የተለያዩ የማኅበረሰቡ አባላትን ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ይህም በምልከታ ወቅት ለተፈጠሩብኝ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ስለረዳኝ የማኅበረሰቡ አባላት እምነታቸውን የተገነዘቡበትን መንገድ ከነ ምክንያቱ ለመረዳት አስችሎኛል፡፡

### 1.6.1.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

ፍንደርስቴፕ እና ጆንስተን (235) *"Focus groups together a group of six to ten people who, under the guidance of a moderator, engage in a group question - and - answer discussion."* በማለት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ቁጥራቸው ከ6-10 የሚደርሱ ሰዎች የሚሳተፉበት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአወያዩ መሪነት የቡድን ጥያቄ እና መልስ ይካሄዳል፡፡ ይህንን ሐሳብ ከግምት ውስጥ በማስገባት በከዋኔው ወቅት ከዋኝ እና ተሳታፊ ከነበሩ ሰዎች ጋር የተተኳሪ ቡድን ውይይት አድርጌያለሁ፡፡ በተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ውስጥ ስድስት ወንዶች እና ሁለት ሴቶች ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ውይይቱን ያካሄድኩት መጋቢት 8/2005 ዓ.ም አዱላላ ከተማ ውስጥ ነበር፡፡ ይህም በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ በግልጽ መረዳት ያልቻልኳቸውን አንዳንድ ትእምርቶች እንድረዳ አድርጎኛል፡፡

## 1.6.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ የተጠቀምኩት የመረጃ መተንተኛ ዘዴ አውድ ተኮር ሥነ ዘዴ *(Contextual Methdological Approach)* ነው፡፡ ይህ የመተንተኛ ዘዴ የቃል ግጥሙን ከዋኔ ከነ ማህበረ ባህላዊ አውዱ ለመመርመር ያስችላል፡፡ እኔም ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተገልግያለሁ፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች ከመስክ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች አውድ ተኮር ስነ ዘዴን በመጠቀም ተንትኛለሁ፡፡

## 1.7. የመስክ ተሞክሮ

ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ግብዓት የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በሦስት ዙር የተጠናቀቀ የመስክ ሥራ አካሂጃለሁ፡፡ በመጀመርያው ዙር የመስክ ሥራ በዋናነት ራሴን ከጥናት አካባቢው ጋር ለማስተዋወቅ ችያለሁ፡፡ በሁለተኛው ዙር የመስክ ሥራዬ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎችን ሰብስቢያለሁ፡፡ በመጨረሻም በሦስተኛው ዙር የመስክ ሥራ በትንተና ወቅት ካጋጠሙኝ ክፍተቶች በመነሳት ቃለ መጠይቅ አካሂጃለሁ፡፡ ይህንን የመስክ ተሞክሮ እንደሚከተለው በዝርዝር አቅርቤያለሁ፡፡

**የመጀመርያው ዙር የመስክ ተሞክሮ፡-** ይህን የመስክ ሥራ ራሴን ከጥናት አካባቢው ጋር ለማስተዋወቅ፣ ባህሉን እና ቋንቋውን በቅጡ የሚያውቅ ሁነኛ የመስክ መሪ (guide) ፈልጎ ለማግኘት፣ ስለ ጥናቱ በቂ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና መረጃዎቼን መቼ፣ ከማን እና እንዴት መሰብሰብ እንዳለብኝ ለመወሰን አስቤ ያካሄድኩት ነው፡፡ የመስክ ሥራው የተከናወነው ከታህሳስ 19/2005 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 21/2005 ዓ.ም ነበር፡፡

በዚህም መሠረት እርብ ታኅሳስ 19/2005 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ቃሊቲ መናሀርያ በመነሳት ወደ ደብረ ዘይት ሄድኩ፡፡ ከደብረ ዘይት የሊበን ጨቃላ ወረዳ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው አዱላላ ከተማ አመራሁ፡፡ አዱላላ ከተማ እንደደረስኩ ወደ ወረዳው ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ውስጥ ገብቼ መታወቂያዬን እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያስጻፍኩትን ደብዳቤ በማሳየት ከቢሮው ሠራተኞች ጋር ተዋወቅሁ፡፡ ከዛም ስለ ጥናቱ በአጭሩ አስረድቻቸው ቅዳሜ ታኅሳስ 20/2005 ዓ.ም ሰፋ ላለ ሰዓት ተገናኝተን እንድንወያይ እና የመስክ መሪ (አስተባባሪ) በመምረጥ እንዲያግዙኝ እንዲሁም ከገዳ አባላት ጋር የምገናኝበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹልኝ ጠየቅኳቸው፡፡ ጥያቄዬን ተቀብለውኝ ስልክ ቁጥር ከተለዋወጥን በኋላ ወደ ማረፊያዬ ሄድኩ፡፡

ቅዳሜ ታኅሳስ 20/2005 ዓ.ም ጠዋት 3:00 ሰዓት ላይ ተገናኝተን ከተወያየን በኋላ በከተማዋ ውስጥ እና በአካባቢዋ እየተዘዋወሩ ባህል ላይ ያተኩሩ ጥናቶችን የሚያካሂዱት አቶ አያናው ነዲን በመስክ መሪነት መረጥናቸው፡፡ አቶ አያናው የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ሲሆኑ ከሌሎቹ በተሻለ መልኩ ስለ ባህሉ ያውቃሉ፤ ኦሮምኛ ቋንቋ የአፍ መፍቻቸው ነው፡፡

ከሰዓት በኋላ ከመስክ መሪዬ ጋር በመሆን አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ[1] ቤት ሄድን፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ መቼ መሄድ እንዳለብኝ፣ እንዴት ምልከታ ማካሄድ እንደምችል፣ ወዘተ. ተነጋግረን ተለያየን፡፡ ገበያው ሲጠናቀቅ ወደ አንዳንድ መዝናኛ ቤቶች በመሄድ ከሌሎች የገዳ አባላት ጋር ተዋወቅሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ስለ ጥናቴ ስነግራቸው መረጃ በመስጠት ሊተባበሩኝ እንደሚችሉና ባህላቸው በመጠናቱ ደስተኛ እንደሆኑ ገለጹልኝ፡፡

እሁድ ታኅሳስ 21/2005 ዓ.ም ከረፋዱ 4፡15 ሰዓት ላይ አዱላላ ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው የዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ጽሕፈት ቤት ሄድን፡፡ ወደ ጽሕፈት ቤቱ እንደደረስን የሄድንበትን ጉዳይ አስረዳናቸው፡፡ የጽሕፈት ቤቱ አባላትም በበዓሉ ዋዜማ መጋቢት አራትም ሆነ የበዓሉ እለት የዝቋላ ተራራን በመውጣት የገዳሙን አባቶች ማነጋገር እና የተለያዩ መረጃዎችን ማግኘት እንደምንችል ገለጹልን፡፡ በዚህ መልኩ የመጀመርያውን ዙር የመስክ ሥራ አጠናቅቄ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ፡፡

**ሁለተኛው ዙር የመስክ ተሞክሮ፡-** ሁለተኛውን የመስክ ሥራ ያካሄድኩት ከመጋቢት 3/2005 ዓ.ም እስከ መጋቢት 8/2005 ዓ.ም ድረስ ነበር፡፡ ማክሰኞ መጋቢት 3/2005 ዓ.ም ስለ ጥናቴ በቂ ግንዛቤ ካላቸው ሦስት የመስክ ረዳቶቼ ጋር በመሆን ወደ አዱላላ ከተማ ሄድን፡፡ እዛም እንደደረስን የመስክ መሪዬ ቋንቋውን እና ባህሉን የሚያውቁ ሁለት የመስክ ረዳቶች እንዳገኙልኝ ገለጹልኝ፡፡ በአጠቃላይ ሰባት ሆነን ለረቡዕ ከሰዓት ጉዞ ዝግጅት አደረግን፡፡ ረቡዕ መጋቢት 4/2005 ዓ.ም ከቀኑ ሰባት ሰዓት ተኩል (7፡30) የጨቃላ ተራራን መውጣት ጀመርን፡፡ ከሦስት ሰዓት ከአስራ አምስት ደቂቃ የተራራ ጉዞ በኋላ ( በጉዟችን ወቅት በየመካከሉ ለሦስት ጊዜ ያህል ለጥቂት ደቂቃዎች እረፍት አድርገን ነበር፡፡) ጨቃላ ተራራ አናት የሚገኘው የዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ደረስን፡፡

ቤተ ክርስቲያኑ ደርሰን ትንሽ እረፍ ካልን እና ማደርያችንን ካዘጋጀን በኋላ ከቤተ ክርስቲያኑ ወረድ በማለት የተራራው መሀከል ላይ ተንጣሎ የሚገኘውን የጨቃላ ሀይቅ (የዝቋላ ጸበል) ተመለከትን፡፡ የመስክ መሪዬ እና ሦስቱ የመስክ ረዳቶቼ ከዚህ በፊት ይመጡ እንደነበር እና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሀይቁ የውሀ መጠን እየቀነሰ መምጣቱን

---

[1] አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ፡- አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ ከ 1992 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም በአባ ገዳነት ስልጣን ላይ የነበሩ እና ዝቋላ አካባቢ ተወልደው ያደጉ ሰው ናቸው፡፡ አባ ገዳን ትልመ ጥናት ከማዘጋጀቴ በፊት የወረዳው ገዳ ቢሮ በመሄድ ተዋውቂያቸው ነበር፡፡

ገለጹልኝ፡፡ በመቀጠልም የዋቄፈታ እምነትን እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን በአንድ ላይ የሚከተሉት የማኅበረሰብ አባላት የአምልኮ ስርዓት ወደሚፈጽሙበት ጫካ ሄድን፡፡ ጫካው ውስጥ እንደገባን ከ2002 ዓ.ም በፊት የአምልኮ ስርዓት ይፈጽሙበት የነበረው ሲዳ የነበረበትን ቦታ አሳዩኝ፡፡ ሲዳው በ2002 ዓ.ም ከተሰበረ ወዲህ የአምልኮ ስርዓቱን የሚፈጽሙበትን ኦዳ ተመለከትን፡፡ የከበራ ስርዓቱ የሚጀመረው ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ በመሆኑ የበዓሉ ከዋኞችም ሆኑ ተሳታፊዎች በስፍራው አልነበሩም፡፡ እኛም ንጋት ላይ ለመመለስ ተነጋግረን ወደ ማደርያችን ሄድን፡፡

መጋቢት 5/2005 ዓ.ም ከንጋቱ አስር ሰዓት ተኩል ሲሆን ከእንቅልፋችን በመነሣት የከበራ ስርዓቱ ወደሚፈጸምበት ቦታ መሄድ ስንጀምር ቁጥራቸው በርከት ያለ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች ተሰልፈው ከሀይቁ “ጸበል” ያስቀዳሉ፡፡ እነሱን አልፈን ስርዓቱ ወደሚፈጸምበት ጫካ ልንሄድ ስንል የገዳሙ ጥበቃ ወደ “ባእድ አምልኮ ስፍራ” መሄድ እንደማይቻል እና እምቢ ብለን ከሄድን አስፈላጊው እርምጃ እንደሚወሰድብን ገለጹልን፡፡ እኛም "የጸበሉን" ዙሪያ የመጎብኘት እንጂ ሌላ ዓላማ የሌለን መሆኑን ገልጸን በጥበቃው እንዳንታይ እየተጠነቀቅን በሀይቁ ዳርቻ ወደ ሚገኘው ጫካ ውስጥ ገባን፡፡

ከጫካው ውስጥ ስንገባ አብዛኞዎቹ የበዓሉ ከዋኞች እና ተሳታፊዎች በቡድን በቡድን ሆነው ቁጭ ብለዋል፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ተኝተዋል፡፡ አንዳንድ ከዋኞችን እንዴት ወደ ከበራ ስፍራው መምጣት እንደቻሉ ስንጠይቃቸው የጸበል ስርዓቱ ከመጀመሩ በፊት ጥበቃው ያን ያህል ጠንካራ እንዳልነበረ ገለጹልን፡፡ ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት ከሃያ አምስት ደቂቃ ሲሆን ተኝተው የነበሩትም ሆነ ቁጭ ብለው የነበሩት ከዋኞች እና ተሳታፊዎች የከበራ ስርዓቱን ጀመሩ፡፡ ስርዓቱን ከመጀመርያ ጀምሮ በትኩረት የተከታተልኩ ሲሆን የመስከ ረዳቶቹ በመቅረጸ ድምጽ መቅረጽ ጀመሩ፡፡ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን የከበራ ስርዓቱ ተጠናቀቀ፡፡

ስርዓቱ እንደተጠናቀቀ አብዛኞዎቹ የከበራው ተሳታፊዎች በፍጥነት እየወጡ ይሄዱ ነበር፡፡ ሁለት ሰዓት ተኩል (2፡30) አካባቢ የከበራ ስርዓት መፈጸምያ ስፍራው ባዶ ሆነ፡፡ በዚህ ጊዜ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታቦት ወጥቶ ሀይቁን መዞር ጀመረ፡፡ ታቦቱን አጅበን ቤተ ክርስቲያኑ ጽሕፈት ቤት ስንደርስ የገዳሙን አባቶች ማግኘት የምንችለው ከሰዓት በኋላ እንደሆነ ተነገረን፡፡

ከቀኑ ሰባት ሰዓት ተኩል (7:30) ሲሆን ጽሕፈት ቤቱ ውስጥ በመገኘት ከገዳሙ አበምኔት አባ ተስፋ ማርያም ደበሳይ እና ከገዳሙ ጸሐፊ አባ ወልደ ሩፋኤል አበበ ጋር አንድ ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ የወሰደ (እስከ 9:15 ድረስ) ቃለ ምልልስ አደረግን፡፡

ለተጨማሪ ቃለ መጠይቅ እና ለቡድን ውይይት ይረዳኝ ዘንድ ቋንቋውን እና ባህሉን የሚያውቁት የመስክ ረዳቶቼ በኦሮምኛ ቋንቋ የተከወነውን ቃል ግጥም በጽሑፍ ማስፈር (*transcribe*) ጀመሩ፡፡ እርብ መጋቢት 6/2005 ዓ.ም ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት የዝቋላ ተራራን በመውረድ ወደ አዱላላ ከተማ መጓዝ ጀመርን፡፡ አዱላላ ከተማ ደርሰን እረፍ ካልን በኋላ በድጋሜ ቃል ግጥሞቹን ወደ ጽሑፍ መገልበጥ ቀጠሉ፡፡ ወደ ጽሑፍ የተገለበጠውን ቃል ግጥም በኅብረት ወደ አማርኛ መተርጎም ጀመሩ፡፡ የትርጉም ሥራው በዚህ ቀን ሊጠናቀቅ ባለመቻሉ ቅዳሜ መጋቢት 7/2005 ዓ.ም ቀጥሎ ዋለ፡፡ የትርጉም ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ብቻ ልረዳቸው ያልቻልኳቸውን ሐሳቦች በቅደም ተከተል ማስታወሻዬ ላይ በመጻፍ እሁድ መጋቢት 8/2005 ዓ.ም በበዓሉ ላይ ከዋኝና ተሳታፊ ከነበሩ ሰዎች ጋር ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት አደረግሁ፡፡

**ሦስተኛው ዙር የመስክ ተሞክሮ፡-** ሦስተኛውን ዙር የመስክ ሥራ ያካሄድኩት ከመጋቢት 13/2005 ዓ.ም እስከ መጋቢት 15/2005 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ወቅት ትንተና ጀምሬ የነበረ ሲሆን በትንተናዬ ወቅት የታዩኝን ክፍተቶች ለመሙላት የሚረዳ ቃለ መጠይቅ አዘጋጅቼ ወደ መስክ ሄጃለሁ፡፡ ቃለ መጠይቁንም በሚገባ አከናውኜ ተመልሻለሁ፡፡

## 1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠመ ችግር እና የተወሰደ መፍትሔ

የምርምር ሥራዎች በሚካሄዱበት ወቅት እንደ ምርምሩ ሁኔታ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ እኔ ይህን ጥናት በማካሂድበት ወቅት ክብረ በዓሉ የተከናወነው ከንጋቱ አስራ አንድ ተኩል (11:30) በመሆኑ እና ከዋኔውም ጫካ ውስጥ ስለተካሄደ በቪዲዮ ለመቅረጽ ተቸግሬ ነበር፡፡ ይህ ችግር እንደሚያጋጥመኝ ቀድሜ ስለተረዳሁ የ"ፓውዛ" መብራት ይገኘ ነበር፡፡ መብራቱን መጠቀም ስጀምር ግን ብርሀኑ "ጸበል" ቦታ ድረስ ጎልቶ ታዬ፡፡ በዚህ ጊዜ ከዋኞቹ በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ጥበቃዎች ችግር ሊፈጠርባቸው እንደሚችል በመግለጽ መብራቱን እንዳልጠቀም ከለከሉኝ፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ ክዋኔውን በመቅረጸ ድምጽ ቀርጫለሁ፣ ክዋኔውንም በትኩረት ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብርሃን መታየት ሲጀምር ክዋኔውን በቪዲዮ መቅረጽ ችያለሁ፡፡

# ምእራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1. ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

"የቃል ግጥም ክዋኔ እና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል" በሚል ርእስ ለማቀርበው ጥናት ንድፈ ሐሳባዊ ማእቀፍ የሚሆኑኝ አውዳዊ ንድፈ ሐሳብ፣ ስርዓት እና የእምነት ውህደት (syncretism) የሚሉት ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህን ንድፈ ሐሳቦች እንደሚከተለው በአጭሩ አብራርቻለሁ፡፡

#### 2.1.1.አውዳዊ ንድፈ ሐሳብ

በፎክሎር የጥናት መስክ ውስጥ አውዳዊ ንድፈ ሐሳብ መቀንቀን የተጀመረው በ1960ዎቹ ዓ.ም አካባቢ ሲሆን አቀንቃኞቹም እንደ Roger Abrahams, Dan Ben-Amos, Alan Dundes, Robert Georges እና Kenneth Goldstein ያሉ የፎክሎር ባለሙያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ከስነ ልሳን ቃላዊነትን (verbal behavior)፣ ከስነ ሰብእ ተግባራዊነትን (functionalism)፣ ከማኅበራዊ ሳይንስ ሚናን (role-playing)፣ ከሥነ ልቡና "ego mechanism" እና ሌሎችንም እሳቤዎች ወደ ፎክሎር በማምጣት በመስኩ ውስጥ ተግባራዊ አድርገዋል ዶርሰን (Dorson.1972: 45)፡፡

የአውዳዊ ንድፈ ሐሳብ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ተግባራዊ መደረግ ቀድሞ የነበረውን ፎክሎርን ከቴክስቱ ብቻ ለመረዳት የሚደረግ ሙከራ ያስቀረና ቴክስቱ በተፈጠረበትና አገልግሎት በሚሰጥበት ማኅበራዊ እና ባህላዊ አውድ ውስጥ አስገብቶ መተንተን ያስቻለ ነው፡፡ በቀደመው ዘመን የአንድ ምርምር ዋና አላማ ቴክስቶችን ብቻ ሰብስቦ ማጥናት ብቻ ተደርጎ ይታሰብ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ባለፉት ዘመናት በነበረው የምእራባውያን የባህል ዕውቀት (በጽሑፍ ላይ ጥገኛ በሆነው) ላይ የተመሠረተ አስተሳሰብ እንደሆነ ፊኔጋን (Finnegan) የተባሉ ምሁር (1992፡17) ያስረዳሉ፡፡ ሎፔዝ Lopez የተባሉት ምሁርም አውዳዊ ንድፈ ሐሳብ ከነባሮቹ በቴክስት ላይ ያተኮሩ የፎክሎር ንድፈ ሐሳቦች በብዙ መልኩ የተለየ ነው በማለት ከላይ የተገለጸውን ሐሳብ ያጠናክራሉ (2006፡ 77)፡፡ በዚህ ንድፈ ሐሳብ መሠረት የመስከኞች ትኩረት ቴክስቶችን ከመሰብሰብ ያለፈ ነው፡፡ አውድ

ተኮር ምርምር ሙሉውን ፎክሎራዊ ገጽታ ይቀርጻል፤ በከዋኞች፣ በተሳታፊዎች እና በተመልካቾች መካከል ያለውን አእምሯዊና ባህላዊ መስተጋብር ይተነትናል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ፎክሎርን ከቴክስቱ ብቻ ለመረዳት ከሚሞክሩት ምሁራን የሚለዩት፣ የፎክሎር እሳቤ ተግባራዊ መደረግ ያለበት ቴክስቱ ላይ ሳይሆን ትውፊቱ በሚከወንበት ጊዜ ባለው ሁኔታ ላይ በመሆኑ ሙሉ ክዋኔው መቀረጽ አለበት፤ ስለሚሉ ነው፡፡ ክዋኔ ከቴክስትነቱ ባሻገር ከዋኙን፣ ክዋኔው የሚካሄድበትን አጋጣሚ፣ የአከዋወን ስልቱን፣ ተመልካቹን/ተሳታፊውን፣ በከዋኙ እና በተሳታፊዎቹ መካከል ያለውን መስተጋብር ያካትታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አጋጣሚውን ያስገኘውን ማኅበረሰብ ባህላዊ ዳራ ከግምት ውስጥ ያስገባል ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው ፌኔጋን አውድ የሁኔታውን ተቋም እና በውስጡ ያሉትን ተሳታፊዎች የሚጨምር ሲሆን ይህ ጉዳይ ፍቺውን ለማግኘት ተጨማሪ ነገር ሳይሆን ማእከላዊ (መሠረታዊ) ነገር ነው፤ በማለት ሐሳባቸውን የሚገልጹት (94)፡፡

የአውዳዊ ንድፈ ሐሳብ አቀንቃኝ ከሆኑት አንዱ የሆኑት ቦውማን (Bauman.1983፡ 363) አውድን ማኅበራዊ (*social*) እና ባህላዊ (*cultural*) በማለት ለሁለት ከፋፍለውታል፡፡ ባህላዊ አውድ በውስጡ ልማዳዊ ተግባራትን እና የሰዎቹ አኗኗር በፎክሎሩ ውስጥ የተቀረጸበትን መንገድ ያሳያል፤ ከዚህም በተጨማሪ እንደ ሃይማኖት፣ ዝምድና፣ ጉርብትና፣ ክበራ፣ ጸሎት ወዘተ. ያሉ ተቋማትን እንዲሁም የመስተጋብር መንገዳቸውን ይመለከታል፡፡ በሌላ በኩል ማኅበራዊ አውድ ማኅበራዊ መዋቅሮችንና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን በውስጡ ይይዛል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ቦውማን እነዚህን ሁለት አውዳዊ ገጽታዎች በጥልቀት ለመመርመር የሚያስችል እና ስድስት ንኡሳን ክፍሎች ያሉት "ቼክ ሊስት" (*check list*) አዘጋጅተዋል፡፡ የመጀመሪያው የፍቺ አውድ (*context of meaning*) ሲሆን የቀረበውን ቴክስት የኅብረተሰቡ አባላት ምን አይነት ፍቺ እንደሚሰጡት የምንመረምርበት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃነት ያስቀመጡት ተቋማዊ አውድን *(institutional context)* ነው፡፡ ተቋማዊ አውድ እርስ በእርስ ከተሳሰሩ ባህሪዎች እና ማህበራዊ አላባውያን የተገነባ፣ ለአንድ ዓላማ የተመሠረተ ተግባራዊ ተቋም ነው፡፡ በመቀጠል የፎክሎሩ ዘውግ ከሌላ አይነት ፎክሎር ጋር እንዴት ይዛመዳል? ከሚል ጥያቄ ጋር ያስቀመጡት የተግባቦት ስርዓት አውድን *(context of cultural domain)* ነው፡፡

ቦውማን ፎክሎሩን የፈጠረው ምን ዓይነት ህዝብ እንደሆነ የምንረዳበትን እና ማኅበራዊ መሠረት *(social base)* ብሎ የሰየሙትን የአውድ ክፍል በአራተኛነት አስቀምጠዋል፡፡ ሌሎቹ ግለሰባዊ አውድ *(individual context)* እና ሁኔታዊ አውድ *(context of situation)* ናቸው፡፡ ግለሰባዊ አውድ ከዋኙ የሚከውነውን ጥበብ ከማን፣ እንዴት እና ለምን እንደተማረው የምንረዳበት አውድ ነው፡፡ ከዋኙ በማኅበሩ ውስጥ ያለውን ቦታም የምንገነዘበው በግለሰባዊ አውድ አማካይነት ነው፡፡ ሁኔታዊ አውድ በክዋኔው ወቅት የሚፈጠሩትን ማኅበረሰባዊ እና ግለሰባዊ አጋጣሚዎች ይመለከታል በማለት ቦውማን ያስረዳሉ (367)፡፡

## 2.1.2.ስርዓት *(ritual)*

ክዋኔ፣ ስርዓት እና ሚት በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው፡፡ ስርዓት ለብቻው አይቆምም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማኅበራዊ ልማድን፣ ታሪካዊ ተግባራትን እና በየዕለቱ የሚደጋገሙ ክንውኖችን እንደሚያካትት ቤል (Bell) የተባሉ ምሁር ያስረዳሉ (1997:171)፡፡ ማርታ እና ማርቲን (Martha and Marthine) የተባሉት ምሁራን በበኩላቸው ስርዓት እንደ አንድ የልማድ ዓይነት የሚታይ እና በተለያዩ የፎክሎር ምሁራን ዘንድም የሚጠና የፎክሎር ዘውግ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስርዓቶች ተደጋጋሚ፣ በስርዓቱ የተዋቀሩ፣ ቁጥጥር ያለባቸው እና ብዙውን ጊዜ በአንድ ቡድን ውስጥ ያለን አባልነት የሚያመለክቱ እንደሆኑ ያስረዳሉ (2005:95)፡፡ ከእነዚህ ሐሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ስርዓት ከክዋኔ እና ሚት ጋር ተቆራኝቶ እና ተጠየቃዊነት ባለው መልኩ ተዋቅሮ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በድግግሞሽ የሚቀርብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የሰው ልጅ ከሚያከናውናቸው የተለያዩ ስርዓቶች መካከል በጣም የታወቁት (ጎልተው መውጣት የቻሉት) የልማዱ አካላት ሲሆኑ ሃይማኖታዊ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ፡፡ ቤል የስርዓት ክዋኔ አይነቶችን የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር፣ ዓመታዊ፣ መስዋእት ማቀረቢያ፣ ከበሽታ ለመፈወስ የሚፈጸሙ፣ ጾምን ተከትለው የሚመጡ እና ፖለቲካዊ በማለት ለስድስት ይከፍሏቸዋል (91)፡፡

ከእነዚህ መካከል የመጀመርያው ማለትም የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር እንደ ውልደት፣ እድገት፣ ጋብቻ እና ሞት ያሉና በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚከሰቱ ታላላቅ ዑደቶችን ተከትለው በየባህሉ የሚደረጉ ስርዓቶች ናቸው፡፡ ዓመታዊ ስርዓት ወደሚለው ዘውግ

ስንመጣ ስርዓቱ የሚካሄደው አልፎ አልፎ ሲሆን የወቅቶችን፣ የአየር ጠባይን፣ የእርሻ ሥራዎችንና ሌሎች ማኅበራዊ ክንውኖችን መለዋወጥ ተከትሎ የሚመጣ ነው፡፡ አንዳንዶቹ በየዓመቱ (በተመሳሳይ ቀን) ይከበራሉ፡፡

መስዋእት ማቅረቢያ የተሰኘው ስርዓት ደግሞ መለኮታዊ ኃይል ላደረገላቸው በጎ ነገር ምላሽ የሚያዘጋጁበት ነው፡፡ ምላሹ የአምልኮ፣ የምስጋና እና የተማጽኖ ሊሆን ይችላል፡፡ በአንጻሩ ከበሽታ ለመፈወስ ወይም ከችግር ለመውጣት የሚካሄደው ክበራ በማኅበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ችግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ከችግሮቹ ለመውጣት (ለመንጻት) የሚከወን ነው፡፡ ፖለቲካዊ ስርዓቶች የሚዘጋጁት የፖለቲካዊ ተቋማትን ኃይል ለመገንባት፣ ለማሳየት እና ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ከእነዚህ ዘውጎች መሀል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን ዓመታዊ ስርዓት ለይቼ ለማስረዳት እሞክራለሁ፡፡

**ዓመታዊ ክበራዎች፡-** የሕይወት ዘመን ሽግግር በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የሚከሰቱ ታላላቅ ዑደቶችን ሲያሳዩ ዓመታዊ ስርአቶች በበኩላቸው ለቀናት፣ ለወራትና ለዓመታት በአጠቃላይ ለጊዜ ዑደቶች ማኅበራዊ ትርጉምና ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ስርዓቶች የአየር ጠባይን፣ የእርሻ ሥራን፣ እና አልፎ አልፎ ሌሎች ማኅበራዊ ተግባራትን ተከትለው ስለሚመጡ ተተንባይ (predictable) ናቸው፡፡ አንዳንድ ስርዓቶች የፀሐይን አቆጣጠር መሠረት ሲያደርጉ ሌሎቹ ደግሞ የጨረቃን አቆጣጠር መሠረት ያደርጋሉ፡፡ የፀሐይን አቆጣጠር መሠረት የሚያደርጉት ስርዓቱን የሚፈጽሙት በተመሳሳይ ቀን ሲሆን በጨረቃ አቆጣጠር የሚቆጥሩት ግን ቀኑ በየዓመቱ እንደሚቀያየር ቤል (102) ያስረዳሉ፡፡

ዓመታዊ ስርዓቶች ወቅትን ጠብቀው የሚመጡ *(seaosnal)* እና የመታሰቢያ *(commemorative)* በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ወቅትን ጠብቀው የሚመጡት ስርዓቶች ለአርሶ አደሮች ዘር ከመዝራትና ከአጨዳ ጋር የሚያያዝ ሲሆን ለአርብቶ አደሮች ደግሞ ከግጦሽና ከብቶቻቸውን ከቦታ ቦታ ከሚያንቀሳቅሱበት ወቅት ጋር ይያያዛል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስርዓቶች ምንም እንኳን እንደ አፈሩ ልምላሜ፣ እንደ ስርዓቶቹ አከባበር ስልትና የእርሻ ዓይነት የሚወሰኑ ቢሆኑም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ እንደሚገኙ ቤል ያስረዳሉ፡፡

ቤል "*the sowing of seed is usually marked by offerings to ancestors or deities in order to secure protection for the fields*" (102). በማለት በአብዛኛው ዘር መዝራት ለአማልክት

ስለት በማቅረብ እንደሚጀመር ይገልጻሉ፡፡ ይህም የእርሻውን ጥበቃ ለማጠናከር ይረዳል፡፡ በምላሹ እህሉ ደርሶ ስርዓቶች ሲካሄዱ የመጀመርያዎቹ ፍሬዎች ለአማልክቱ ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዴ አማልክቱ ራሳቸው መጥተው ስርዓቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ቆይተው ከመንደሩ ወጥተው ሊሄዱ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

የዓመታዊ ስርዓቶች ሁለተኛው (ሌላ) ቡድን የሆኑት የመታሰቢያ ስርዓቶችን በተመለከተ ቤል (105) ሲያስረዱ በርካታ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ዓመታዊ የሆነውን የቀን መቁጠርያቸውን በሙሉ በኅብረተሰቡ ውስጥ በሰፊው የሚታመንባቸውን ትልልቅ እምነቶች በሚገልጹ ተከታታይ ስርዓቶች እንደሚሞሉት ይገልጻሉ፡፡ ልማዳዊ የሆነው የክርስቲያኖች የቀን መቁጠርያ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፣ ስቅለት፣ ሞት እና ትንሣኤን ያካትታል፡፡ ተጨማሪ የሆኑ የቅዱሳን ቀኖች እና ሌሎች ዓመት በዓሎችም በትውፊቱ ውስጥ ስለተፈጠሩ ይከወናሉ፡፡ ዓመታዊ ስርዓቶች ታሪካዊ የሆነውን ጉዳይ ወደ ተቀደሱ ሚቶች ይቀይሩታል፤ በየዓመቱም በተደጋጋሚ ይከወናሉ፡፡ በመጨረሻም ትልቅ ምስል በመፍጠር የከዋኔው ተግባር ማንነትን እስከመገንባት ይደርሳል፡፡

### 2.1.3.የእምነት ውህደት (syncretism)

"*syncretism*" *[syn]* "*with*" እና *[krasis]* "*mixture*" ከሚሉት ሁለት የግሪክ ጥንታዊ ቃላት የመጣ ሲሆን ቃላቱ በጥምረት "ውህደት" *(a mixing together, compound)* የሚል ፍቺ እንደሚሰጡን የተለያዩ ምሁራን፣ ለምሳሌ ስትዋርት እና ሾው (Stewart and Shaw) ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የእምነት ውህደት "*syncretism*" የተሰኘው እሳቤ በታሪክ ውስጥ የተለያዩ ፍቺዎች እየተሰጡት አሁን ካለንበት ዘመን እንደደረሰና አሁንም ድረስ አወዛጋቢነቱ እንደቀጠለ ከገለጹ በኋላ በሪቻርድ ዌብነር ሀሳብ እንደሚስማሙ ያስረዳሉ፡፡ ዌብነር የተባለው ተመራማሪ በ 1992 ዓ.ም በአሜሪካ የስነ ሰብእ ማኅበር ስብሰባ ላይ "*syncretism*" ማለት የተለያዩ ሁለት ታሪካዊ ትውፊቶች አካል የሆኑ የሃይማኖትና የስርዓት ገጽታዎች መጣመር እንደሆነ መግለጹን ይጠቁማሉ (1994:3-9)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የእምነት ውህደት የሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ልማዳዊ ባህሎች መዳቀል እና አንድ መሆን ነው፤ በማለት በርናርድ እና ዮናታን (Barnard and Jonathan, 2002፡ 812) ያስረዳሉ፡፡ የእምነት ውህደት *(religious syncretism)* ሲባል በቀላሉ ከጎረቤት እቃ

እንደመዋስ ሳይሆን የሌላውን መውረስን እና ከራስ ጋር ማዋሀድን የሚጠይቅ እንደሆነ ማሮኒ (Maroney) ይገልጻሉ (2006: 6)።

እነዚህንና መሰል ፍቺዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የእምነት ውህደት ይኖር ዘንድ በመጀመርያ ደረጃ ቢያንስ ሁለት የተለያዩ ትውፊቶች እና እምነቶች ሊኖሩ እንደሚገባ መገመት ይቻላል። አብዛኛውን ጊዜ የእምነት ውህደት ሲፈጠር መፈጠሩ ሳይታወቅ (የእምነት ውህደት መፈጠሩን ማኅበረሰቡ ሳይገነዘበው) ሊቆይ እንደሚችል እና ይህም ንቁ ያልሆነው የእምነት ውህደት መልክ (ቅርጽ) እንደሆነ ሌዎልፖልድ እና ጄፒ (Leolpold and Jeppe) የተባሉ ምሁራን ያስረዳሉ (2004: 4)።

እምነቶቹ መጣመር፣ መወራረስና መዋሀድ አለባቸው። በሁለት የተለያዩ ባህሎች መካከል እንደ ወረራ፣ ንግድ፣ ስደት፣ የሃይማኖት ስርጭት/መስፋፋት እና የጋብቻ ትስስር ወዘተ. የመሰሉ ሁኔታዎች ሲከሰቱ የእምነት ውህደት ሊፈጠር ይችላል። ውህደቱ ደግሞ አንዱ እምነት ሌላውን ተቋቁሞ ወይም ደግሞ የራሱን ሙሉ ለሙሉ ሳይለቅ ከጊዜ በኋላ የሌሎችንም ይዞ የመዝለቅ ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ስትዋርት እና ሾው (20) የአንደኛው እምነት ተከታዮች በሌላው ላይ የሚፈጥሯቸው ተጽዕኖዎች በቀላሉ ተቀባይነት እንደማያገኙ ያስረዳሉ። በዚህም የተነሳ የባህል ለመዳው በአንዴ የሚካሄድ ሳይሆን በጣም በጥቂቱ፣ የተወሰነ ለውጥ ተደርጎበት፣ እንደገና ፈርሶ ተሰርቶ እንዲሁም እንደገና ተገንብቶ የሚካሄድ ነው።

በሌላ በኩል ሌዎልፖልድ እና ጄፒ ተጽእኖ ፈጣሪ የሆነው ባህል "በዝቅተኛው" ባህል ባለቤቶች ላይ ተጽእኖ በመፍጠር ውህደቱ ሊፈጠር እንደሚችል ይገልጻሉ። እንዲህ ባለ ኹኔታ የሚፈጠረው የእምነት ውህደት የተጽእኖ ፈጣሪዎቹን ኃይል በመቋቋም እና "ሀገር በቀል የሆኑትን አማልክት" (indigenous gods) በተጽእኖ ፈጣሪዎቹ አማልክት ስም የማምለክ ውጤት እንደሆነ ያስረዳሉ (4)። ከእነዚህ ሐሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የእምነት ውህደት በሁለት የተለያዩ ባህሎች መካከል በሚፈጠሩ የተለያዩ ግንኙነቶች አልያም ደግሞ በተጽእኖ ምክንያት ሊከሰት ይችላል። በእነዚህም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ውህደቱ በሚፈጠርበት ጊዜ ግን ተጽእኖ የሚደረግበት ባህል ባለቤቶች የተጽእኖ ፈጣሪዎችን እምነት ለመቋቋም ጥረት ያደርጋሉ።

የእምነት ውህደት በአንድ ሃይማኖት ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ስርዓቶች ከሌላ በውሰት የመጡ ናቸው? ብሎ ይጠይቃል፡፡ በውሰት ከመጡ ውሰቱ እንዴት እንደተካሄደ እና አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን አይነት ትርጉም እንደሚሰጠው ይመረምራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስለ ሃይማኖቶቹ ምንጮች፣ በባህሎች መካከል ስለተፈጠሩ ውርርሶች እንዲሁም የሌላውን ባህል በመቀበላቸው ምክንያት በመጡት ተጽዕኖዎች ዙርያ የተለያዩ ታሪካዊ ጥያቄዎችን ይሰነዝራል በማለት ስትዋርት እና ሾው ያስረዳሉ (128)፡፡

ለጥያቄዎቹ መልስ በሚሰጥበት ጊዜም በባህሉ ውስጥ የእምነት ውህደት እንዴት እንደተፈጠረ ብቻ ሳይሆን ሁለት የተለያዩ እምነቶች በምን መልኩ በአንድነት ተዋህደው እንደሚገኙ ትንታኔ ይሰጣል ማለት ነው፡፡ የእምነት ውህደት የልዩነት እና የማንነት ትግል መሆኑን ስትዋርት እና ሾው (196) ሲያስረዱ የእምነት ውህደት የልዩነትና የማንነት ትግል (politics) እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ "እውነተኛውን" ሃይማኖት ለይቶ የተወሰኑ ተግባራትን እንደ "እውነት" ሌሎችን ደግሞ እንደ "ሀሰት" መፈረጅ አስቸጋሪ ነው፡፡ የእምነት ውህደት በአንዳንዶች ዘንድ ተቻችሎ መኖርን የሚሰብክ አወንታዊ እሳቤ ተደርጎ ሲቆጠር በሌሎች ደግሞ "ንጹሕ የሆነው እምነት" "ንጹሕ ባልሆነው" መመረዙን የሚያሳይ አሉታዊ እሳቤ ነው፡፡

ባጠቃላይ ክዋኔ፣ ስርዓት እና የእምነት ውህደት እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው ሊቆሙ የሚችሉ እንደሆነ ቢታወቅም ጨርሰው የተፋቱ ስላልሆኑና ለጥናቴ አስፈላጊ ሆነው ስላገኘኋቸው በዚህ ጥናት ውስጥ ተገልግዬባቸዋለሁ፡፡ በዚህም መሠረት ቦውማን ማኅበራዊና ባህላዊ ተብለው የሚከፈሉትን የአውድ ዋና ዋና ገጽታዎች በጥልቀት ለመመርመር የሚያስችል ስድስት ንኡሳን ክፍሎች ማለትም የፍቺ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ ሁኔታዊ አውድ፣ ማኅበራዊ መሠረት፣ ግለሰባዊ አውድ እና የተግባቦት ስርዓት አውድ የተሰኙትን የአውድ ገጽታዎች መሠረት በማድረግ የቃል ግጥም ትንተናዬን አቅርቤያለሁ፡፡

የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ስርዓት ሲፈጸም ነው ቃል ግጥሞቹ የተከወኑት፡፡ ይህም ስርዓት አመት ጠብቆ የሚከወን ነው፡፡ በእለቱ የዋቄፈታ እምነት ተከታዮቹ ስርዓት ሰበብ የበልግ ዝናብ እንዲዘንብ ልእለ ተፈጥሮን መማጸን ሲሆን የክርስቲያኖቹ ሰበብ ደግሞ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የእረፍት ቀን መሆኑ ነው፡፡ ሁለቱም ምክንያቶች በዓመታዊ ስርዓት ውስጥ

የሚካተቱ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ቤል በዝርዝር ካስቀመጧቸው የስርዓት አይነቶች መካከል ዓመታዊ ስርዓት ለብቻው ተመርጦ የተብራራው፡፡

የቃል ግጥም ክዋኔው እና የስርዓቱ ባለቤት የሆነው ፎክ ቡድን ከሁለት የተለያዩ እምነቶች ተውጣጥቶ የተዋሀደ ነው፡፡ አንደኛው እምነት "ትክክል" ሌላው ደግሞ "ስህተት" ተብሎ በኃይል እንዲያምን ለማድረግ ሲሞከር ተቋቁሞ የራሱን ሙሉ ለሙሉ ሳይለቅ የሌላውንም ሙሉ ለሙሉ ሳይቀበል ውህድ እምነት የፈጠረ የማኅበረሰብ ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻ የዚህ ማኅበረሰብ የእምነት ውህደት እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ እና አሁን ያለበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተንትኜ አቅርቤያለሁ፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል እና ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የመጀመርያ፣ የሁለተኛና የሦስተኛ ዲግሪን ለማሟላት በርካታ የጥናት ጽሑፎች ተደርገው እናገኛለን፡፡ ከእነዚህም መካከል የተወሰኑት ክብረ በዓል ላይ የተደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ በጣም ጥቂቶቹ (ሦስቱ) ደግሞ በዝቋላ አካባቢ የተደረጉ ናቸው፡፡

ስርዓት ላይ ከተደረጉት ጥናቶች መካከል በቤተ መጻሕፍት ፍለጋዬ ያገኘኋቸው የመሶብ ወርቅ ቅጣውን "የገና ክብረ በዓል በላሊበላ" (1997 ዓ.ም)፣ የምንዳ ገብሬን "የጌዲዮ ልማዳዊ ስርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው" (2000 ዓ.ም)፣ የሙሉቀን ዘውዱን "በባህርዳር አካባቢ ወንዞች ዳር የሚፈጸሙ የአምልኮ ስርዓቶችና ክዋኔያቸው" (2001 ዓ.ም)፣ የማሞ ተፈራን "በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ የአምልኮ ስርዓቶች በዳንግላ ወረዳ" (2002 ዓ.ም) እና የግርማ ቡኬን "የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር እና እምነት" (2003 ዓ.ም) ሲሆን ሁሉም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተሠሩ ናቸው፡፡

እነዚህ ጥናታዊ ጽሑፎች አንድም ዋና ጉዳያቸውን ቃል ግጥም አላደረጉም፣ አንድም ደግሞ በዋናነት አውዳዊ ንድፈ ሐሳብን አልተጠቀሙም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የከበራውን ስርዓት ከማኅበረሰቡ ዝርው ቃል ታሪኮች ጋር በማገናኘት ተንትነው የእምነት ውህደት ካለ አልመረመሩም፡፡ በዚህም ምክንያት በቅኝቴ ውስጥ አላካተትኳቸውም፡፡ በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝቴ ውስጥ በጥልቀት የመረመርኳቸው ትኩረታቸውን በዝቋላ አካባቢ ያደረጉትን

ጥናቶች ሲሆን እነሱም፡- የሙሉጌታ ነጋሳ (1997 ዓ.ም)፣ የታደሰ አይችሉህም (1999ዓ.ም) እና የሰሎሞን ደርቤ (2000 ዓ.ም) ምርምሮች ናቸው፡፡

በዚህ ቅኝት የተመረጡትን የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ሂሳዊ በሆን መልኩ የዳሰስኩ ሲሆን ዓላማዬን ከግብ ለማድረስ የጥናቶቹ ዓላማ፣ ዘዴ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት፣ ትንታኔና ማጠቃለያ ምን እንደሚመስል መርምሬያለሁ፡፡ በጥናቶቹ ውስጥ የተካተቱት ነጥቦች ምን ምን እንደሆኑ፣ በምን መልኩ፣ ለምን ዓላማ እንደመጡም የገለጽሁ ሲሆን ተገቢ መሆናቸውንና ተገቢ አለመሆናቸውንም መዝኛለሁ፡፡ በመጨረሻም ስለ ጥናቶቹ ያለኝን አጠቃላይ ምዘና ጠቅለል አድርጌ አስቀምጫለሁ፡፡

**ሙሉጌታ ነጋሳ** በ 1997 ዓ.ም "በ አደአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴርጉማ ከግጭት አፈታት አንጻር" በሚል ርእስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የጥናት ጽሑፉን አቅርቧል፡፡ የሙሉጌታ ጥናት ዓላማዎች ሦስት ሲሆኑ የመጀመሪያው የኦሮሞ ሴረጉማ ምንነትን ከግጭት አፈታት አንጻር በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን /የሚኖረውን/ ማኅበራዊ ጠቀሜታ ማሳየት የሚል ነው፡፡ የሴረጉማን ክዋኔዎችና ማኅበራዊ አውድ በቴፕሪከርደር፣ በፎቶግራፍና በቪዲዮ ካሜራዎች በመቅረጽ ለመረጃ ምንጭነት ማመቻቸት እና በሴረጉማ የግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ ባህላዊ አባቶችና ሌሎችም ተሳታፊዎች የሚጫወቱትን ሚና ማስተዋወቅ የሚሉት ደግሞ በሁለተኛ እና በሦስተኛ ደረጃ የዘረዘራቸው ዓላማዎች ናቸው፡፡ ሙሉጌታ በዓላማነት ካስቀመጣቸው ሐሳቦች መካከል የመጀመርያው ተገቢነት ያለው ሲሆን ቀሪዎቹ ግን የአንድ ፎክሎር ተመራማሪ ዓቢይ ዓላማ ሊሆኑ የማይችሉ ነጥቦች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ጥናት የሚካሄደው ለመረጃ ምንጭነት ለማመቻቸት እና ለማስተዋወቅ ሳይሆን የማኅበረሰቡን ዕውቀት እና የሕይወት ፍልስፍና ለመመርመር ቢሆን የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

ሙሉጌታ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ምልከታንና ቃለ መጠይቅን ተጠቅሟል፡፡ ቅንብር ተፈጥሯዊ አውድን በማዘጋጀት በቴፕሪከርደር፣ በፎቶግራፍና በቪዲዮ ካሴት በመጠቀም ሴርጉማን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቧል፡፡ የቡድን ውይይትም በተወሰነ መልኩ መጠቀሙን ይገልጻል፡፡ በምልከታው ወቅት ተፈጥሯዊ መቼት ያልተጠቀመበትን ምክንያት ግልጽ ማድረጉ በጥሩ ጎንነት ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ምልከታ ባደረገበት ወቅት /ከ ነሀሴ 15- መስከረም 30/ ክረምት ስለሆነና ወንዝ ስለሚሞላ አስታራቂ ሽማግሌዎች

ወንዝ ተሻግረው ስለማይገናኙ ነው ብሏል፡፡ ከመስከረም በኋላም መደበኛ የትምህርት ወቅት ስለሆነ መመልከት እንዳልቻለ ጠቁሟል፡፡ ሁለተኛው የመስክ ቆይታ (አርቴፊሻል መቼት ተጠቅሞ መረጃ የሰበሰበበት) ከየካቲት 15/1997 በኋላ ሆኖ እያለ በዚህ ወቅት ተፈጥሯዊ አጋጣሚው ስለመኖሩ የገለጸው ነገር አለመኖሩ ግን እንደ ክፍተት ሊታይ ይችላል፡፡

በጥናቱ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ስለ ግጭት አጠቃላይ ሁኔታ አስረድቷል፡፡ "የግጭት አፈታት ከአንዳንድ ድርጅቶችና የህግ ሰነዶች አንጻር (የተባበሩት መንግስታት፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረት፣ የአፍሪካ ቀጠናዎች መንግሥታት፣ የኢትዮጵያ የህግ ሰነዶች)" እና "የአድአ ሊበን ወረዳ ከግጭት አንጻር" በሚሉ ሁለት ንዑሳን ርእሶች ከፋፍሎ አብራርቷል፡፡ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ በዚህ መልኩ መቅረብ አለበት ብዬ አላምንም፡፡ ከዛ ይልቅ በፎክሎር ዲሲፕሊን ውስጥ በሚገኙት እና እንደ Performance, ritual, functionalism, myth ባሉት ንድፈ ሐሳቦች አማካኝነት ጥናቱን ሊመረመር ይገባ ነበር፡፡

ወደ ጥናቱ የትንታኔ ክፍል ስንሄድ በንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት ክፍሉ የተፈጠረው ክፍተት አላሰራ ሲለው እንመለከታለን፡፡ የሜርጉማ ማኅበራዊ ፋይዳ በማለት ፍትህ ከማስገኘት አንጻር፣ ዘላቂ ሰላም ከማስገኘት አንጻር፣ ስነ ልቦናዊ መረጋጋትን ከማስገኘት አንጻር፣ ልማዳዊ ዕውቀት ከማስጨበጥ አንጻር ብሎ በመዘርዘር በንድፈ ሐሳብ አማካኝነት ሳይተነትን መረጃ ሰጪዎቹ የነገሩትን በቀጥታ ያስቀምጣል፡፡ የግጭት አፈታት ክዋኔ ስርዓቶቹንም እንዲሁ በቅደም ተከተል አስፍሯቸዋል፡፡

የጥናቱ ግኝት በመስኩ የነበረውን ክፍተት የሚሞላ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ምንም እንኳን በንድፈ ሐሳብ ታግዞ በወጉ የተተነተነ ባይሆንም ከዚህ በፊት በአካባቢው ስላለው የግጭት አፈታት ሁኔታ ጥናት ስላልተካሄደ የማኅበረሰቡ የግጭት አፈታት ሁኔታ ምን እንደሚመስል መግለጽ ችሏል ብዬ አስባለሁ፡፡ በዚህም መሠረት ሜረጉማ በዘመናዊ የፍርድ ሂደቶች የሚያጋጥሙ ክፍተቶችን መሙላት የሚችል ማለትም ጠበኞቹ ከታረቁ በኋላ ቂም እንደማይዙ በቀልም እንደማይኖር እንዲሁም የጊዜና የገንዘብ ብክነቱም ያን ያህል እንዳልሆነ ለማሳየት ችሏል፡፡

**ታደሰ አይችሉህም** በ 1999ዓ.ም "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ስርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ከዕለት ሕይወት ከትእምርታዊነቱ አንጻር፡-

በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ኃይማኖት ገዳማት"

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የጥናት ጽሑፉን አቅርቧል፡፡ የታደሰ ጥናት ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ ያለውን የገዳም ስርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ከዕለት ሕይወት በተመረጡት ሁለት ገዳማት አማካይነት ማሳየት ነው፡፡ ዋና ዓላማውም የተቋሙን አስተዳደራዊ አደረጃጀት፣ የገዳማውያኑን የሥራ ክፍፍል፣ የጸሎት፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ እና የጾም ስርዓት፣ የተቋሙን የግጭት አፈታት ዘዴ፣ ወዘተ. መግለጽ ነው፡፡

ታደሰ በዋናነት ቃለ መጠይቅና ምልከታን በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ተጠቅሟል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልዩ አስረጅ ሁኔታዎች (case studies) በማለት ሁለት ገዳማውያን ወደ ገዳሙ ከመጡበት ቀን ጀምሮ ምንኩስና እስከተቀበሉበት ጊዜ ድረስ ያለፉበትን ሕይወት እና አሁንም ያሉበትን ሁኔታ በዝርዝር ያሳየ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ አንድ በግጭት ወይም በጥፋት ዙርያ የቀረበ ታሪክ (በጥፋቱ ስለተባረረ ገዳማዊ የሚተርክ ታሪክ) አስገብቷል፡፡ ይህን ዓላማ የያዘ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ሊያደርግ የሚገባው ምልከታን ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ ደግሞ የምልከታን ክፍተት ለመሸፈን ያገለግላል፡፡ ታደሰ ግን አቀያይሯቸዋል፡፡ ይህም እስከ ጥናቱ መጨረሻ ድረስ ችግር ሲፈጥርበት ይታያል፡፡

የታደሰ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች በክህነት ደረጃቸው፣ በመንፈሳዊ የትምህርት ዕውቀታቸው፣ ምንኩስናን ከተቀበሉበት ጊዜ አንጻር፣ በአመክሮና በደጅ ጠኝነት ከሚገኙ፣ በአርድእትነት የሚያገለግሉ፣ ወዘተ. መከተታቸው የተሟላ መረጃ እንዲያገኝ እና ያገኘውንም እንዲያነጻጽር ስለሚረዳው በጥሩ ጎንነት ሊታይ የሚችል ነው፡፡

ታደሰ ገላጭ የምርምር ዘዴ እና ትእምርታዊ መስተጋብራዊነት ንድፈ ሐሳብ (symbolic interactionism theory) መሠረታዊ መርሆዎችን በመጠቀም ትንተናውን አካሂዷል፡፡ በእርግጥም መርሆዎቹን በትንተናው ውስጥ ሲጠቀምባቸው ይታያል፡፡

ነገር ግን የታደሰ ጥናት ዋና ዓላማ የተቋሙን አስተዳደራዊ አደረጃጀት፣ የገዳማውያኑን የሥራ ክፍፍል፣ የጸሎት፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ እና የጾም ስርዓት፣ የተቋሙን የግጭት አፈታት ዘዴ፣ ወዘተ. መግለጽ ሆኖ እያለ ትእምርታዊ ንድፈ ሐሳብን ብቻ መጠቀም በቂ ነው ብዬ አላስብም፡፡ ምክንያቱም በዓላማው ውስጥ የተዘረዘሩት ነገሮች ከግብ ሊደርሱ

የሚችሉት በዚህ ንድፈ ሀሳብ አጋዥነት ብቻ አይደለምና፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ በዓላማው ላይ የተዘረዘሩትንና በእነዚህ ንድፈ ሐሳቦች አማካኝነት ሊሠሩ ይገባቸው የነበሩ ክፍሎችን ማካተት አልነበረበትም፡፡

የጥናቱን የትንታኔ ክፍል በምንመለከትበት ጊዜ በዓላማውና በንድፈ ሐሳባዊ ዳራው ላይ ተከስተው የነበሩት ክፍተቶች በዚህ ክፍል ላይ ችግር ፈጥረውበታል፡፡ ክፍተቱን ለመሙላትም በምልከታ አማካኝነት ሊሰበሰቡ ይገቡ የነበሩትን መረጃዎች በቃለ መጠይቅ ሲሰበስባቸው ይታያል፡፡ በዚህም መሠረት የአስተዳደር ስርዓትና የሥራ መዋቅር በሚል ንዑስ ርእስ ስር የአበምኔት አመራረጥና የሥራ ኃላፊነት፣ የግጭት አፈታት ዘዴ እና በጥፋቶች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች፣ የእንግዶችና የአዲስ አባላት አቀባበል እንዲሁም የምንኩስና አቀባበል ስርዓት በሚሉ ንዑስ ርእሶች አማካኝነት በቃለ መጠይቅ ያገኘውን መረጃ ተንትኗል፡፡ ታደሰ ምልከታን የቃለ መጠይቅ አጋዥ እንጂ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ባለማድረጉ ክዋኔውን ቸል ብሎታል፡፡ ከዚህ ውጪ ትእምርታዊነትን መነሻ አድርጎ የተሰራው ትንታኔ ጠንካራና ከጥናቱ አንድ ዓላማ ጋር የሚያያዝ ነው፤ ብዬ አስባለሁ፡፡

በታደሰ ጥናት የማጠቃለያ ክፍል መጀመርያ ላይ የሰፈሩት ሐሳቦች ከመጻሕፍትና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ ናቸው፡፡ የመረጃዎቹ ትኩረትም ስለ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ገዳም፣ ደብርና ገጠር ስሪቶች ምንነት እንጂ እሱ ጥናት ስላደረገባቸው ገዳማት የሚገልጹ አይደሉም፡፡ ቀጥሎ የቀረበው መረጃም እንዲሁ ስለ ምንኩስና ሰፋ ያለ ትንታኔ ይሰጣል፡፡ ትኩረቱን ስላደረገባቸው ገዳማት ማጠቃለያ ሲሰጥም በትንታኔው ክፍል ያቀረባቸውን ሐሳቦች በአጭር በአጭር አስቀመጣቸው እንጂ የጥናቱን ግኝት በወጉ አልገለጸም፡፡

**ሰሎሞን ደርቤ** በ 2000 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት ያቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ‹‹የዝቋላ አቦ ክብረ በአል አከባበር›› የተሰኘ ርእስ ያለው ሲሆን ዓላማውም በዝቋላ ተራራ ጫፍ ላይ የሚከበረውን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክብረ በዓል ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳወቅ እና የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል መከበር ያለውን ፋይዳ መመርመር ነበር፡፡ ጥናቱን ለማሳካት በዋና መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የተገለገለው ቃለ መጠይቅንና ምልከታን ነው፡፡ በሰሎሞን ጥናት ውስጥ ቀደም ሲል በቃኘሁት፣ በታደሰ አይችሉህም

የጥናት ሥራ ውስጥ የታየው ክፍተት ሲደገም ይታያል፡፡ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴውም ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ምልከታን ሁለተኛ ያደርገዋል፡፡ ነገር ግን የሰሎሞንን ዓላማ የያዘ አጥኝ ምልከታን፣ ቃለ መጠይቅንና የቡድን ውይይትን በቅደም ተከተልና በአግባቡ ሊጠቀምባቸው ይገባል፡፡

የበዓሉን ክዋኔ በወቅቱ ተሳታፊ በመሆን በቪዲዮና ፎቶግራፍ ካሜራዎች እንዲሁም በቴፕሪከርደር የመቅረጽ እድል አግኝቷል፡፡ በበአሉ ላይ መገኘቱና መቅረጹ ደግሞ ተፈጥሯዊ መቼት መጠቀሙን ይጠቁመናል፡፡ ይህም ከበራውን ከነ ክዋኔው ይበልጥ ለመረዳት የበለጠ አመች የሆነ የመረጃ መሰብሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ የመረጃ አቀባዮቹ ስብጥር የሃይማኖት አባቶችን፣ ዲያቆናትን፣ ወጣት ወንዶችና ሴቶችን እንዲሁም የተለያየ ሙያ ያላቸውን ጎልማሳና አዛውንት የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ ነው፡፡ ይህ ስብጥር በጥሩ ጎንነት ሊታይ የሚችል ነው፡፡

ሰለሞን በንድፈ ሃሳባዊ ዳራው ስለ ክብረ በዓል (festival) እና ስለ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል (religious festival) ምንነት ብቻ ይገልጻል፡፡ ምንነቱንም የገለጸው ስለ ክብረ በአል ምንነት፣ አከባበር፣ አይነቶች የሚገልጹ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ሳይሆን የተለያዩ የአማርኛና የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላትን መነሻ በማድረግ ነው፤ ከ Smith Jrome ብያኔ ውጭ ማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለትምህርት ክፍሉ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በተሰሩ ጥናቶች ውስጥ ስለ ክብረ በአል ምንነት የገለጹትን እንደ ዋቢ መጠቀሙ አግባብ አይደለም፡፡

አንድ ማህበረሰብ እምነቱን፣ ፍርሃቱን፣ ምኞቱን፣ ውዳሴውን፣ ነቀፋውን፣ ደስታውን፣ ሀዘኑን ወዘተ. በቃል ግጥሞች አማካኝነት ይገልጻል፡፡ የዝቋላ አቦ ክብረ በአል ከዋኞችና ተሳታፊዎችም ከዚህ ውጭ ስላልሆኑ ቃል ግጥሞች ላይ የበለጠ ትኩረት ቢሰጥ ኖሮ ከዚህ የተሻለ ትንታኔና ግኝት ላይ መድረስ ይቻል ነበር፡፡ አጥኚው ለቃል ግጥሞቹ ያን ያህል ትኩረት መስጠት አስፈላጊ አይደለም ብሎ ቢያምን እንኳን ክብረ በአሉን አሁን ካደረገው ሰፋ ባለ መልኩ ከከበራ ስርአት ንድፈ ሀሳብ (ritual theory) አንጻር የበለጠ ቢመረምረው ጥሩ ይሆን ነበር፡፡ ሰለሞን በአላማው የገለጻቸውን ዝርዝሮች ከግብ ለማድረስ ከክዋኔ ንድፈ ሀሳብ (performance theory) ወይም ከአውዳዊ ንድፈ ሀሳብ (contextual theory) አንጻር ቢተነትነው እንዲሁም እመረምራለሁ ያለውን የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል መከበር ያለውን ፋይዳ ለመረዳት "functionalism theory" መጠቀም ነበረበት ብዬ እስባለሁ፡፡

ይህም ባለመሆኑ የተነሳ በንድፈ ሀሳባዊ ዳራው ክፍል ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እና ስለ ዝቋላ ገዳም የክብረ በአል አከባበር ከመጻህፍት እና ከተለያዩ ሰዎች ያገኘውን መረጃ ሊያሰፍር ችሏል፡፡ የክብረ በአሉን አከባበር መገለጽ የነበረበት በዚህ ክፍል ሳይሆን በአጥኚው የንድፈ ሀሳብ እውቀት (etic) እና የመስክ መረጃ (emic) ላይ ተመስረቶ በሚካሄደው የትንተና ክፍል ውስጥ ነበር፡፡ በትንተናው ክፍል ውስጥም በንድፈ ሀሳባዊ ዳራነት ያስቀመጣቸው መረጃዎች ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚመስል መልኩ ከዋዜማው ጀምሮ በእለቱ ጠዋት እና ቀን የተደረጉትን የክዋኔ ሂደቶች መዘርዘር ላይ አተኩሯል፡፡

በበዓሉ ዋዜማ ቅዱስ ያሬድ ከደረሰውና «አንቀጸ ብርሃን» ከሚባለው የማርያም ምስጋና ከተደገመ በኋላ ዝማሜ እንደሚካሄድ በመቀጠልም በጸናጽልና በከበሮ ተዘምሮ እንዳበቃ ካህኑ መንገድ ስለሄዱ ሰዎች ልመናና ጸሎት አድርሶ ምድር ሁሉ የእግዚአብሄር ናት የሚለውን የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በዜማ እንደሚቀባበሉት ይገልጻል፡፡ ይህም እንዳበቃ የጻድቁን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ክብር የሚያሞግስ ዋዜማ ቅኔ ይደረሳል በማለት ያብራራል፡፡ በመቀጠልም ስለተለያዩ ጉዳዮች ከተጸለየ በኋላ በድጋሜ ቅኔ ይደረሳል፤ በማለት የዋዜማውን አከባበር ገልጾታል፡፡

ከዚህ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ሰሎሞን ያለውን ሁኔታ ከመግለጽ ባሻገር ከተደረሱት ቅኔዎች መካከል ማሳያ ሊሆኑ የሚችሉ ቃል ግጥሞችን በማቅረብ ከአውዱ ጋር አዋህዶ ለመተንተንም ሆነ የተሳታፊዎቹ ምላሽ ምን ይመስል እንደነበረ ለማሳየት አልሞከረም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዋዜማው ማታ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ከዋኞቹ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ለእለቱ የሚስማሙ ጸሎቶችንና ዝማሬዎችን እየተቀባበሉ እንደሚያቀርቡ ከመግለጽ አልፎ ስለ ቃል ግጥሞቹ ክዋኔ ሁኔታ ዝርዝር ማብራርያ ሲሰጥ አይታይም፡፡

"የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር በዋዜማው"፣ "በእለቱ በጸበሉ ዙርያ"፣ "የደለጋ ስርዓት"፣ "በቤተክርስቲያን ውስጥ የተካሄዱ ክንውኖች"፣ "በበዓሉ እለት አጣብቂኝ፣ የሰይጣን መቃብር፣ የአቡዬ ወንበር እና የአርብ ዕሮብ ዳገት" በተባሉ ስፍራዎች የተካሄዱ ክንውኖች ምን እንደሚመስሉ አብራርቷል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ የቀረቡት ቃል ግጥሞች በቁጥር ስምንት ሲሆኑ በመደብ በመደብ አልተከፋፈሉም፡፡ በበቂ ሁኔታ የተተነተኑ ሳይሆን "ተራራውን ሲወጡ ከተዘመሩት

መካከል"፣ "ታቦቱ ሲወጣ ከተዘመሩት መካከል" ተብለው የቀረቡ ናቸው፡፡ በጥናቱ ዋና ክፍል ውስጥ ከቀረቡት ከእነዚህ ቃል ግጥሞች ውጭ በአጠቃላይ ምን ያህል እንደተሰበሰበና ከተሰበሰበው መካከልም እነዚህ በምን መስፈርት ለትንተና እንደተመረጡ የሚጠቁም መረጃ በጥናቱ ዋና ክፍልም ሆነ በአባሪ ውስጥ አልተገለጸም፡፡

በሰሎሞን ማጠቃለያ ላይ የተጠቀሰው ግኝት የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል መንፈሳዊ እርካታ የሚገኝበት፣ ከህመም የሚፈውስ፣ ህይወት ያለው የባህላዊ ጥበብ ማከናወኛ የህዝቦች የባህል መድረክ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ሰሎሞን እንዲህ አይነት ድምዳሜ ላይ ከመድረስ ይልቅ ከክዋኔዎቹ ማህበረሰቡ አንዳች በረከትና ደስታ አገኛለሁ ብሎ እንደሚያምን ቢገልጽ የተሻለ ነበር ብዬ አምናለሁ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዝቋላ አቦ ክብረ በአል ሃይማኖታዊ ሥርአቶች (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥርአቶች) እና ሀገር በቀል አምልኮዎች የሚከወኑበት ስለሆነ ክበራው "ዝንቅ" የሆነ ኢትዮጵያዊ መልክን የሚያጸባርቅ ፎክሎራዊ ገጽታ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በመጀመርያ ደረጃ "የኢትዮጵያ መልክ" በዚህ መልኩ ነው የሚገለጸው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ስለ ክብረ በአሉ ዝንቅነት መጠቀስ የነበረበት የሰሎሞንን አይነት ዓላማ ይዞ በመነሳት አልነበረም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አጥኚው በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ካገኛቸው መረጃዎች በመነሳት የክርስቲያኖቹ ክብረ በዓል ከዋዜማው ጀምሮ አስከ በአሉ ፍጻሜ ድረስ ምን እንደሚመስል አብራርቷል፡፡ የሀገር በቀል አምልኮውን ግን በጥልቀት አልተመለከተውም፡፡ በምክንያትነት ያቀረበው ሀሳብ ደግሞ ቄሶቹ ስለ ሀገር በቀል አምልኮው መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደሉም የሚል ነው፡፡ ይህ ግን አሳማኝ አይደለም፡፡ ምክንያቱም መረጃውን መጠየቅ የነበረበት ከእምነቱ ተከታዮች እንጂ ከማይመለከታቸው ወገኖች (ከቄሶች) አልነበረምና፡፡

ሰሎሞን ትንታኔውን የሚያቆምበት ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ሳይኖረውና የሁለቱንም ወገኖች ክብረ በአላት (የክርስቲያኖቹን በዝርዝር እና የሀገር በቀል አምልኮ ተከታዮችን በወፍ በረር) በተናጥል አቅርቦ "ዝንቅ ምልአት" የሚል ግኝት ማስቀመጡ አግባብነት የለውም እላለሁ፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዋና ክፍተቶች በንድፈ ሀሳብ አለመታገዙ፣ የአንድን ክብረ በአል ፎክሎራዊ ገጽታዎች ሁሉ ተጠየቃዊነት በሌለው መልኩ መመርመሩ (መታገጊያ

አለማበጀቱ)፡ ክብረ በዓሉን ከቃል ግጥሞቹ ከዋኔ ነጥሎ ማየቱና በቃል ግጥሞቹ ከዋኔዎች አማካይነት የከዋኞቹንም ሆነ የተሰታፊዎቹን እምነትና የህይወት ፍልስፍና ማየት እንደሚቻል ልብ ካለማለቱ የመጣ ነው፤ ብየ እስባለሁ፡፡ በጥናቱ ውስጥ የቀረበትም ቃል ግጥሞች በወጉ አለመተንተናቸው ሌላው ክፍተት ሲሆን የመረጃ አሰባሰብ ዘዴውም የራሱ የሆነ ክፍተት የሚታይበት ነው፡፡

በአጠቃላይ የሦስቱንም አጥኝዎች የጥናት ዘዴ በምንመለከትበት ጊዜ ለመረጃ ማሰባበሲያ ዘዴያቸው እንጂ ለመተንተኛ ዘዴያቸው ትኩረት ሲሰጡ አይታዩም፡፡ ከታደሰ ጥናት በስተቀር፡ የትንታኔ ክፍላቸው በንድፈ ሀሳብ የታገዘ አይደለም፡፡ ማጠቃለያቸውም ከጥናታቸው አላማ ጋር ተያይዞ ግኝታቸውን የሚጠቁም፡ ሌላ አጥኝን የሚጋብዝ ሳይሆን አጠቃላይ ጥናታቸውን በአጭር በአጭሩ ያስቀመጠ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ክፍተቶች እንዳሉ ቢሆንም በርእሶቻቸውና በጥናቶቻቸው መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ይታያል፤ ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት ትኩረታቸውን በሊበን ጩቃላ አካባቢ ያደረጉት እነዚህ ጥናቶች ከፎክሎር ዲሲፕሊን የንድፈ ሀሳብና የስነዘዴ እሳቤዎች አንጻር በተገቢ መልኩ ተሰርተዋል ማለት አይቻልም፡፡ የእኔ ጥናት በተለይም በቃል ግጥሞቹ ከዋኔና የእምነት ውህደት ላይ ያሉትን ክፍተቶች ይሞላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

## ምእራፍ ሦስት

# 3. የቃል ግጥም ከዋኔና የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል

በዚህ ምእራፍ በዋናነት ሦስት ንኡሳን ርእሶችን አካትቻለሁ፡፡ በመጀመርያው ንኡስ ርእስ ከዋኔው የተካሄደበትን ወረዳ መልካምድራዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎች ዳስሻለሁ፡፡ በመቀጠልም የዝቋላ አቦ ክብረ በአል መከወኛ ስፍራ ምን እንደሚመስል ቃኝቻለሁ፡፡ ከቃል ግጥሙ ጋር የሚፈጸሙ ስርአቶች ምን እንደሚመስሉም ገልጫለሁ፡፡ በትንተናዬ ውስጥም ሁለቱንም እምነቶች አዋህደው የሚከተሉት የማህበረሰብ ክፍሎች የቃል ግጥም ከዋኔን የመባያ ጉዳዮች በማህበረ ባህላው አውድ ውስጥ አስገብቼ የተነተንኩት ደግሞ በሁለተኛው ንኡስ ርእስ ነው፡፡ በመጨረሻም የእምነት ውህደቱ እንዴት ሊመጣ እንደቻለ እና አሁን ያለበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በመተንተን ምእራፉን አጠናቅቂያለሁ፡፡

## 3.1 . የሊበን ጩቃላ ወረዳ መልካምድራዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች[2]

ከ1998 ዓ.ም በፊት የሊበን ጩቋላ (ዝቋላ) ወረዳ በአደአ ሊበን ወረዳ ውስጥ ይካተት ነበር፡፡ ከየካቲት 1998 ዓ.ም በኋላ ግን ራሱን ችሎ አንድ ወረዳ ሆኗል፡፡ የሊበን ጩቋላ (ዝቋላ) ወረዳ በኦሮምያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን ውስጥ ከሚገኙት አስር (10) ወረዳዎች መካከል አንዱ ሲሆን 18 ቀበሌ ገበሬ ማህበራትንና አንድ የከተማ ቀበሌ አለው፡፡ በወረዳው ውስጥ የተለያዩ የቱሪስት መስህቦች የሚገኙ ሲሆን የጩቃላ (ዝቋላ) ተራራ፣ ሲዳ ናቤ እና የማጃ ሸለቆ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

### 3.1.1. መልካምድራዊ እና ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች

የጩቃላ ሊበን ወረዳ 642.22 ኪ.ሜ.[2] የሚሸፍን ሲሆን ከሆኑ አጠቃላይ ስፋት 6.2 በመቶ ይሸፍናል፡፡ የዚህ ወረዳ ዋና ከተማ አዱላላ ትባላለች፡፡ አዱላላ[3] አዱ እና ኢላላ ከሚሉ

---

[2] መረጃውን ያገኘሁት የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በ2001ዓ.ም ካዘጋጀውና የወረዳውን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ከሚገልጸው ጥናት (Liban Chukkala Socio Economic Profile for the year 2001 E.C.) ላይ ነው፡፡

ሁለት ቃላት የተመሰረተ ነው፡፡ ክብረ በዓሉ የሚካሄድበት ዝቋላ (ጨቃላ[4]) ተራራ ከአዲስ አበባ ከተማ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በ84 ኪሎ ሜትር ከደብረዘይት ከተማ ደግሞ በስተ ደቡብ ምእራብ በኩል በ40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

የጨቃላ ሊበን ወረዳን የሆኑ ሦስት (3) ወረዳዎችና የደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን አንድ ወረዳ ያዋስኑታል፡፡ እነዚህም በምስራቅ ሎሜ ውረዳ፣ በደቡብ ቦራ ወረዳ፣ በሰሜን አደአ ወረዳ እና የደቡብ ምእራብ ሸዋ ዞን አካል የሆነው ክርሳ እና ኮንዳሊቲት ወረዳ በምእራብ በኩል ያዋስኑታል፡፡

የጨቃላ ሊበን ወረዳ ውስጥ የሚገኘው የጨቋላ ተራራ 2989 ሜትር ከፍታ አለው፡፡ በወረዳው አሸዋ፣ ቀይ አፈር፣ ነጭ ድንጋይ እና ጥቁር ድንጋይ እና የተለያዩ ማእድናት ይገኛሉ፡፡ የአዋሽ  እና የሞጆ ወንዞች ይገኛሉ፡፡ የአየር ጠባዩም 57 በመቶ ቆላማ ፡ 23 በመቶ ወይናደጋ እና 20 በመቶ ደጋ ነው፡፡ በአካባቢው እንደ ጅብ፣ ጦጣ፣ ቀበሮ፣ አእዋፍ፣ ከርከሮ፣ የሜዳ ፍየል፣ ጃርት የመሳሰሉ የዱር እንስሳት ይገኙበታል፡፡

## 3.1.2. ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች

የወረዳው የ2001 ዓ.ም የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤትን መሰረት ያደረገው መረጃ እንደሚገልጸው በወረዳው ውስጥ 36,828 ወንዶች እና 32,173 ሴቶች በአጠቃላይ 69,001 ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል 52.4 በመቶ የሚሆኑት ከ15-64 እድሜ ያላቸው (መስራት የሚችሉ) ሲሆን ከአጠቃላዩ የወረዳው ነዋሪ ህዝብ  መካከል 94.8 በመቶ የሚሆኑት በእርሻ ስራ ላይ የተሰማሩ ናቸው፡፡

የትምህርት ቤት ስርጭቱን በምንመለከትበት ጊዜ ደግሞ አሁንም በ 2001ዓ.ም የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት ስናደርግ የምናገኘው የሚከተለውን መረጃ ነው፡፡ በወረዳው በአጠቃላይ አርባ አራት (44) ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን ሀያ ስድስቱ (26) ከ አንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል አስራ ስምንቱ (18) ደግሞ ከ አምስተኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ከዘጠነኛ ክፍል በላይ

---

[3] " "አዱ" ፀሐይ ማለት ሲሆን "ኢላላ" ደግሞ ኑ ማለት ነው፡፡ በአንድ ላይ ኑ እና ፀሐይ እዩ እንደማለት ነው፡፡"

[4] ጨቃላ፡- ጨቃላ ማለት የታፈነ ማለት ነው፡፡

የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶችም ሆኑ ከፍተኛ ተቋማት የሉም ማለት ነው፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 11,992 ተማሪዎችና 298 መምህራን ይገኛሉ፡፡

በሊበን ጩቃላ ወረዳ 15 ጤና ኬላዎች፣ እና 3 ጤና ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ በጤና ተቋማቱ ውስጥ የሚሰሩ አርባ አራት (44) የጤና ባለሙያዎች አሉ፡፡ ማህበረሰቡ የሆስፒታል አገልግሎት የሚያገኘው ከጎረቤት ከተሞች ነው፡፡

በ1999 ዓ.ም እና በ2000 ዓ.ም በወረዳው በተለይም በአዱላላ ከተማ ውስጥ በመጠጥ ውሀ እና የኤሌክትሪክ መብራት ሃይል አቅርቦት በኩል የታየው መሻሻል በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ በጥቂት አመታት ውስጥ የሊበን ጩቃላ ወረዳ እንደ ጎረቤት ከተሞች ማለትም እንደ ቢሸፍቱ እና አቃቂ የማደግ ተስፋ ይኖረዋል፡፡

በክልሉ ውስጥ እንደሚገኙ ሌሎች ዞኖችና ወረዳዎች ሁሉ የሊበን ጩቃላ ወረዳም ኦሮምኛ ቋንቋን ለስራ እና ለትምህርት ቋንቋነት እንደሚጠቀም የ2001 መረጃን መሰረት ያደረገው የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጥናት ይጠቁማል፡፡ ይህን ማለት ግን በወረዳው ሌሎች ቋንቋዎች አይነገሩም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ምን ያህል ቋንቋዎች ምን ያህል ከመቶ እንደሚናገሩ የሚጠቁም መረጃ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ በወረዳው ከመንግስታዊ የፍትህ ተቋማት በተጨማሪ የገዳ ስርአት የተጣሉትን በማስታረቅ፣ ለተጎዱት ካሳ በማስከፈል የራሱን አተዋጾ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

በሊበን ጭቋላ ወረዳ የሚገኙ ማህበረሰቦች በዋናነት የዋቄፈታ፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና፣ የፕሮቴስታንት እና የእስልምና እምነቶች ተከታዮች ናቸው፡፡ የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች "ከጥንት ጀምሮ በአካባቢው የነበርን እኛ ነን፤ ክርስትና ዘግይቶ የመጣ ሃይማኖት ነው፤" ይላሉ፡፡ ክርስትና ብቻ ሳይሆን እስልምናም ወደ አካባቢው ዘግይቶ እንደመጣ ባለፈው ስምንት ዓመት ስልጣን ላይ የነበሩት አባገዳ ለገሰ ነገዎ (ቃለ መጠይቅ፣ ታህሳስ 23/2005) ይናገራሉ፡፡

ክርስቲያኖቹ ይህንን ሀሳብ አይቀበሉም፡፡ ከዛ ይልቅ በስድስተኛው ክፍለ ዘመን ቅዱስ ያሬድና አፄ ገብረ መስቀል በእግዚአብሄር ፈቃድ ወደ ዝቋላ በመምጣት የተራራውን አቀማመጥ እና ጠቅላላ አካባቢውን ካደነቁ በኋላ በአካባቢው ታቦተ እግዚአብሄር አብን እንደተከሉ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅዱስ ያሬድ ቦታውን ባርኮ ሰባት ቀን ቆየ፡፡

በዚህ ጊዜ ቦታው በኋላ ዘመን ታላቅ ስመጥር ገዳም እንደሚሆን ተንብዮ እንደነበር ያምናሉ (ዳንኤል፡፡ 1999፡ 400)፡፡

## 3.2. የቃል ግጥም ክዋኔ በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል

የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል የአምልኮ ስርአት የሚካሄደው ዝቋላ ተራራ ላይ ሲሆን የእድሜም ሆነ የጾታ ስብጥር የሚታይባቸው የማህበረሰቡ አባላት ተገኝተው በከዋኝነት እና በተሳታፊነት ይከውናሉ፡፡ በዚህ ንኡስ ርእስ ሦስቱንም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የአምልኮ ስፍራው እና ከቃል ግጥሙ ጋር የሚከወኑ ስርአቶች ምን እንደሚመስሉ ገልጫለሁ፡፡

### 3.2.1 . የአምልኮ ስፍራ

የአምልኮ ስርአቱ የሚከናወነው በኦሮምያ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ሸዋ ዞን ሊበን ጩቃላ ወረዳ ውስጥ በሚገኘውና ከባህር ጠለል በላይ 3000 ሜትር ከፍታ ባለው የዝቋላ ተራራ ላይ ነው፡፡ ከአዱላላ ከተማ ተነስቶ ተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ በሀገሬው ሰው (ለለመደው) ያለማቋረጥ ኹለት ሰዓት[5] በእግር ዳገቱን መውጣት እንደሚጠይቅ ቃለ መጠይቅ ያደረግሁላቸው ሰዎች ይናገራሉ፡፡

እጅግ ፈታኝ የሆነው አቀበት ተጠናቆ ተራራው እናት ላይ ሲደረስ የዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም በተለያዩ እጸዋት ዙርያውን ተከቦ ይታያል፡፡ ይህ ገዳም ከመገደሙ በፊት በስድስተኛው መ.ክ.ዘመን ቅዱስ ያሬድና አፄ ገብረ መስቀል ወደ ተራራው በመምጣት መልካምድራዊ አቀማመጡን ካደነቁ በኋላ የእግዚአብሄር አብን ታቦት ተክለው እንደሄዱ ዳንኤል ክብረት ይገልጻሉ (1999፡ 400)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅዱስ ያሬድ ቦታውን ከባረከው በኋላ ሰባት ቀን ሰንብቶ ከረጅም ጊዜ በኋላ ታላቅ ስመ ጥር ገዳም እንደ ሚሆን ተንብዮለት መሄዱን ያብራራሉ፡፡ ዳንኤል የዝቋላ ገዳም በግራኝ ጊዜ ጠፍ ሆኖ እንደነበርና ንጉስ ሳህለ ስላሴ (1805- 1840) እንዳደሱት እና ገዳሙ በሚኒሊክ ጊዜ የበለጠ እንደተጠናከረ ያስረዳሉ፡፡

የዝቋላ ገዳም አበምኔት አባ ተስፋ ማርያም ደበሳይ በ1129 ዓ.ም ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለመጀመርያ ጊዜ ቦታውን በጸሎት ቦታነት

---

[5] ሰዓት፡- የመስክ እረዳቶቼ እና እኔ ግን ሦስት ሰዓት ከአሥራ አምስት ደቂቃ (ከ7፡30 እስከ 10፡45) ወስዶብናል፡፡

እንደተጠቀሙበት ይገልጻሉ፡፡ አፄ እንድርያስ በ1414 ዓ.ም በገብረ መንፈስ ቅዱስ በመሰየም ገዳሙን እንደገደሙት እና መናንያን እንዲኖሩበት እንዳደረጉ ያስረዳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 5/ 2005)፡፡ የገዳሙ ጸሐፊ አባ ወልደ ሩፋኤል አበበ በበኩላቸው አፄ እንድርያስ ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም በተጨማሪ የመድኃኒአለምን፣ የማርያምን፣ የቅዱስ ሚካኤልን፣ የቅዱስ ገብርኤልን፣ የቅዱስ ጴጥሮስንና የጳውሎስን አብያተ ክርስቲያናት በዝቋላ ተራራና በዙርያው ማሳነጻቸውን ያብራራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 5/ 2005)፡፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በ1527 ዓ.ም በግራኝ ወረራ ጊዜ የፈረሱ ሲሆን የዝቋላ ገዳም ከ270 ዓመታት በላይ በጠፍንት ቆይቶ በ1804 ዓ.ም በሸዋው ንጉስ ሳህለ ስላሴ አማካኝነት ታድሶ እንደገና የባህታውያንና የመነኮሳት መኖርያ ሆኗል፡፡ በ1894 ዓ.ም ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ አሁን ያለውን ቤተክርስቲያን በሳር ክዳን ያሳነጹ ሲሆን በንግስት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት በ1915 ዓ.ም የሳሩ ክዳን በቆርቆሮ ተተካ፡፡ ቤተክርስቲያኑ አሁን ባለው ኹኔታ የታደሰው በ1993 ዓ.ም ነው በማለት እነዚህ ሁለት አባቶች ያስረዳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 5/ 2005)፡፡



ፎቶ 1. በ1993 ዓ.ም የታደሰው የዝቋላ አቦ ቤተ ክርስቲያን ይህን ይመስላል፡፡

ቤተ ክርስቲያኑ ከሚገኝበት ዳገት ወረድ እንዳሉ ወይም በዝቋላ ተራራ መሀከል ላይ የዝቋላ ሀይቅ ይገኛል፡፡ ይህን ሀይቅ የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች ነቤ (ነብይ) የተቀበረበት ቦታ ላይ የፈለቀልን ሆራ ነው ብለው እንደሚያምኑ አባገዳ ለገሰ ይናገራሉ፡፡

> ነቤ ዝቋላ ተራራ ላይ ሲቀበር ዝቋላን ጨምሮ ዘጠኝ ቦታዎች ላይ ሀይቆች ፈለቁ፡፡ እነዚህ ሀይቆች አሁንም ድረስ ይመለከባቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ተራራዎቹ እና ሀይቆቹ የተቀደሱ የአምልኮ መፈጸምያ ስፍራዎች ሆኑ፡፡ እኛም ጥቅምት 5 እና መጋቢት 5 ላይ ወደዚህ ተራራ እና ሀይቅ እየመጣን እናከብራለን፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005)

በአንጻሩ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያን ህዝብ ካልማርክልኝ ከዚህ አልወጣም በማለት ለመቶ ዓመታት (100 ዓመታት) ጸልየውበታል፤ ወደ ጸበልነትም ተቀይሯል፤ ተራራውም በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱስ ያሬድ ተባርኮልናል፤ በ12ኛው ክፍለ ዘመንም የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የጸሎት ቦታ በመሆን አገልግሏል ብለው ያምናሉ፡፡

የሀይቁ ስፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም እየጠበበ መጥቷል፡፡ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በስፈራው በሚጸልዩበት ወቅት ሀይቁ ሞልቶ በአራቱም አቅጣጫ (በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምእራብ) ወደ ታች ይፈስ ነበር፣ በአሁኑ ጊዜ ተራራው ወገብ ላይ በአራቱም አቅጣጫዎች ትንንሽ ምንጮች መፍሰሳቸው ይህንን የሚያረጋግጥ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ድንጋያማ በሆነው ተራራ ላይ ምንጮቹ በዚህ መልኩ ሊፈሱ አይችሉም ነበር በማለት የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ፡፡ በ1980ዎቹ ጭራሽ ሊጠፋ ደርሶ እንደነበረና አሁን ግን ቀስ በቀስ እየጨመረ መምጣቱንም ያስረዳሉ፡፡

ሀይቁ ዙርያውን ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ነው፡፡ ኹለት መቶ ዘጠና (290) ከሚደርሱት የዕጸዋት እና የሳር ዝርያዎቹ መካከል አስሩ (10) ብቻ በሰው የተተከሉ ናቸው፡፡ ከደኑ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ዕጸዋት የሐበሻ ጥድ፣ ወይራ፣ እስታና የኮሶ ዛፍ ናቸው፡፡

ከሀይቁ በስተ ምስራቅ አቅጣጫ ባለው የደኑ ክፍል ውስጥ የዋቄ ፈታ እምነት ተከታዮች በየዓመቱ ጥቅምት እና መጋቢት ወር ውስጥ አምልኮ ይፈጽማሉ፡፡



ፎቶ 2. ከዋኞቹ እሬቻ ያደርጉበት የነበረው የዝቋላ ሀይቅ ዳርቻ እና አሁንም ድረስ ስርዓቱን የሚፈጽሙበት ሜካ

### 3.2.2. ከቃል ግጥሙ ጋር የሚፈጸሙ ስርአቶች

መጋቢት 5 ቀን 2005 ዓ.ም የዋቄፈታ እምነትንና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖትን በአንድ ላይ በሚከተሉ የማህበረሰብ ክፍሎች የተከበረው ክብረ በዓል የተጀመረው ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት ከሃያ አምስት (11፡25) ላይ ነበር፡፡ ፈጣሪን የበልግ ዝናብ ለመለመን የተካሄደው ይህ ስርዓት የተከወነው በመዝሙርና በምርቃት ነው፡፡ የክበራ ስርአቱ ሲጀመር ከዋኞቹ እና ተሳታፊዎቹ በእጃቸው እርጥብ ቅጠል[6] ያዙ፡፡ አባገዳው የኦሮሞ ህዝብ እግዚአብሔርን አመስጋኝ፣ ፈጣሪን፣ ባህሉን እና ቋንቋውን አክባሪ እንደሆነ ከገለጹ በኋላ በሰላም ያሳደራቸው አምላክ በሰላም እንዲያውላቸው፣ ሀገራቸውን ሰላም እንዲያደርግላቸው የሚማጸን ምርቃት መረቁ፡፡

በመቀጠልም አባገዳዎች እና ሽማግሌዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለስለስ ባለ ዜማ "ኦሆ! ዞሮ መጣ ሆ…." ("Ohoo yaa mareehoo…") የሚል ዝማሬ ጀመሩ፡፡ ተሳታፊዎችም

---

[6] እርጥብ ቅጠል፡- እርጥብ ነገር ከለምለምነት እና ከበረከት ጋር እንደሚያያዝ አባ ሙዳ በየነ ይገልጻሉ፡፡ ጥቅምት ላይ ቁጠማ በብዛት ስለሚኖር በቅጠሉ ፋንታ ሳር በእጃቸው እንደሚይዙም ያብራራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005)፡፡

በተመሳሳይ ድምጽ "ዞሮ መጣ ሆ...." በማለት ተቀበሉ፡፡ በዚህ መልኩ እየተቀባበሉ በመዘመር እዛው ጫካ ውስጥ ሃያ ሜትር አካባቢ ርቆ ወደ ሚገኘው ዛፍ[7] (ኦዳ) ሄዱ፡፡

ፈጣሪ ምህረት ሊያወርድላቸው ተመልሶ መምጣቱን የሚጠቁሙ፣ እግዚአብሄር ፍጥረቱን የማይረሳ በመሆኑ እነሱንም እንዳይረሳ የሚማጸኑ ከሀያ የሚበልጡ ስንኞች ያለው ቃል ግጥም በዚህ መልኩ እየተቀባበሉ አቀረቡ፡፡ ከቀረበው ቃል ግጥም ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ስንኞች ማንሳት ይቻላል፡-

**ኦሮምኛ**

Ohoo yaa mare hoo...
Ohoo yaa mare hoo...
Yaa waaqa hunda uumtee maree hoo...
Waaqa hunda keenya maree hoo...
Mee nu ilaali waaqni maree hoo...
Dhagahi maaf diddaa maree hoo...
Nuyaadadhu jenna maree hoo...
Uumaa kee hin dagattu maree hoo...
..................................................

**ትርጉም**

እሆ! ዞሮ መጣ ሆ...፣
ሁሉን የፈጠርህ እግዚአብሔር ሆይ፣ ዞሮ መጣ ሆ...፣
የሁላችን ፈጣሪ ዞሮ መጣ ሆ...፣
ወደ እኛ ተመልከት ፈጣሪ ዞሮ መጣ ሆ...፣
ስማን ለምን እምቢ ትለናለህ ዞሮ መጣ ሆ...፣
አስታውሰን እንልሃለን ፈጣሪ ዞሮ መጣ ሆ...፣
የፈጠርከውን አትረሳም ዞሮ መጣ ሆ...፣
..............................................

"መሬ ሆ..." የሚለውን ሀረግ በያንዳንዱ ስንኝ ውስጥ ደጋግመው የተገለገሉበት ሲሆን ፈጣሪ በዓመቱ ዞሮ መጣ ማለት እንደሆነ አባገዳ ለገሰ ነገም ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005)፡፡ የፈጣሪን ትልቅነት የሚገልጹ፣ ፈጣሪ ወደ እነሱ እንዲመለከት

[7] ዛፍ፡- የሙዳ ስርአቱ ይካሄድ የነበረው ሲዳ ላይ ነበር፡፡ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ግን ሲዳው በመሰበሩ ምክንያት የሙዳ ስርአቱ በዛፍ ላይ መደረግ እንደ ጀመረ አባ ሙዳ በየነ ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005)፡፡

የሚያሳስቡ እና ቸርነቱን የሚዘክሩ ስንኞችን ያካተተውን ይህን ዝማሬ ያጠናቀቁት እንዲህ እያሉ በመዘመር ነበር፡፡

| **ኦሮምኛ** | **አማርኛ** |
|---|---|
| Adiiyyoohoo hoo... hoo... | አዲዮ ሆ ፣ ሆ... ፣ |
| Gama roobee ohoo... | ማዶ ዘነበ ኦሆ...፣ |
| Adiiyyoohoo hoo hoo | አዲዮ ሆ ፣ ሆ... ፣ |
| Gama roobee | ማዶ ዘነበ፣ |
| .................. | ............... |

"ማዶ ዘነበ" የሚለውን ዝማሬ በሚዘምሩበት ወቅት የዛፉን ዙሪያ ቅቤ እየቀቡ ነበር፡፡ ዜማው ቀደም ብለው ሲዘምሩት ከነበረው ትንሽ ፈጠን ያለ ሲሆን የፊት ገጽታቸውም ብሩህ እየሆነ መጣ፡፡ አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ ይህ ለውጥ ሊመጣ የቻለው እግዚአብሄር እንደሚደርስላቸው፣ እንደሚታረቃቸው እና ማዶ የዘነበው ዝናብ እዚህም እንደሚዘንብ ስለሚያምኑ ገና ቅቤ መቀባት ሲጀምሩ ደስተኛ እንደሚሆኑ ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/ 2005 ዓ.ም)፡፡



ፎቶ 3. አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ በቤታቸው ውስጥ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው

ዝማሬው ከተጠናቀቀ በኋላ ፊታቸውን ወደ ዝቋላ ሀይቅ አድርገው ከዛፉ ፊት ለፊት በመቆም እጆቻቸውን ወደፊት ዘርግተው ከዛፉ ስር ቆሙ፡፡ የመጀመርያው መሪቂ አንገታቸውን ሰበር በማድረግ "ደፋር አትበሉኝ፣ ሳይገባኝ ስለምናገር ይቅናህ በሉኝ" (Na ofkolchaa) አሉ፡፡ ከሌሎች ከዋኞች መሀከልም ይሁን ከተሳታፊዎች መሀከል ከእኔ

የሚበልጥ (የሚሻል) እንዳለ አውቃለሁ፡፡ ሳይገባኝ ነውና የምመርቅ አባካችሁ ደፋር አትበሉኝ፤ የሚል መልክት እንዳለው የማህበረሰቡ አባላት ይናገራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ተሳታፊዎቹ እንዲህ በማለት በቃል ግጥም አበረታቷቸው፡-

| **ኦሮምኛ** | **ትርጉም** |
|---|---|
| Ganamni nu haa ofkolchu | ንጋቱ ይቅናን፤ |
| Galgalli nu haa ofkolchu | ምሽቱም ይቅናን (ብሩህ ሁን)፡፡ |

ይህ ማበረታቻ አትፍራ፤ ተናገር፤ ሀሳብህ ሳይበታተን መርቅ እንደማለት ነው፡፡ መራቂው ይህንን ቃል ግጥም ካልሰማ መመረቅ አይጀምርም፡፡ ከዚህ በኋላ የእግዚአብሄርን ማንነት የፍጥረቱን ኹኔታና ቀዳሚ ፍጥረቶቹ እነማን እንደሆኑ የሚገልጹ ምርቃቶችን መረቁ፡፡ ምርቃቱንም የጀምሩት የአምላክን ስም በመጥራት፤ ሁሉንም ፍጥረታት እንደፈጠረና እሱ የሁሉ ፈጣሪ እንደሆነ፤ ምድርን ፍጥረታት ሁሉ እንዲጠቀሙባት አስቦ እንደ ፈጠራት እንዲህ በማለት ገለጹ፡፡

| **ኦሮምኛ** | **ትርጉም** |
|---|---|
| Hayyee waaqi (2) | አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፤ (2 ጊዜ) |
| Waaqa uumaa | ፈጣሪ እግዚአብሔር፤ |
| Waaqa uumamaa | የፍጥረታት ፈጣሪ፤ |
| Waqaa jechuun kan hundaa | እግዚአብሔር ማለት የሁሉም ነው፤ |
| Lafa jechuun kan hundaa | ምድር ማለት የሁሉም ነው፤ |
| ……………………………. | ………………………………… |

በመቀጠልም የኦሮሞን ቀዳሚዎች በመጥራት አምላክ የእነሱም ፈጣሪ እንደሆነ በሚጠቁሙ ቃል ግጥሞች "ጥቁሩ[8] አምላክ" ያሰማሯቸውን እንስሳት እንዲጠብቅላቸው፤ ሀገራቸውን ሰላም እንዲያደርግላቸው፤ መዋደድን እንዲሰጣቸው፤ ወዘተ. የሚገልጽ ረዘም ያለ ምርቃት አሰምተው "ይህ ምርቃት ይደረግላችሁ፡፡" በማለት አጠናቀቁ፡፡

ከዚህ በኋላ ሁለተኛው መራቂ "አቤቱ አምላክ ሆይ" በማለት ጀምረው እንደሚከተለው መረቁ፡-

---

[8] "ጥቁሩ"፡- አምላክ ጥቁር ነው የሚሉት ከሰማይ ጥቁረት እና ርቀት ተነስተው እንደሆነ አቦ ጫላ ሶሪ ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፤ መጋቢት 15/2005)፡፡

| **ኦሮምኛ** | **ትርጉም** |
| --- | --- |
| Hayyee waaqi (2)<br>Sagaltama Gabraa<br>Saglan Booranaa<br>Waaqa Gurraachaa garaa garbaa<br>Waaqayyo galtee fi gantee nu lagi | አቤቱ እግዚአብሄር ሆይ፣ (2 ጊዜ)<br>ዘጠናው አገልጋዮች፣<br>ዘጠኙ ቦረናዎች፣<br>ሆደ ሰፊው ጥቁር እግዚአብሄር፣<br>እግዚአብሄር ሆይ ከድንገተኛ ከስተትና ክህደት ሰውረን፡፡ |
| ...................................... | ...................................... |

መራቂው አምላክ ዝናብ እንዲያዘንብላቸው፣ ከብቶቻቸውን፣ የእህል ዘራቸውን፣ ማህበረሰባቸውን እንዲባርክላቸው የሚማጸነውን ምረቃት በሽማግሌ እንዲያሳድራቸው (እንዲያስተዳድራቸው) በመመኘት አጠቃለሉ፡፡

ሦስተኛው መራቂ "በሰላም ያሳደረ በሰላም ያውለን" ብለው በመጀመር ሰላም እንዲወርድላቸው፣ እውነት እንዲገለጥላቸው፣ እግዚአብሄር እንዲታረቃቸው ከመረቁ በኋላ በጎደለው ፈጣሪ እንዲሞላበት ተመኝተው ምርቃታቸውን ጨርሰዋል፡፡ ወደ አራተኛው መራቂ ስንመጣ ደግሞ "ለእግዚአብሄር ምስጋና ይድረሰው" በማለት ይጀምራሉ፡፡ ማህበረሰቡ የሚሠራው ሥራ ሁሉ እንዲባረክ ከለመኑ በኋላ ከመማረክ እንዲሰውራቸው፣ ልጆች የወላጆችን ቃል እንዲሰሙ፣ አምላክም የዱሮው[9] እንዲሆንላቸው ወዘተ. መርቀዋል፡፡ እግዚአብሄር የኦሮሞን ህዝብ እንዲባርክና በኦሮሞ ፈጣሪ የሚያምን እንዲባረክ የሚማጸን ምርቃት በመመረቅ አጠናቀዋል፡፡ አምስተኛው መራቂ "እግዚአብሄር ሆይ ስማን" ብለው ከጀመሩ በኋላ የከበራ ቦታቸው የእነሱ እንዲሆን፣ እለቱ በሰላም እና በደስታ በዓላቸውን የሚያከብሩበት እንዲሆን በመመኘት የምርቃት ስርአቱን አጠናቀዋል፡፡

ምርቃቱ ሲካሄድ መጀመርያ የመመረቅ እድል የሚሰጣቸው በወቅቱ አባገዳ የሆኑት ሰው ወይም ደግሞ አባገዳነት ስልጣን ከያዘው ጎሳ የመጡ የአባገዳ አባል እንደሆኑ የገዳ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ የሆኑት አቶ ጫላ ሶሪ ይገልጻሉ፡፡ አባገዳው ከመረቁ በኋላ በሚቀጥለው ስምንት ዓመት ስልጣን ከሚይዘው ጎሳ የመጡ የገዳ አባል ይመርቃሉ፡፡ አቦ ጫላ "ይህን ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ ከአምስቱም ጎሳዎች ማለትም ከቢርመጂ፣ ከቤልባ፣ ከአልቸሲ፣ ከሙደና እና ከሮበሌ የመጡ አባ ገዳዎች ወይም ደግሞ የገዳ አባላት ተራ በተራ ይመርቃሉ" (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005 ዓ.ም) በማለት ያስረዳሉ፡፡

---

[9] የዱሮው፡- ጥንት ልአለ ተፈጥሮ መሬት ላይ እየኖረ ችግራቸውን ይፈታላቸው እንደነበረ የሚተርክ ሚት አላቸው፡፡

በበዓሉ ወቅት አምስቱንም ጎሳዎች የሚወክሉ አባገዳዎች ወይም ደግሞ የገዳ አባላት ካልተገኙ በአካባቢው የሚገኙ የሀገር ሽማግሌዎች ሊመርቁ ይችላሉ፡፡ መጋቢት 5/2005 ዓ.ም በተካሄደው ክዋኔ ላይ አሁን በስልጣን ላይ ያሉት አባገዳም ሆኑ አምስቱንም ጎሳዎች የሚወክሉ የገዳ አባላት አልተገኙም[10] ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ አጠቃላይ ፕሮግራሙን ያስተባብሩ የነበሩት እና ምርቃቱን የጀመሩት ያለፈው ስምንት ዓመት ስልጣን ላይ የነበሩት አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ ናቸው፡፡ ሌሎቹ መራቂዎች ደግሞ አባ መልካ[11]ፎሌ፣ አቦ ዶሪ ሲዳ ቦታ፣ አቦ ሶምቤ ቃቻ እና አቦ ዮዬ ቡታ ነበሩ፡፡

በቃል ግጥሙ ክዋኔ ወቅት ተሳታፊዎች እጆቻቸውን ወደ ፊት አምጥተው ጣቶቻቸውን በመዘርጋት መራቂው የሚሏቸውን ስንኞች ሁሉ በመቀበል ደግመው ሲሉ ነበር፡፡ በዚህ መልኩ የምርቃት ስርአቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በቡድን በቡድን ሰብሰብ ብለው ቁጭ በማለት ዝማሬ ጀመሩ[12]፡፡



ፎቶ 4. በቡድን በቡድን ሰብሰብ ብለው ሴቶቹ የሚበላውን እና የሚጠጣውን ሲያዘጋጁ የሚያሳይ ምስል

[10] አባ ሙዳ በየነ የአሁኑ አባገዳ እና የአምስቱ ጎሳዎች የገዳ አባላት ለምን እንዳልተገኙ ሲገልጹ "በ 2002 ዓ.ም ሲዳችን ስለተሰበረብን እና ከኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች ጋር ያለው ግጭት ስላልተፈታ ዝቋላ እየሄድን ማክበሩን ትተነዋል" በማለት ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005 ዓ.ም)፡፡

[11] አባ መልካ፡- አያት ቅድመ አያቶቻቸው በአካባቢው ተወልደው የኖሩ እና በየዓመቱ ከብት በማረድ በዓሉን የሚያከብሩ ሰው ማለት ነው፡፡

[12] በፊት የምርቃት ስርአቱን እንደፈጸሙ እንደገና መሬ ሆ... የሚለውን ዝማሬ እየዘመሩ ከጫካው ወጣ ብለው ወደ ሀይቁ ዳርቻ በመሄድ እሬቻ (በእጃቸው የያዙትን ሳር ወይም እርጥብ ቅጠል ሀይቁ ውስጥ እየነከሩ ወደ ውጭ መርጨት፡፡) ያደርጉ እንደነበር አባ ሙዳ በየነ ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005 ዓ.ም)፡፡

የሙዳ ስርአቱ እና የምርቃት ስርአቱ በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀጥሎ የመጣው የቃል ግጥም ከዋኔ ዝማሬ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በተከወነው ቃል ግጥም "እግዚአብሄር ኖር መባልን ይወዳል፤ ኖር እግዚአብሄር" በማለት ሲዘምሩ ነበር፡፡ እነሱም የእግዚአብሄር ልጆች ስለሆኑ እንግዳ መቀበል ልማዳቸው እንደሆነ እና እንግዳ በመቀበላቸው ያገኙትን በረከት በመዘርዘር አዜሙ ፡ የዚህ ዝማሬ ዜማ ቀደም ሲል ከተዘመሩት ሁለት ዝማሬዎች የበለጠ ፈጣን ሲሆን ፊታቸው ላይ ይታይ የነበረው ደስታም እጅግ ከፍ ያለ ነበር፡፡ ከተከወነው ቃል ግጥም የተወሰኑ ስንኞችን እንመልከት፡-

| **ኦሮምኛ** | **ትርጉም** |
| --- | --- |
| Waaqayyo noorii jaalatahee | እግዚአብሄር ኖር ይወዳል፤ |
| noori yaa waaqayyohee | እግዚአብሄር ሆይ ኖር፤ |
| Warri waaqayyo hee | የእግዚአብሄር ሰዎች፤ |
| nooriidhaan bulahee | እንግዳን መቀበል ልማዳቸው ነው፤ |
| ................................ | ........................................ |

ወንዶቹ "እግዚአብሄር ሆይ ኖር" የሚለውን ቃል ግጥም እየከወኑ ባለበት ሰዓት ሴቶቹ ቡና እያፈሉ ነበር፡፡ ቡናው ተፈልቶ፤ እጣኑ እና ሰንደሉ ተጫጭሶ፤ ዳቦው እና ጠላው ከቀራረበ በኋላ እንደገና መመረቅ ተጀመረ፡፡ አባ መልካ መርቀው ዳቦውን ቆረሱና ሁሉም እንዲይዝ ተደረገ፡፡ ዳቦ እና ቆሎ እየበሉ፤ ጠላና ቡና እየጠጡ "ፈጣሪ ሆይ ቆይልን" እያሉ መዘመር ጀመሩ፡፡ ዝማሬው ስርአቱን በመፈጸማቸው ያገኙትን በረከት እና በዓመቱ ደግመው እንደሚመጡ የሚጠቁም ነው፡፡ በረከቱን ይዘውላቸው እንደመጡ የሚያምኑት ደግሞ ማርያም፤ ሚካኤል፤ ገብርኤል እና አቴቴ እንደሆኑ በምሳሌነት ከጠቀስኳቸው የሚከተሉት ስንኞች መረዳት ይቻላል፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
| --- | --- |
| Yaa maariyaam loon galanii hoo | ማርያም ሆይ ከብቶቻችን ገቡልን፤ |
| Situ haadha caffeeti, sireeti | አንቺ ነሽ ባለ ቁጤማ፤ |
| Siif haa horan loon | ከብቶች ይርቡልሽ፤ |
| Situ haadha bakkeeti | የማስማርያቸው ቦታ ባለቤት አንቺ ነሽና፤ |
| ................................ | ............................................ |
| Mikaayela of na ga'ee | ሚካኤል ራሴን አስቻለኝ፤ |
| Mikaayela jaadaa of na ga'ee | ታላቁ ሚካኤል ራሴን አስቻለኝ፤ |

| | |
|---|---|
| Safaareeffa fuulee of na ga'ee | ለሰውና ለከብት ያስባል፣ |
| Mikaa'elli duulee nubira ga'ee | ሚካኤል ዘምቶ ደረሰልን፣ |
| Safaareeffa fuulee of na ga'ee | ገደሉን እየሞላ ደረሰልን፣ |
| ........................................ | ..................................... |
| Ya gabri'eela abbaa nafsee hoo | ገብርኤል የነፍስ አባታችን፣ |
| Yoom dhuftee geese hoo | ከመቼው መጥተህ ደረስክልን፣ |
| Aayyoleen, cirracha mootee | አቴቴ በጠጠር አሸነፈች፣ |
| Cilaaloo moo gaboo biyya oolte | ከጭላሎ ወይስ ከጀቦ ነበርሽ፣ |
| ........................................ | ..................................... |

በምርቃቱ እግዚአብሄር አቤት ይበለን ይላሉ፡፡ የእግዚአብሄር አቤት ማለት ወይም ደግሞ ልመናቸውን መስማት የሚረጋገጠውም በሰላም፣ በዝናብ፣ በበረከት ወዘተ. በመሆኑ እነዚህን ነገሮች እየዘረዘሩ በዚህ መልኩ ይለምናሉ፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
|---|---|
| Mee rabbi nuf haa owwaatu | ፈጣሪ አቤት ይበለን፣ |
| Biyya kenya nagaa naa godhu | ሀገራችንን ሰላም ያድርገው፣ |
| Nagaa dhugaa nuuf haa godhu | ሰላሙንም የእውነት ያድርግልን፣ |
| ........................................... | ........................................... |
| Kan barate ifatti nuu haa ba'u | የተማረ ይሳካለት፣ |
| Kan qotu maasaatti nuuf haa ba'u | አራሽ በማሳው ይሳካለት፣ |
| Biyya keeyya salaami nuuf haa ta'u | ሀገራችንን ሰላም ያድርገው፣ |
| Jaalalli waaqarraa nuuf haa bu'u | ፍቅር ከሰማይ ይውረድልን፣ |
| Malkaaf tulluun tole nuuf haa jedhu | ወንዙ ተራራው እሺ ይበለን፣ |
| Nama malkaatti ba'ee argatu rabbinu | ወንዝ ሄደን የምንለምነው |
| haa godhu | የሚሰማይሁንልን፣ |
| Mee robaan rabbi nu haa qaqqabu | ፈጣሪ በዝናብ ይድረስልን፣ |
| Qabbanaan nu haa ga'u | በጥላ ይድረስልን፣ |
| ..................................... | ........................ |

ምርቃቱ ሲጠናቀቅ ፊታቸውን ወደ ዝቋላ ሀይቅ አዙረው ምርቃት ሲቀበሉ የነበሩት ሁሉ እንደገና ቂጭ አሉ፡፡ በመቀጠልም እግዚአብሄር ሆይ በሰላም ውሎ መግባት ባንተ ነው እና

እንዲህ እናመሰግንሀለን እያሉ ሲዘምሩ መራቂው ዳቦውን መቁረስ ጀመሩ፡፡ ከዛም ከዳቦው እና ከቆሎው መብላት ከቡናው እና ከጠላውም መጠጣት ተጀመረ[13]፡፡

ምግብ እና መጠጡም ሆነ ዝማሬው ሲጠናቀቅ የክብረ በዓሉ መዝጊያ የሆነው ምርቃት ተከወነ፡፡ በዚህ ቃል ግጥም አማካኝነት እግዚአብሄር ሰላምን ይስጠን፣ ልጆቻችንን ይጠብቅልን፣ ሀገራችንን ሰላም ያድርግልን ወዘተ. እያሉ ይመርቃሉ፡፡ ከዋኞቹም ሆኑ ተሳታፊዎች ዝማርያቸው፣ ሙዳቸው[14] እና ምርቃታቸው እንደተሰማላቸው ስለሚያምኑ፣ ምላሽም እንደሚያገኙ እርግጠኛ ስለሆኑ ደስተኛ ሆነዋል በማለት አባገዳ ለገሰ ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005)፡፡

ምግብና መጠጡ እንዲሁም ዝማሬው ሲጠናቀቅ አባገዳው እና አቶ ሶምቤ ቃቻ ተራ በተራ መመረቅ ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ የተካሄደው ምርቃት ቀደም ሲል ከተከወኑት ምርቃቶች ይለያል፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ስንኞች እንመልከት፡-

| **ኦሮምኛ** | **ትርጉም** |
|---|---|
| Gooftaan keenya natti haa dhufan | ፈጣሪያችን ይምጣልን፣ |
| Nuyi hin morru | እኛ አንጠነቁልም፣ |
| Hin fallu | ክፉም አናስብም፣ |
| Wallaquma kadhamna | የምንለምነው ፈጣሪን ነው፣ |
| Dhugaaf dubbanna | የምንናገረው እውነት ነው፣ |
| Gadaatti bulla | የምናድረው በገዳ ነው፤ |
| Gadadoo nu lagi | ከድህነት አውጣን ፤ |
| Jenneti gadaatti bulla | ብለን ነው ከገዳ የምናድረው፣ |
| Nama hin minu aadaa' | ሰውን አንጎዳም፣ |
| namaa hin miinu | የሰውን ባህልም አንጎዳም፣ |
| Safuu namaa hin sukkuumnu | የሰውን እሴት አንረግጥም፣ |
| ................................... | ................................. |

[13] በፊት ከእነዚህ ምግብና መጠጦች በተጨማሪ ከብት ወይም በግ ይታረድ ነበር፣ ውተት፣ ጠጅ፣ ብርዝ ወዘተ. ይኖር ነበር በማለት አባገዳ ለገሰ ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005 ዓ.ም)፡፡

14 ሙዳቸው፡-ሙዳ ማለት ዛፍ ወይም የአምልኮ ስርአት የሚፈጸምበት ድንጋይ (ሲዳ) ቅቤ መቀባት ማለት ነው፡፡

ይህን ቃል ግጥም በክወኑበት ወቅት "የአቡዬ ወንበር"[15] እና "የአርብ እሮብ ዳገት"[16] ወደ ተባሉት ስፍራዎች ሲሄዱ እግረ መንገዳቸውን ቆም በማለት የሚመለከቱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስርአቱን ለማየት የመጡ ሰዎች የሌሎች ሀይማኖት ተከታይ የሆኑ ወጣቶች አንዳንድ ድምጾችን ሲያሰሙ (ሲያጓሩ)፣ ከቀኞቹ ሲመርቁም "ሲያሾፉባቸው" ነበር፡፡



ፎቶ 6. ስርአቱ ሊጠናቀቅ ሲል የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ሲመለከቷቸው የሚያሳይ ምስል

ለዚህ ነው "እኛ አንጠነቁልም"፣ "የምንለምነው ፈጣሪን ነው" ወዘተ. እያሉ የመረቁት፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አባ መልካ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ፡-

> እኛ ወልደን ያሳደግናቸው የገዛ ልጆቻችን ያሾፉብናል፤ ዛፍ ታመልካላችሁ ይሉናል፤ ተራራ ታመልካላችሁ ይሉናል፤ ... እኛ ግን የምናመልከው አንድ እግዚአብሔርን ነው፡፡ እዚህም እዛም ያለው አንድ እግዚአብሔር ነው፡፡ አሁን ከዚህ ስንጨርስ አቦ ታቦት ሄደን እናነግሳለን፡፡ ምርቃቱ ላይ እንደዛ ያልኩት ቢሰሙም ባይሰሙም መናገር ስላለብን ነው፡፡ ...
>
> (ቃለ መጠይቅ፡፡ መጋቢት 5/2005)


15 የአቡዬ ወንበር፡- አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ እረፍት ማድረግ ሲፈልጉ ይቀመጡበት ነበር ተብሎ በኦርቶዶክሶች የሚታመንበት ድንጋይ ነው፡፡

16 የአርብ እሮብ ዳገት፡- በመጠን የተለያዩ ሁለት ድንጋዮች መካከል ሰዎች እንዲያልፉ ይደረጋል፡፡ በሰላም ካለፉ በሚያልፉበት ጊዜ ድንጋዮቹ ካጣበቋቸው አርብ እና እሮብን አይጾሙም ተብሎ ይታመናል፡፡ በሰላም ካለፉ ደግሞ ጿሚ እንደሆኑ ይታሰባል፡፡ አሁን አሁን ግን በዚህ ምክንያት ብዙ ሰዎች ስነ ልቦናቸው እየተጎዳ ስለሆነ ገዳሙ እንደከለከለ እና አንዳንድ ሰዎች ግን በፈቃዳቸው እንሚሄዱ የገዳሙ መጋቢ አባ ይናገራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 5/2005)

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ከዋኞቹ እንዲህ አይነት ቃል ግጥም እንዲከውኑ ያደረጋቸው በጊዜው የተፈጠረው ሁኔታዊ አውድ[17] ነው፡፡ ይህ ምርቃት ሲጠናቀቅ (ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል) የከበራ ስርአቱ ተጠናቀቀ፡፡

እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች የዋቄፈታ ስርዓቱ ሲጠናቀቅ የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ንግስ ስርአትን ለማክበር ወደ አቦ ቤተ ክርስቲያን[18] ይሄዳሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ አቶ ደምሴ ዳዲ እንዲህ በማለት የበለጠ ያጠናክሩታል፡-

> የክርስትና እምነትን ብቻ ተከታይ ከሆኑት ምእመናን ጋር በመሆን ሀይቁን እንዞራለን፡፡ የተወሰኑት ታቦቱ ወደ መቅደስ ሲገባ ወደየቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ ብዙዎቻችን ግን ታቦቱ ወደ መቅደሱ ከገባ በኋላ የቅዳሴ ስርአቱ እስኪጠናቀቅ እንጠብቃለን፡፡ አጠቃላይ ክብረ በአሉ ሲያልቅ ወደ መጣንበት እንመለሳለን፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ፡ መጋቢት 7/2005 ዓ.ም)



ፎቶ 5. አቶ ደምሴ ዳዲ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው የሚያሳይ ምስል

---

[17] ቀደም ብየ ከጠቀስኳቸው በአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ምክንያት ከተከወኑት ቃል ግጥሞች በተጨማሪ እንደሁኔታው የሚፈጥሯቸው እና ለአውዱ እንዲመች አድርገው በማሻሻል የሚከውኗቸው ቃል ግጥሞች ናቸው፡፡

[18] በዚህ ቀን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን እለተ እረፍት ሰበብ አድርጎ የሚካሄድ ትልቅ የንግስ ክብረ በዓል አለ፡፡ በዓሉ የሚከበረው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች በሆነው እና እዛው ከሀይቁ ዳርቻ ከፍ ብሎ በሚገኘው የዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በሀይቁ ውስጥ ለአንድ መቶ ዓመታት ጸልየውበታል ተብሎ ስለሚታሰብ ከረፋዱ ሦስት ሰዓት አካባቢ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታቦት ሀይቁን ዞሮ ወደ መቅደሱ ተመልሶ ይገባል፡፡

## 3.3. ትንታኔ

የዋቄፈታ እምነትን እና የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አዋህደው የሚከተሉት የማህበረሰብ ክፍሎች መጋቢት 5/ 2005 ዓ.ም በከወኑት ክብረ በዓል ላይ ጎልተው የታዩትን የመባያ ጉዳዮች (motifs) ለይቼ በማውጣት በማህበረ ባህላዊ አውድ ውስጥ አስገብቼ ተንትኛለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል የተፈጠረውን የእምነት ውህደት ሰበብ እና አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተንትኜ አቅርቤያለሁ፡፡

### 3.3.1.የመባያ ጉዳዮች

የዋቄፈታ እምነትን እና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን በአንድ ላይ የሚከተሉት የማህበረሰብ አባላት የከበራ ስርአቱን የፈጸሙት የዝቋላ ተራራ ላይ ከሚገኝ ሀይቅ ጎን ባለ ጫካ ውስጥ ነው፡፡ በመጀመርያ እነዚህ ስፍራዎች በማመስገኛም ሆነ በመለመኛ ቦታነት ሊመረጡ የቻሉበትን ምክንያት መርምሬያለሁ፡፡ በቃል ግጥሞቹ ከዋኔ ወቅት የማህበረሰቡ ቀደምት አባቶች ከእነ ጎሳቸው ተደጋግመው ይጠራሉ፤ በክብርም ይወደሳሉ፡፡ እንግዳ መቀበል የማህበረሰቡ ትልቅ እሴት ነው፡፡ ልእለ ተፈጥሮ የተለያዩ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነዚህን ጉዳዮች እንደሚከተለው ተንትኛቸዋለሁ፡፡

#### 3.3.1.1. ፈጣሪን በፍጥረቱ አማካይነት ማመስገን

መጋቢት 5/2005ዓ.ም የተከበረው ይህ ክብረበዓል የተከወነው ዝቋላ ተራራ ላይ ከሚገኘው ዝቋላ ሀይቅ ጎን ባለው ጫካ ውስጥ ነው፡፡ የበዓሉ ከዋኞችና ተሳታፊዎች "እንዲህ እንወጣልሀለን" በማለት ሲዘምሩ ነበር፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
|---|---|
| Raagiyyoohoo akkana yaanaa hee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን እንዲህ እንወጣልሃለን |
| Raagiyyoohoo amma dachaanaahee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን አሁን እንመለሳለን፣ |
| Raagiyyoohoo cuqqala gumaahee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን ጨቃላ ያንተ ፍሬ ነው፣ |
| ................................ | ................................ |

ከዋኞቹ እግዚአብሄርን "እንዲህ እንወጣልሃለን" የሚሉት ዝቋላ ተራራ አናት ላይ ባሉት ዛፎች ውስጥ ሆነው ነው፡፡ ከዛፎቹ በቅርብ ርቀት የዝቋላ ሀይቅ ይገኛል፡፡ "እንዲህ" የሚለውን ቃል ከስፍራ አንጻር ስንመረምር ተራራ፣ ዛፍ እና ሀይቅን እናገኛለን፡፡ አማኞቹ

'ጩቃላ ያንተ ፍሬ ነው" በማለት ተራራውን እሱ እንደፈጠረው ይገልጻሉ፡፡ ሲመርቁም ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሄር እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ህይወታቸው ምቹ እንዲሆን ፍጥረታትን ሁሉ ስለሰጣቸው ያመሰግናሉ፡፡ ማመስገን ብቻ ሳይሆን መጪው ጊዜም ጥሩ እንዲሆንላቸው መለመን ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በእጅ ስለማይጨበጥ እና ስለማይዳሰስ ተጨባጭ በሆኑት ፍጥረታቱ አማካኝነት ያመሰግኑታል፡፡

በዋቄፈታ እምነት መሰረት በምድር ላይ ካሉ ፍጥረታት መካከል ተራራ፣ ዛፍና ወንዝ (ሀይቅ) ተለይተው ለክበራ የተመረጡበት ምክንያት አንድም ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጋር ይገናኛል፡፡ አንድም ደግሞ ከማህበረሰቡ የቀደመ ያኗኗር ዘይቤ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እነዚህን አንድምታዎች የበለጠ ግልጽ የሚደርጉልን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገሩት ሚቶች እና አፈታሪኮች ናቸው፡፡ በመጀመሪያ አቶ ጫላ ሶሪ የተረኩልኝ ይህንን ነው፡፡

> እግዚአብሔር የሰውን ልጅ መፍጠር ባሰበ ጊዜ አንዱን ዛፍ ለሁለት ከከፈለው በኋላ አንደኛውን ክፋይ ወንድ ሌላኛውን ክፋይ ደግሞ ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች ዘጠኝ ልጆች ወለዱ፡፡ ዘጠኙ ፍጥረታት የተቀደሱ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በቦረና አካባቢ ዘጠኙን ሰዎች የሚወክሉ ዘጠኝ ሀይቆች አሉ፡፡ ከእነዚህ ዘጠኝ ሀይቆች መካከል አንዱ ዝቋላ ሀይቅ ነው፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ፣ 7/2005ዓ.ም፡፡)

በሌላ በኩል ደግሞ የመጀመርያው ሰው "ሆሮ" እንደሚባል እና ከተራራ አናት እንደወጣ የሚናገሩት አባገዳ ለገሰ ናቸው፡፡

> እግዚአብሔር ሆሮን ከተራራ አናት ላይ ፈንቅሎ እንዲወጣ በማድረግ የመጀመርያው የሰው ፍጥረት አደረገው፡፡ ሆሮ ተራራ ላይ እየኖረ እያለ ውሃ መጠጣት ስለፈለገ ወደ ወንዝ ወረደ፡፡ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰማና ወደ ኋላው ዞር ሲል ከእግዚአብሔር ዐይን ጋር ተጋጨ፡፡ ዐይኑ ሲጋጭ ለኹለት ተከፈለና አንዱ አካል ወንድ ሌላው አካል ደግሞ ሴት ሆነ፡፡ ኹለቱ የመጀመርያ ፍጥረታት ስለተፈራሩ አንዳቸው ከሌላቸው ሸሹ፡፡ ወንዱ ከወንዝ ወዲህ ሴቷም ከወንዝ ማዶ ሆነው እየኖሩ እያለ ውሃ ለመጠጣት ወደ ወንዙ ሲወርዱ ይተያዩ ነበር፡፡ ቆይቶ ሴቷ ከወንዝ ማዶ ሆና በወገቧ ላይ ሀረግ በማሰር የሀረጉን ጫፍ ላከችለት፡፡ ወንዱም ስቦ ወሰዳት እና ተጋብተው ዘጠኝ ልጆች ወለዱ፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 7/2005ዓ.ም)

ከእነዚህ ሚቶች መረዳት እንደሚቻለው ተራራ፣ ዛፍ እና ወንዝ (ሀይቅ) የሰው ልጅ መፈጠርያ ቦታዎች ስለሆኑ የልእለ ተፈጥሮ ሀይል ተገልጾባቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

የማህበረሰቡ አባላት ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አምልኳቸውን በእነዚህ ስፍራዎች የሚፈጽሙት አሁንም የእግዚአብሄር መንፈስ የሚገለጸው በተራራ፣ በዛፍ እና በወንዝ (ሀይቅ) አካባቢ ነው፤ የሚል እምነት ስላላቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቀዳሚዎቹ በተፈጠሩበት ቦታ ተገኝቶ እነሱን መዘከር ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለልእለ ተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ለቀዳሚዎቹም ያለውን ክብር ለመግለጽ ይረዳዋል፡፡ ለዚህም ነው የማህበረሰቡ አባላት በአማካይ ከሁለት ሰዓት በላይ በእግር መጓዝ የሚጠይቀውን የዝቋላ ተራራ በመውጣት በዓሉን የሚያከበሩት፡፡

የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችን በምንመለከትበት ጊዜ በብሉይ ኪዳን ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እግዚአብሄር በተራራ ላይ ይገለጽላቸው ስለነበር ተራራን እንደ ቅዱስ ቦታ ይቆጥሩታል፡፡ እግዚአብሄር ከአእላፍ ቅዱሳኑ ጋር በመሆን ከሲና ተራራ መጥቶ በፋራን ተራራ እንዳበራላቸው ዘዳግም 33፡2 ይጠቁማል፡፡ የጽዮን ተራራ በሰሜን ወገን በመልካም ስፍራ የቆመ የምድር ሁሉ ደስታ እና የትልቁ ንጉስ ተራራ እንደሆነ መዝ 48፡ 2 ይጠቁማል፡፡ በሀዲስ ኪዳንም ክርስቶስ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ተለያዩ ተራራዎች እየወጣ ህዝቡን ያስተምር እንደነበር ከማቲዎስ 5፡7 እና ከሉቃስ 6፡17 መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህም መሰረት ሁለቱንም እምነቶች በአንድ ላይ የሚከተሉ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ተራራን ለአምልኮ ስፍራነት እንዲመርጡ ያደረጋቸው ምክንያት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የልእለ ተፈጥሮ መንፈስ የሚገለጽበት ስፍራ በመሆኑ ነው፡፡

የማህበረሰቡ አባላት በአካባቢው ካሉ ተራሮች መካከል ዝቋላ ተራራን ለአምልኮ እንዲመርጥ ያደርገው ተጨማሪ ምክንያት ስፍራው የነብያቸው (ነቤ) መቃብር እንደሆነ ማመናቸው ነው፡፡ ነቤ አዋሽ ወንዝ የመነጨበት አካባቢ ሲኖር መላእክት ሊገድሉት ይፈልጋሉ፡፡ ለመግደል ያነሳሳቸው ደግሞ ነቤ ከብት እያረደ በግንባሩ ላይ ደም መቀባቱ ነው፡፡ መላእክቱ ነቤን ለመግደል ከእግዚአብሄር ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን ፊጣሪ ከብት አርዶ ደም ተቀብቶ እያለ ግን እንዳይገድሉት አስጠንቅቋቸው ነበር፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ሊገድሉት ፈልገው በመጨረሻ ተሳክቶላቸው ሊገድሉት ሲሞክሩ ስላያቸው በቅሎው ላይ ወጥቶ በፍጥነት መሄድ ጀመረ፡፡ እነሱም ተከተሉት፡፡ አዋሽ ከመነጨበት ተነስቶ ሶዶ መሀከል ሆረ ጅጅጋ ሲደርስ በቅሎው ስለደከመችበት ወንጂ አካባቢ በቅሎውን ሳር አብልቶ ውሃም አጠጥቶ አረፍ አለ፡፡ ጉዞውን ቀጥሎ ቦሰገሪ ሲደርስ በቅሎው በድጋሚ ደከመች፣ ጊዜውም መሸ፡፡ በዚህ ጊዜ መላእክቱ ደርሰውበት ቀጥቅጠው ከገደሉት በኋላ ሬሳውን

ተሸክመው መጀመርያ ወደ አገኙበት ቦታ ወስደው ለመቅበር እየሄዱ እያለ ዝቋላ ሲደርሱ ደከማቸው እና ዝቋላ ቀበሩት፡፡ ቀብረውት ሲመለሱ መቃብሩ ፈንድቶ የዝቋላ ተራራ፣ ሲዳ እና ዝቋላን ጨምሮ ስድስቱ ሆራዎች (ሀይቆች) ተፈጠሩ፡፡ በዚህም የተነሳ ዝቋላ ተራራ ላይ ይገኝ በነበረው ሲዳ ላይ ሙዳ እንደሚደረግ እና በሀይቁ ዳርቻም የእሬቻ ስርአት እንደሚፈጸም አባገዳ ለገሰ ነገዎ ይናገራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005ዓ.ም)

ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት ያደረኩላቸው የማህበረሰቡ አባላት ቀዳሚዎቻቸው በተራራ፣ ዛፍ እና ወንዝ (ሀይቅ) ላይ እንደተፈጠሩ ቢናገሩም ቦታዎቹን ግልጽ አድርገው አይተርኩም፡፡ ነቤ ግን ዝቋላ ተራራ ላይ እንደተቀበረና መቃብሩ ፈንድቶ የዝቋላ ተራራ እና ሀይቅ እንደተፈጠረ ይተርካሉ፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ፈጣሪን በፍጥረቱ አማካይነት ለማመስገን ሲያስብ ይህ ተረክ እምነቱን የበለጠ ያጸናለታል፡፡



ፎቶ 6. መጋቢት 5/2005 ዓ.ም በተከበረው ስርአት ላይ የሙዳ ስርአት የተፈጸመበት ኦዳ

በእነዚህ ስፍራዎች የአምልኮ ስርአት የመፈጸም ምክንያት ከመፈጠርያ ቦታነት ባሻገር ከማህበረሰቡ የቀደመ የአኗኗር ዘይቤ ጋር ይያያዛል፡፡ በዚህ ምእራፍ መጀመርያ ላይ እንደጠቀስኩት ማህበረሰቡ በአርብቶ አደርነት ይተዳደር ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ከብቶች የሚበሉት ሳር ሲደርቅ የነበሩበትን አካባቢ በመልቀቅ ወደ እርጥብ ሳር እና ወንዝ

ወደሚገኝበት ሌላ ስፍራ ይሄዳሉ፡፡ ያም አካባቢ ሲደርቅ እንዲሁ ወደ ሌላ እየተዘዋወሩ መኖር የአርብቶ አደርነት ህይወት መገለጫ ነው፡፡

ይህን የአኗኗር ዘይቤ ስንመረምር ማህበረሰቡ ከወንዝ እና ከዛፍ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከብቶቻቸው ብቻ ሳይሆን ሰዎቹ የሚጠጡት፣ ምግባቸውን የሚያዘጋጁት፣ ንጽህናቸውን የሚጠብቁት ወዘተ. ከወንዝ ወይም ደግሞ ከሀይቅ ውሃ ነው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት በእንቅስቃሴያቸው ወቅትም ሆነ ለተወሰነ ጊዜ ተረጋግተው በሚኖሩበት ወቅት ከፀሐይ እና ከዝናብ የሚጠለሉት ዛፍ ስር ነው፡፡ ሲደክማቸው የመያርፉት፣ ከብቶቻቸውን አሰማርተው የሚቀመጡት፣ ሰው ቢጣላ የሚያስታርቁት ዛፍ ስር ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ እንደ ውሃማ አካላቱ ሁሉ ዛፍም የህልውናቸው መሰረት መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በሰዎቹ ላይም ሆነ በከብቶቻቸው ላይ ጥቃት የሚሰነዝሩ አካላት ቢኖሩ የሚከላከሉበት ጠንካራ መኖርያ ቤት እና አጥር ግቢ የላቸውም፡፡ ተራራው ከፍታ ቦታ ስለሆነ ጠላት ገና ከሩቅ ሲመጣ ተመልክቶ ለመከላከል እና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ይመቻል፡፡ በዚህ ምክንያት ወደ ተራራ በመውጣት ጊዜያዊ ጎጆቸውን ይቀልሳሉ፤ በዛም ይኖራሉ፡፡

በሌላ በኩል በእነዚህ ስፍራዎች የልእለ ተፈጥሮ መንፈስ እንደሚገለጽ ማመናቸው ይህን የአኗኗር ዘይቤ እንዲፈጥሩ ያደረጋቸው ይመስለኛል፡፡ የአምላክን ጥበቃ እና እርዳታ በቅርበት ስለሚያገኙ ጠላት ቢመጣ እንኳን ከጎናቸው ልእለ ተፈጥሮ ስላለ በቀላሉ ለመመከት ባስ ካለ ደግሞ ለማጥቃት ይችላሉ፡፡ የማሸነፍ ብቃቱ ሊመጣ የሚችለው እኛ ብቻችንን አይደለንም ከሚል ስሜት ነው፡፡ ከመሀከላቸው የሚጣሉ ሰዎች ቢኖሩ የፍትህ ስርአቱ አሁንም በልእለ ተፈጥሮ እርዳታ ይከናወናል፡፡ የእርቅ ስርአቱ ዛፍ ስር "የፈራጁን ፍርድ አቅና" (Murteessa murti qajeelchi) ተብሎ ከተመረቀ በኋላ ስለሚከናወን ፍርድ አይዛባም፡፡ ባለጉዳዮቹም ፍርድ ተዛባብኝ ብለው አያጉረመርሙም፡፡

ሦስቱንም የአምልኮ ስፍራዎች በተመለከተ የተገለጹት ሚቶች እና የማህበረሰቡ የቀደመ የአኗኗር ዘይቤ ለስፍራዎቹ የተለየ ክብር እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል፡፡ በፈጣርያቸው እና በቀዳሚዎቻቸው አማካኝነት በእነዚህ ስፍራዎች የአምልኮ ስርአት በመፈጸማቸውም በልእለ ተፈጥሮው ተሰሚ እንደሚሆኑ እና አፋጣኝ ምላሽ እንደሚያስገኝላቸው ጽኑ እምነት አላቸው፡፡ በእለቱ ከዋኞቹ ይህንን እምነት በመያዝ ስርአቱን ከመፈጸማቸው በፊት ስለ

ዎች እና ስለ ክብቶች ብቻ መርቀው አልተለያዩም፡፡ የማመስገኛ ቦታዎቹ ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ በማለት እንዲህ ሲሉ መርቀዋል፡-

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
|---|---|
| Malkaa fitisa godhi | ወንዙን ተጠሮቶ የሚያረካ፣ |
| Elaa bakkeen kun ulfaataadha iddoo itti | ይህ ቦታ የተከበረ ነውና |
| Aadaa guddifatan | ባህላችንን የምናሳድግበት፣ |
| Biyya fardi itti garmaamu | ፈረስ የምንጋልብበት፣ |
| Biyya itti muudan | ሹመት የምንሾምበት፣ |
| Biyya dadhaa nuuf haa ta'u | የተመቸ ሀገር ይሁንልን፣ |
| ………………………………. | ………………………… |

ይህ ቦታ…" የሚለው አገላለጽ ሦስቱንም የማመስገኛ ስፍራዎች የሚመለከት ነው፡፡ ማመስገኛ ቦታዎቹ ባህላቸውን የሚያሳድጉባቸው እንዲሆኑላቸው ሲመርቁ ከእምነት ጋር ብቻ ተያይዞ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ስፍራዎቹ የአምልኮ ብቻ ሳይሆኑ የገዳ ስርአት (የገዳ ባቶች የሚሾሙት፣ የሚሻሩት፣ ሰው ሲጣላ የሚያስታርቁት ወዘተ.) የሚፈጸምባቸው ናቸው፡፡ የገዳ ስርአቱ ሲከወን አጠቃላዩ ክዋኔ የማህበረሰቡን ቁሳዊ፣ ስነ ቃላዊ፣ ትውን ፐበባዊ እና ሀገረሰባዊ ዳንሶች ጎልተው ይታዩበታል፡፡ ለዚህ ይመስላል "ባህላችንን የምናሳድግበት" ሊሉ የቻሉት፡፡

ማህበረሰቡ አባላት በስፍራዎቹ አምልኮ ሲፈጽሙ እሬቻ ያደርጋሉ፤ ክብት አርደው ይበላሉ፤ ጠጅም ይጠጣሉ፡፡ ይህንን የአምልኮ ስርአት በዚህ መልኩ በመፈጸማቸው ደግሞ ሰላምን እንደሚያገኙ እና ቦታውም እንደሚከብር የሚገልጹት እንዲህ በማለት ነው፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
|---|---|
| Bakkeen kun Bakkee nagaa haa ta'u | ይህ ቦታ የሰላም ይኹን፣ |
| Ammallee kan waliin cooma nyaatee | ጮማ ምንቆርጥበት ይኹን፣ |
| Waliin Daadhii dhugu nu haa godhu | ጠጅ ምንጠጣበት ይኹን፣ |
| Bakkeen kun bakka irreechaa haa taatu | ይህ ቦታ የእሬቻ ቦታ ይኹን፣ |
| Bakkeen kun bakka kabajaa haa taatu | ይህ ቦታ የክብር ይኹን፣ |
| ………………………………. | ………………………… |

ሌላ በኩል ከዋኖቹ ይህን ቃል ግጥም ሊከውኑ የቻሉት ካለው ሁኔታዊ አውድ በመነሳት ው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሁኔታ የበለጠ ግልጽ የሚሆነው ቃል ግጥሙ ከምርቃትነት ወደ ርግማንነት ሲለወጥ የተከወነውን ቃል ግጥም በማጤን ነው፡፡

| **ኦሮምኛ** | **ትርጉም** |
|---|---|
| Kan nu ballescu nurraa haa badu | ሊያጠፋን የፈለገ ከኛ ይጥፋ፣ |
| Kan nudhibe haa dhibamn | እኛን ያስቸገረ ይቸገር፣ |
| Kan nu cabse haa cabu | የሚሰብረን ይሰበር፣ |
| Kan siidaa keenya cabse haa cabu | ሲዳችንን የሰበረ ይሰበር፣ |
| Kan aadaa keenya cabse haa cabu | ባህላችንን ያናናቀ ይጥፋ፣ |
| Kan nu miidhe haa miidhamu | የጎዳን ይጎዳ፣ |
| Kan sa'a Keenya miidhe haa miidhamu | ከብቶቻችንን የሚጎዳ ይጎዳ፣ |
| Kan dhugaa keenye irriite haa rivriitu | እውነታችንን የረገጠ ይጥፋ፣ |
| ............................................. | ................................ |

ባህላችንን የሚያጠፉ ይጥፉ" የሚለውም ሆነ ሌሎች ስንኞች ሊከውኑ የቻሉት ሲዳቸው ]መሰበሩ እና ሀይቁ ጋ ሄደው እሬቻ ባለማድረጋቸው የተነሳ እንደሆነ አቦ ሶምቤ ቃቻ ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005)፡፡ ይህ ደግሞ ለማመስገኛ ስፍራዎቹ የላቸውን ግምት የሚያሳይ ነው፡፡ በማመስገኛ ስፍራዎቹ ተገኝተው የሚገለጽላቸውን ልእለ ተፈጥሮ መንፈስ ከማመስገን የሚከለክላቸው እንዲጠፋላቸው ይመኛሉ፡፡

ስንኞቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ክፍል የሚገኘውን የሙሴ ህግ ያስታውሰናል፡፡ ሕይወት በሕይወት፣ ዓይን በዓይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር፣ መቃጠል ]መቃጠል፣ ቁስል በቁስል፣ ግርፋት በግርፋት ይከፈል" (ኦሪት ዘጸአት 21፣ 23-25)፡፡

]ተተኳሪ ቡድን ውይይት ላይ ይህ ሐሳብ ተነስቶ የነበረ ሲሆን ተወያዮቹ ልእለ ተፈጥሮ ጎዳቸውን ሊጎዳላቸው እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ ይህንን የሚሉት ደግሞ ሌሎች ሰዎች እንዲጎዱ ስለሚፈልጉ ሳይሆን የሁሉም እምነት ተከታዮች ሌላው እምነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደር እንደሌለባቸው ስለሚያምኑ እንደሆነ አብራርተዋል (የቡድን ውይይት፣ መጋቢት 8/2005)፡፡

### 3.3.1.2. ቀዳሚዎችን መዘከር

ዚህ ክብረበዓል ወቅት የምርቃት ስርአቱ እንደተጀመረ ከልእለ ተፈጥሮ ቀጥሎ ፀቀዳሚነት የተጠሩት ቀደምት አባቶች ናቸው፡፡ አባቶቹ (ታላላቆቹ) ሲጠሩ የነበረው ደግሞ በጎሳዎቻቸው አማካይነት ነው፡፡

| አሮምኛ | ትርጉም |
| --- | --- |
| Sagaltama Gabraa | ዘጠናው አገልጋዮች፣ |
| Saglan Booranaa | ዘጠኙ ቦራናዎች፣ |
| Torban Baarentummaa | ሰባቱ ባሬንቱዎች፣ |
| ........................... | .................... |

ዐኦሮሞዎች ዘንድ እንደቀዳሚ ከሚታሰቡት የማህበረሰቡ አባላት መካከል አንዱ የሆነው ነው ሦስት ልጆች ነበሩት፡፡ ከእነዚህ ሦስት ልጆች አንዱ ዘጠና[19]፣ ሌላው ዘጠኝ እና የመጨረሻው ሰባት ልጆችን ወለደ ተብሎ እንደሚታመን የማህበረሰቡ አባላት ይተርካሉ[20]፡፡ ነዚህ ቀዳሚዎች ዘጠና፣ ዘጠኙ እና ሰባቱ እየተባሉ በምርቃት ውስጥ የሚጠቀሱት የተለየ ሥራ ስለሠሩ፣ በልእለ ተፈጥሮ ስለተመረጡ ወይም ደግሞ ጻድቃን ስለሆኑ አይደለም፡፡

ይህ የቀደሙ አባቶችን እየጠሩ ልእለ ተፈጥሮን መለመን በክርስትና ሃይማኖት ውስጥም የሚታይ ሲሆን ክርስትናው ከዋቄፈታ እምነት የሚለየው የተመረጡትን እና ጻድቃኑን ለይቶ በመጥራቱ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የአብርሀም አምላክ፣ የይስሀቅ አምላክ፣ የያእቆብ አምላክ፣ ወዘተ. እየተባለ የሚለመነውን እዚህ ጋ ማስታወስ ይቻላል፡፡ ታራም ከአብርሃም (የበፊቱ አብራም) ውጭ ናኮር እና ሐራን የተባሉ ልጆች ነበሩት፡፡ በልእለ ተፈጥሮ

---

[19] ዘጠና፡- የልጆቹ አባት አንዱ ልጁ እንደተወለደ መልኩ እሱን ስላልመሰለ ሚስቱን ከሌላ ወንድ ወልዳዋለች ከባርያ ወልዳዋለች የሚሉም አሉ፡፡) ብሎ ስለጠረጠረ ከቤት አስወጥታ እንድትጥለው አደረገ፡፡ ልጁ የእናቱን ጡት ሳይጠባ ከቤት ውጭ በፀሐይ ላይ ለሦስት ቀናት እያለቀሰ ቆየ፡፡ በሦስተኛው ቀን "ልጁ ሞተ ወይ?" ብሎ ሲጠይቅ እንዳልሞተ ነገር ግን ፀሐዩ ሰውነቱን እንዳጠቆረው እና ያለቀሰበት ድምጹም እንደተዘጋ ነገሩት፡፡ ገና የተወለደ ህጻን ያለ እናቱ ጡት በፀሐይ ላይ ይሄን ያህል መቆየቱ ስለገረመው፣ ሚስቱም ወተቱ ጡቷን እንደያዘው እና ማጥባት እንዳለባት ስለጨቀጨቀችው እንድታስገባው ፈቀደላት፡፡ ይህ ልጅ እያደገ ሲመጣ ከወንድሞቹም ሆነ ከጓደኞቹ የበለጠ ጠንካራ አዳኝ ሆነ፡፡ አንድ ቀን ለአደን ጫካ ሲገባ ዘጠኝ ልጃገረዶች አግኝቶ ሁሉንም ደፈራቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ጫካ ውስጥ የተለያዩ እንስሳትን በማደን እየመገባቸው ሚስቶቹ አደረጋቸውና እያንዳንዱ አስር አስር ልጆች በድምሩ ዘጠና ልጆች እንደወለዱ ወለዱ አባገዳ ለገሰ ይተርካሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005)፡፡

[20] ይተርካሉ፡- መጋቢት 8/2005 ዓ.ም ባካሄድኩት የቡድን ውይይት ወቅት መረጃ ሰጭዎቹ ይህንን ቃላዊ ዝርው ትረክ ነግረውኛል፡፡

ተመረጠው አብርሃም ስለነበረ ከወንድሞቹ ተለይቶ ዘሩ ይጠራል፡፡ አብርሃምም ከይስሀቅ ላ ከባርያው የወለደው እና እስማኤል የተባለ ልጅ ነበረው፡፡ አምላክ ግን አብርሃምን እርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ።" ሎ ይነግረዋል (ዘፍጥ. 11፡26፡፡ ዘፍጥ.17፡19)፡፡

ነዚህ ሁለት ተረኮች ቀደም ብየ የገለጽኩትን ሀሳብ የበለጠ ያጠናክሩታል፡፡ በዋቄፈታ ምነት መሰረት በትዳር ውስጥ መወለድም ሆነ ከትዳር ውጭ መወለድ ዘር እንዳይጠራ ያደርግም፡፡ በምንም መንገድ ቢወለዱ የአምላክ ፍጥረታት ስለሆኑ ብቻ ይዘከራሉ፡፡ ይህ ይሆን ኖሮ ግን በቃል ግጥሙ ውስጥ ካገኘናቸው ሦስት ልጆች መካከል አንዱ ብቻ ተመረጠ፣ እንዲሁም ዘጠና የወለደው (ከትዳር ውጪ የተወለደው) ከነጭራሹ ዘሩ ልተጠቀሰ ነበር፡፡

በዓሉ ከዋኞች በምርቃቱ ወቅት የሚጠሯቸው ጎሳዎች በዓሉን ወደ ሚያከብረው ሀበረሰብ ጎሳ እያጠበቡ ይሄዳሉ፡፡ በዚህም መሰረት "የመጫና ቱለማ ሀገር" በማለት ቀጥላሉ፡፡

| ኦሮምኛ | አማርኛ |
| --- | --- |
| Biyyaa Maccaaf Tuulamaa | የመጫና ቱለማ ሀገር፣ |
| Biyyaa fincaan Tulamaa sadeeni | የሶስቱ የቱለማ ልጆች ሀገር፣ |
| ..................................... | ................................. |
| Yaa waaqa lamaa liiban | የኹለቱ ሊበን አምላክ፣ |
| Yaawaaga shanan giddaa | የአምስቱ ጂዳ አምላክ፣ |
| Biyya biyya nagaa nuuf godhi | ሀገራችንን ሰላም አድርግልን፣ |
| Giddaa biyya nagaa nuuf godhni | ጂዳን ሰላም ሀገር አድርግልን፣ |
| Ada'aa biyya nagaa nuuf godli | አድኣን ሰላም ሀገር አድርግልን፣ |
| Liibaniin nagaaa nuuf godhi | ሊበንን ሰላም አድርግልን፣ |
| Nagaa dhugaa nuuf godlni | ሰላሙንም የእውነት አድርግልን፡፡ |
| ..................................... | ................................. |

ጬጫ እና ቱለማ የራያ ልጆች ሲሆኑ ቱለማ ዳጪ፣ በቾ እና ጂሌ የተባሉ ልጆች ንደነበሩት አባ ሙዳ በየነ ይናገራሉ፡፡ ከእነዚህ ልጆች መካከል አንዱ ከሆነው ዳጪ ተወለደው ገላን ሊበን፣ ጂዳ፣ አድኣ፣ አቡ፣ ወረጃርሶ እና ጋዱላ የተባሉ ልጆች እንደነበሩት መጥቀስ የጎሳዎቹ ስያሜ የመጣው ከዚህ እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡ "የኹለቱ ሊበን አምላክ" ማለት የገለጹትም እንዲሁ የሊበን ልጆች የሆኑትን ቱምኤን እና ኦቦራን ለመጥቀስ ነው፡፡

ደም ኩራ፣ ጋሊይ፣ ከኩ፣ አራበሳ እና ዶዮ የተባሉ ልጆች በመወለዳቸው በምርቃቱ ነጥ "የአምስቱ ጂዳ አምላክ" ተብሎ ሊገለጽ ችሏል (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15 005)፡፡

ይ እንደጠቀስኩት የዘር ሀረጋቸውን እያጠበቡ በሚመጠቡበት ጊዜ እንኳን ሊጠቅሱት ለጉትን (የራሳቸውን) ጎሳ ብቻ ነጥለው እንደማይጠሩ ከዚህ ቃል ግጥም መረዳት ቻላል፡፡ ለዚህም ነው የቱለማን ልጆች ለመጥራት እየፈለጉ ወንድሙን (መጫን) ለተውት፡፡ የቱለማ ልጆችም ሳይነጣጠሉ ሁሉም በአንድ ላይ ይጠራሉ፡፡ በዝርዝር ጥራት ቢበዛባቸው እንኳን ቁጥራቸውን ሳይጠቅሱ እንደማያልፉ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ቃላ ተራራ የሚገኝበት የሊበን ጨቃላ ወረዳ ስለሆነ ነው ዘር ቆጠራው ሊበን ላይ ጠናቀቀው፡፡

ርቃቱ ላይ ከቀደሙ አባቶች በተጨማሪ ነቤ[21] ተቀምጦ የፈረደበት፣ ያስታረቀበት እና ፃላው ያረፈበት ቦታ ነው ተብሎ የሚታመነው ስፍራም ይጠቀሳል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ህ ስፍራ በእጅጉ ይከበራል፡፡

| **ኦሮምኛ** | **ትርጉም** |
|---|---|
| Biyyaa Odaa Nabee | የኦዳ ነቤ ሀገር፣ |
| Biyyaa Odaa shanani | የአምስቱ ኦዳዎች ሀገር፣ |
| Biyyaa Caffee Shanani | የአምስቱ የጨፌ ሀገር፣ |
| Biyyaa Tulluu Shanani | የአምስቱ የቱሉ ሀገር፣ |
| Biyyaa waraana shanani | የአምስቱ የጦር ሀገር፣ |
| Biyyaa Gadaa shanani | የአምስቱ የገዳ ሀገር፣ |
| Waaqa qamaa shananin nu uumte | አምስቱን የስሜት ህዋሳት የፈጠርከ፣ |
| Kan nagaan nubulchitee | በሰላም ያሳደርከን፣ |
| Nagaaan nu olchi | በሰላም አውለን፡፡ |
| ......................... | .................... |

ዎቹ "የኦዳ ነቤ ሀገር" በማለት የገለጹት ነቤ በአምስቱ ኦዳዎች (ዛፎች) ጥላ ስር ለረፈና ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ስላከናወነ ነው፡፡ አምስቱም ዛፎች በአንድ ቦታ ላይ ለፍ አለፍ ብለው የበቀሉ ናቸው፡፡ በቱለማ ኦሮሞ የገዳ ስርአት ውስጥ አምስት ፓርቲዎች" እንዳሉ አቦ ጫላ ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች አንድ ስርአት ለመከወን ወደ ዳ ነቤ ሲሄዱ በጎሳቸው ከተሰየመው ኦዳ ስር ይቀመጣሉ፡፡ ማለትም ከቢርመጂ የመጡት

---

ነቤ፡- በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ነብይ የሚቆጠር ሰው እንደነበረ የማህበረሰቡ አባላት ይገልጻሉ፡፡

ቢርመጂ፣ ከቤልባ የመጡት አዳ ቤልባ፣ ከአልቺሳ የመጡት አዳ አልቺሳ፣ ከሙደና ጣት አዳ ሙደና እንዲሁም ከሮበሌ የመጡት አዳ ሮበሌ ስር ይቀመጣሉ ለመጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005)፡፡

ል ግጥሙ ውስጥ አምስቱ እየተባሉ ተደጋግመው የተጠቀሱት የቱለማ ገዳዎች ርመጂ፣ ቤልባ፣ አልቺሳ፣ ሙደና እና ሮበሌ ናቸው፡፡ "የአምስቱ የጨፌ ሀገር" የተባለው ለምነትን ለመጠቆም ሲሆን የገዳ እና የጦር ሀገሮች እንደሆኑ የሚገልጹት ደግሞ በገዳ አት የፓርቲ አባልነትም ሆነ በጦርነት ጊዜ ቱለማን የሚወክሉ ጎሳዎች መሆናቸውን ሳየት ነው፡፡

ህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው አዳ፣ ጨፌ፣ ቱለማ፣ ጦር እና ገዳ አምስቱ የሚል ቃል ትለው የቀረቡ ሲሆን እነሱን ተከትሎ የመጣው ስንኝ ደግሞ "አምስቱን የስሜት ህዋሳት ጠርክ" ይላል፡፡ ይህ በአጋጣሚ የተፈጠረ ነው ብሎ ማሰብ ከባድ ነው፡፡ ከዋኞቹ ይህን ፡ የቻሉት ለማህበረሰቡ ህልውና አምስቱም ጎሳዎች አምስቱን የስሜት ህዋሳት ያህል ፈላጊ (መሰረታዊ) መሆናቸውን ለማሳየት ነው፡፡ ዛፍ የቀዳሚዎቻቸው መፈጠርያ፣ ሰብሰቢያ፣ ፍትህ መስጫ፣ ማምለኪያ ወዘተ ሆኖ ያገለገለ ነው፡፡ በዚህ ለምለም ቦታ ዳ ስርአት አማካይነት የተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ወኑበታል፡፡ ጠላት ቢመጣ የሚዘምተው ከአምስቱም ጎሳዎች የተውጣጣ ወታደር ነው፡፡

ላ በኩል እንደ አምስቱ የስሜት ህዋስ የተቆጠሩት ቱለማን የወከሉት በየስምንት ዓመቱ ተቀያየሩ ቱለማን የሚያስተዳድሩት አምስቱ ገዳዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም ተጨማሪ አምስት ቁጥር በመጀመርያ የተፈጠሩትን ፍጥረታት ማለትም ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ክብት፣ መሬት እና ውሃማ አካልን እንደሚወክል አቶ ጫላ ሶሪ ያስረዳሉ (ቃለመጠይቅ፣ ጋቢት 15/2005)፡፡

ጅግ ከቀደሙት (በህይወት ከሌሉት) አባቶች በተጨማሪ አሁን በህይወት ያሉት ማግሌዎችም ትልቅ ክብር እንዳላቸው እና ልእለ ተፈጥሮ በእነሱ አማካኝነት አንዳች ከት እንደሚሰጣቸው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ በእነሱ ስር መተዳደርን ይፈልጋሉና "በሽማግሌ ነድረን" በማለት ይጸልያሉ፡፡ በዝማሬያቸውም ሽማግሌ ምንጭ እንዳፈለቀላቸው ገልጻሉ፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
| --- | --- |
| aqatu mala nuuf male | ፈጣሪ ነው ብልሃት ያስተማረን፣ |
| ori yaa waaqayyohee | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| arsatu burqaa baase | ሸማግሌ አፈለቀ፡፡ |
| ........................ | ................................ |

ኀበረሰቡ ባህል መሰረት ውሃ ሊኖርበት ይችላል ተብሎ የሚታሰብ ቦታ ቢኖር ኛውም ሰው ሄዶ አይቆፍርም፡፡ በጣም የተከበሩ፣ በእግዚአብሄር ዘንድ የተወደዱ እና ጢአት የራቁ ናቸው ተብሎ የሚታሰቡ ሽማግሌ ናቸው ውሃ ሊያፈልቁ የሚችሉት ል እምነት አለ፡፡ የተከበሩት ሽማግሌ ውሃ ይገኝበታል ተብሎ የታሰበውን ቦታ ገና ቆፈርያ ነካ ሲያደርጉት ምንጭ እንደሚፈልቅ አቦ ዮዮ ቡታ ያስረዳሉ (ቃለመጠይቅ፣ ጋቢት 8/2005) ፡፡ ይህን ተግባር ሊፈጽሙ የሚችሉት የዋቄፈታ እምነት ተከታይ እና ካባቢው ተወላጅ የሆኑ ሽማግሌዎች ብቻ አይደሉም ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም ነው ዳንድ አ ቶች[22] የዝቋላ ሀይቅን ከግብጽ ሀገር የመጡት እና የክርስትና እምነት ተከታይ ኑት አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ እንዳፈለቁላቸው የሚተርኩት፡፡

## 3.3.1.3. እንግዳን በመቀበል አንዳች በረከት ማግኘት

ጋቢት 5/2005 ዓ.ም የከበራ ስርአት የፈጸሙት የዋቄፈታ እና የኦርቶዶክስ ክርስትና ምነት ተከታዮች በቃል ግጥም ከዋኔያቸው እግዚአብሄር ኖር መባልን እንደሚወድ እና

---

ንዳንድ አባቶች፡- በቃለ መጠይቅም ሆነ በቡድን ውይይት ጊዜ የተሳተፉ አባቶች እንደገለጹልኝ ከሆነ ስለዝቋላ ቅ አፈጣጠር ሁለት አይነት አፈታሪኮች አሉ፡፡ የመጀመርያው የነቢ መቃብር ሲፈነዳ ከተፈጠሩት ሀይቆች ከል አንዱ ነው፤ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አቡነ ገብረመንፈስ አፈለቁት የሚለው ነው፡፡

ነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዝቋላ ተራራ ላይ ሲኖሩ አንድ ሰው ከብቶቹን እያሰማራ እያለ ድንገት አያቸውና ከየት ደመጡ ሲጠይቃቸው ተሰወሩበት፡፡ በወቅቱ አቡየ ጸሎት እያደረጉ ነበር፡፡ ሲሰወሩበት ደንግጦ ወደ ቤቱ ሄድ ሚስቱን አንድ የሚያስፈራ ሰው ተራራ ላይ አለ፤ ቅቤና ወተት ይዘሽለት ሂጂ ብሎ አዘዛት፡፡ ሴትዮዋም ዘዘችውን ይዛላቸው ስትሄድ አንበሳዎችና ነብሮች በዙሪያቸው ኾነው አየች፡፡ ቅቤውንና ወተቱን ለአቡየ ትታ ታች በመውረድ አካባቢው ስለሚያስፈራ ከብቶቻቸውን ነድተው ከቦታው መጥፋት እንዳለባቸው ነገረችው፡፡ ህ ሀሳብ ተስማምተው ወደ ምድረ ከብድ ሄዱ፡፡ በሌላ ጊዜ ሲመለሱ አቡየ የነበሩበት ቦታ ላይ ምንጭ ፈልቆ ኙ፡፡ በፊት ግን በአካባቢው ውሃ ስላልነበረ ውሃ ለማግኘት ብዙ ርቀት ይሄዱ ነበር፡፡ ከዛ ምንጭ ውሃ በቅል ቅዳት ቡና አፍልተው ጠጡ፡፡ እየቆየም እየሰፋ ስለሄደ ሰውየው በመቆፈር ጉርጓዱን አሰፋው እና ሀይቁ ጠረ፤ በማለት አቶ አያኖ መስቀሎ ይተርካሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005)፡፡

ኑም የእግዚአብሄር ሰዎች ስለሆኑ እንግዳ መቀበል ልማዳቸው እንደሆነ እንደሚከተለው ልጻለ፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
| --- | --- |
| Waaqayyo noorii jaalatahee | እግዚአብሄር ኖር ይወዳል፣ |
| Noori yaaa waaqayyohee | እግዚአብሄር ሆይ ኖር፣ |
| Warri waaqayyo hee | የእግዚአብሄር ሰዎች |
| Nooriidhaan bulahee | እንግዳ መቀበል ልማዳቸው ነው፣ |
| .......................... | .......................... |
| Noorii yaa waaqayyohee | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Maalkaa fi Tulluutti baanaan, | ወደ ወንዝ እና ተራራ ሲወጣ |
| Noori beekaa haa | ኖር ያውቃል፣ |
| Noorii yaa waaqayyohee | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| .......................... | .......................... |

ቃል ግጥም የተከወነው አባገዳው፣ ገዳ አባላትና ሽማግሌዎች ከመረቁ እና ዛፉን ቅቤ ቡ (ሙዳ ካደረጉ) በኋላ ነው፡፡ የሙዳ ስርአቱን ከፈጸሙ በኋላ እግዚአብሄር ኖር ባልን እንደሚወድ የሚነግር ዝማሬ በመዘመር የስርአቱን አስፈላጊነት ይገልጻሉ፡፡ ገቡም ሆነ መጠጡ የሚፈሰው (የሚገበረው) ለልእለ ተፈጥሮ ነው፡፡ ልእለ ተፈጥሮ ሚኖረው በሰማይ ስለሆነ እና በአካል ሊያገኙት ስለማይችሉ የመንፈሱ ማደርያ ለሆነው ንጋይ (ሲዳ) ወይም ደግሞ ዛፍ መስዋእት ያቀርባሉ፡፡ መንፈሱም ምግቡን ይመገባል፤ ጠጡንም ይጠጣል ብለው ያምናሉ፡፡

እምነታቸው እንዲጠነክር ወይም ደግሞ ጸንቶ እንዲቀጥል ካደረጉት ምክንያቶች ካከል አንዱ አቶ አያናው መስቀሎ የተረኩልኝ የሚከተለው ሚት ነው ማለት ይቻላል፡፡

> እግዚአብሄር የሆነ ቤት ሄዶ የሚጠጣ ውሃ እንዲሰጡት ይለምናል፡፡ ሰዎቹ ግን ውሃ ለመስጠት ፍቃደኛ ስላልነበሩ እግዚአብሔር ረግሟቸው ይሄዳል፡፡ ሌላ ቤት ሄዶ ሲለምን ሰዎቹ ለእንግዳ እንዴት ውሃ ይሰጣል በማለት ወተት ሰጡት፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሄር የሰጡትን ወተት ጠጥቶ ሲጨርስ ይህንን ቤተሰብ መረቆ ባረከ፡፡ በተጨማሪም ቤተሰቡን ከሰዎች የተለዩ እና የእግዚአብሄር ተወካይ እንዲሆን በማለት አያንቱ (ቃሉ) አደረገው፡፡
>
> (ቃለ መጠይቅ፡፡ መጋቢት 7/2005)

ህ ሚት መረዳት እንደሚቻለው በእንግድነት ሊቀበሉት ያልወደዱትን ሲረግም በሉትን ያስተናገዱትን ይባርካል፡፡ ለእንግዳቸው ወተት መስጠታቸው የማህበረሰቡን ፎኖር ዘይቤ (አርብቶ አደርነት) የሚጠቁም ነው፡፡ በረከቱ የተገኘው ልእለ ተፈጥሮን ንግድነት ከመቀበል እንደሆነ ስለታመነም ነው ይህ ማህበረሰብ ከላይ የጠቀስኩትን ቃል ም ሊከውን የቻለው፡፡

ርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድም በብሉይ ኪዳን አብርሀም ሦስቱ ሥላሴን በእንግድነት ብሎ በማስተናገዱ ምክንያት መባረኩን እዚህ ጋ ማስታወስ ይቻላል፡፡ አብርሀም እና ሳራ ም ካረጁ በኋላ በተለይም ሳራ ፈጽሞ ልጅ ልትወልድ በማትችልበት እድሜ ላይ እያለች ጅ በረከት የተሰጣቸው እንግዳን በመቀበላቸው ነው (ዘፍጥ 18፡ 1-18)፡፡

ከወነው ቃል ግጥም አማካይነት "እግዚአብሄር ኖር ይወዳል"፤ "ኖር እግዚአብሄር" ሉ፡፡ እነሱም የእግዚአብሄር ልጆች ስለሆኑ እንግዳ መቀበል ልማዳቸው እንደሆነ ልጻሉ፤ እንግዳ በመቀበላቸው ያገኙትን በረከትም ይዘረዝራሉ፡፡

ሚዎችን ስለመዘከር ስተንትን ያነሳሁት ማህበረሰቡ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን ንግድነት ስለመቀበሉ የሚናገረው ሚት ይህንን ሀሳብ የበለጠ ያጠናክረዋል፡፡ በዚህም ረት የማህበረሰቡ አባላት አንድን እንግዳ ተቀብለው የሚያስተናግዱት በር አንኳኩቶ መጣ ብቻ አይደለም፡፡ አብሉኝ አጠጡኝ ብሎ ስለጠየቀም አይደለም፡፡ ለአካባቢው ግዳ በመሆኑ ብቻ በክብር ይስተናገዳል፡፡ እንግዳቸውን ወተት ያጠጡታል፤ ቅቤም ቡታል፡፡ በሙዳ ስርአቱ ላይ ወተት የሚያፈሱት፣ ቅቤም የሚቀቡት ለዚህ ነው ፡፡ ለ ተፈጥሮው ወተት የሰጠውን ቤተሰብ ባርኮ አያና (ቃሉ) እንዳደረገው ሁሉ እነዚህም ች አቡየን በእንግድነት በመቀበላቸው (ምንም እንኳን ቢሰወሩባቸው) ውሃ ፈለቀላቸው፣ ማቸውም ቀለለላቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች እንግዳ በመቀበላቸው (ኖር በማለታቸው) ገኙ በረከቶች እንደሆኑ ያምናሉ፡፡

ዓሉ ተሳታፊዎች የሙዳ ስርአቱን በመፈጸማቸው አንዳች በረከት እንደሚያገኙ፣ ርቃታቸው እንደሚደርስላቸው እና ጸሎታቸው እንደሚሰማላቸው ለዚህም ነው የሙዳ ርአቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በሚከወነው በዚህ ዝማሬ እንዲህ የሚሉት፡-

## ኦሮምኛ

Rabbitu nuuf ta'e gooftaakoo hee
Nanni iddootti bule
Hundumtuu nagaa ta'e
Maseena iyyoo fure
Biyyallee nagaa ta'e
..........................

## ትርጉም

ፈጣሪ አምላክ ሆነልን፣
ሰው በቦታው አደረ፣
ኹሉም ሰላም ሆነ፣
የመካኗን ማህጸን ፈታ፣
ሀገሩም ሰላም ሆነ፣
........................

ህበረሰቡ አባላት የሙዳ ስርአቱን ከመፈጸማቸው በፊት ሲመርቁ ፈጣሪ ጸሎታቸውን ዲሰማቸው፣ ሀገር ሰላም እንዲሆን፣ ኹሉም በቦታው እንዲያድር፣ የመካኗ ማህጸን ዲፈታ ወዘተ. ሲለምኑ ነበር፡፡ ለአምላክ መስዋእት ካቀረቡበት ሰአት ጀምሮ ልመናቸው ሽ እንደሚያገኝ ስለሚያምኑ በዚህ ሰአት የለመኑት ሁሉ እንደተሳካ (እንደደረሰላቸው) ገልጽ ዝማሬ አቅርበዋል፡፡

ገዳ ለገሰ እንደሚገልጹት አንዳንዴ ተሳታፊዎች ከዝማሬ አልፈው ወደ ድርጊት ራሉ፡፡ መካን የሆኑ የክብረበዓሉ ተሳታፊዎች ካሉ የሙዳ ስርአቱ እንደተጠናቀቀ ይዘው ወደጫካው ውስጥ በመግባት ጾታዊ ግንኙነት ያደርጋሉ፡፡ በዛው ቅጽበት ሴቶቹ ደሚጸንሱ እና በዓመቱም ልጆቻቸውን እና ስለታቸውን ይዘው እንደሚመጡ አባገዳ ሰ ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ መጋቢት 8/2005 ዓ.ም)፡፡

ጣሪ አምላክ ሆነልን" የሚለው ስንኝ ካከናወኑት ስርአት ጋር የሚቀራኝ ነው፡፡ ፈጣሪ ለም ላይ ያሉትን ነገሮች ኹሉ በተለይም የሰውን ልጅ ፈጥሯል፡፡ ነገር ግን አንዳንዴ ን ከፍጡራኑ ሊያዞር ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ መስዋእት በማቅረብ ከተለመነ ፊቱን መልሳል፡፡ ማለትም ዝናቡ ይዘንባል፤ የመካኗ ማህጸን ይፈታል፤ ሰላም ይሰፍናል፤ ዘተ፡፡ ለዚህም ነው የሙዳ ስርአቱን ከፈጸሙ በኋላ ፈጣሪ አምላክ እንደሆነላቸው ዷጁት፡፡

ሙዳ ስርአቱ በፊት በተካሄደው ምርቃት ወቅት በከዋኞቹም ሆነ በተሳታፊዎች ላይ ማጽኖ ሁኔታ ይታይ የነበረ ሲሆን በዝማሬው ወቅት ግን የደስታ እና እርግጠኛ የመሆን ኔታ ታይቶባቸዋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ስሜት ሊከሰት የቻለው እግዚአብሄርን ኖር ግለታቸው እንደተባረኩ፣ ጸሎትና ልመናቸው እንደተሰማላቸው፣ ጥያቄያቸውም ደተመለሰላቸው እርግጠኛ ስለሆኑ ነው፡፡ የሚከተሉትን ስንኞች ለአብነት ያህል መልከት ይቻላል፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
| --- | --- |
| Noori yaa waaqayyo | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Ulfaa kee ulfaa ta'e | ቅዱሳንህ ተከበሩ፣ |
| Siidaan kee ulfaa ta'ee | የማምለኪያ ሥፍራህም ተከበረ፣ |
| Namni iddootti bule | ሰው በቦታው አደረ፣ |
| Hundumtuu nagaa ta'e | ኹሉም ሰላም ሆነ፣ |
| Maseena iyyoo fure | የመካኗን ማኅፀን ፈታ፣ |
| Biyyallee nagaa ta'e | ሀገሩም ሰላም ሆነ፣ |
| ........................... | ........................... |

ዚአብሄር ኖር መባልን እንደሚወድ በመግለጽ መስዋዕት በማቅረብ ኖር ካሉት በኋላ ወኑት በዚህ ቃል ግጥም እንደገለጹት የለመኑት ሁሉ በዛው ቅጽበት እንደተፈጸመላቸው ኑዋል፡፡ በማመስገኛ ስፍራው የቀደሙ አባቶች ተፈጥረዋል፣ ተሰብስበዋል፣ ፍርድ ተውበታል፣ ነቤ ተቀብሮበታል፣ ከምንም በላይ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት የአምልኮ ኣት ፈጽመውበታል፡፡ ይኽንም በማድረጋቸው ቅን ፍርድ መፍረድ ችለዋል፣ ሀይቁ ቆላቸዋል፣ የለመኑት ሁሉ ተፈጽሞላቸዋል፡፡ የዚህ ዘመን ሰዎችም እነሱ ያደረጉትን ው ስፍራ በእምነት ስለከወኑ ነው "ቅዱሳንህ ተከበሩ"፣ "የማምለኪያ ሥፍራህም ተከበረ" ት፡፡

## 3.3.1.4. የልእለ ተፈጥሮ ገጽታዎች

ካሁን ካቀረብኩት ትንተና መረዳት እንደሚቻለው በዚህ ክዋኔ ላይ ሲገለጽ የምናየው ዚአብሄር እድሜው ሊለካ የማይችል፣ ተራራ፣ ወንዝ (ሀይቅ) እና ዛፍ ላይ በመንፈስ ገለጥ፣ የሰውን ልጅ አንድም በተራራ አናት ላይ የፈጠረ፣ አንድም ደግሞ ዛፍን ሰንጠቅ ወንድና ሴት አድርጎ የሠራ ነው፡፡ የፈጠረውን የማይረሳ፣ የሰውን ልጅ ራበት ቦታ ላይም በሰዎች የሚመለክ፣ አማኞቹ በደል ሲደርስባቸው እነሱን ተክቶ በቀልላቸው (ተመሳሳዩን ቅጣት የሚቀጣ) ወዘተ. ነው፡፡

ል ግጥም ክዋኔው ላይ የታዩት የልእለ ተፈጥሮ ገጽታዎች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ ረ በዓሉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ በተከወነው ቃል ግጥም ውስጥ በተደጋጋሚ ልእለ ጥሮ ይበየናል፣ ችሎታው እና በረከቱ ይዘረዘራል፣ የሚወደው እና የሚጠላውም ለጻል፡፡ የሚከተሉት ስንኞች ይህንን ሀሳብ ግልጽ ያደርጉታል፦

### ኦሮምኛ

Ohoo yaa maree hoo...
Yaa waaqa hunda uumtee
Maree hoo
Waaqa hunda keenya
Maree hoo
..................................
Hayyee waaqi
Waaqa uumaa
Waaqa uumamaa
Waqaa jechuun kan hundaa
Lafa jechuun kan hundaa
..................................

### ትርጉም

አሆ! ዞሮ መጣ ሆ...
ሁሉን የፈጠርህ እግዚአብሄር ሆይ፣
ዞሮ መጣ ሆ....
የሁላችን ፈጣሪ እግዚአብሄር፣
ዞሮ መጣ ሆ....
..................................
አቤቱ ዓምላክ ሆይ፣
ፈጣሪ አምላክ፣
የፍጥረታት ፈጣሪ፣
አምላክ ማለት የሁሉም ነው፣
ምድር ማለት የሁሉም ነው፣
..................................

 መጣ" የሚለው ሀረግ ክብረ በዓሉ በዓመቱ መድረሱን እና እግዚአብሄርም መስዋዕቱን ብሎ ሊባርካቸው፤ እንዲሁም ፊቱን በምህረት ሊያዞርላቸው ዓመት ጠብቆ መምጣቱን ጠቁም ነው፡፡ ቀጥለው የመጡት ስንኞች በበኩላቸው እግዚአብሄር የሁሉ አስገኘ ሆኑ ሁሉም የእሱ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ "የሁሉም" የሚለው ቃል መደጋገምም ሆነ ሉቱ ስንኞች ውስጥ የአምላክ እና የመሬት ቦታ መተካከት ያለምክንያት የመጣ ደለም፡፡ በዚህ አውድ "ምድር" ልእለ ተፈጥሮ የሁሉም እንደሆነ የሚጠቁመውን ሀሳብ ጨባጭ ለማድረግ የመጣ ቃል ነው፡፡ አንድም በመሬት ሁሉም ፍጥረታት ይኖራሉ፡፡ ሬት መኖር የምችለው እኔ ብቻ ነኝ፤ የግሌ ነች፤ ብሎ የሚሞግት ፍጥረት እንደሌለ ልእለ ተፈጥሮም የእኔ ብቻ ነው አይባልም፤ የሁሉም ነው ሲሉ "አምላክ ማለት ሉም ነው" በማለት መርቀዋል፡፡

 የሁሉም የተባለው ፈጣሪ ሁሉን ቻይ እንደሆነ ደግሞ ከሚከተሉት ስንኞች መረዳት ቻላል፡፡

### ኦሮምኛ

Waaqa Gurraachaa garaa garbaa
Waaqayyo mil-lama bobbaasne
Waaqayyoo mil-afur bobbaasne
Bobbaa bobbaasii
Tiksee xinxalaa godhi

### ትርጉም

ሆደ ሰፊው ጥቁር አምላክ፣
እግዚአብሔር ሁለት እግር አሰማራን፣
እግዚአብሔር አራት እግር አሰማራን፣
ያሰማራነውን አሰማራ፡፡
እረኛውን ብልህ አድርገው፣

Hidda dhalaadduu godhi
Malkaa fitisa godhi
Luuxxuu ijabaa godhi
...............................

ስሩን ሳር አድርግላቸው፡፡
ወንዙን ተጠዋቶ የሚያረክ፣
ሊባን አይኑን ጨለማ አርግልን፣
...............................

ዚህ ስንኞች የሁሉም ፈጣሪ ሲባል የነበረው ልእለ ተፈጥሮ ጥቁር እንደሆነ ጽልናል፡፡ "ሆዴ ሰፌው ጥቁር" የሚለው ገለጻ የቆዳውን ቀለም የሚጠቁም ሳይሆን ን ቻይ፣ ርቆ ሰማይ ላይ የሚገኝ እና የማይታይ መሆኑን የሚጠቁም እንደሆነ አቶ ሶሪ ያስረዳሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 15/2005)፡፡

ት እግር" እና "አራት እግር" የተባሉት ዶሮዎች፣ በጎች፣ ፍየሎችና እና ከብቶች ው፡፡ ማህበረሰቡ ከእንስሳቱ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ስላለለውና ኑሮውም የተመሰረተው ሱ ላይ ስለሆነ ነው በቃል ግጥሙ ውስጥ የተጠቀሱት፡፡ የእንስሳቱ ባለቤቶች ግራት ብቻ ጫጩቶችን በጭልፊት፣ ግልገሎችንም በቀበሮ ከመበላት አያስጥላቸውም፡፡ ነ ተፈጥሮው እረኛውን ብልህ ካደረገው ግን በቀላሉ ጥበቃውን ማጠናከር ይችላል፡፡ ዚህም ሆኖ ሌባው ገፍቶ ከመጣ ማየት የማይችል እንዲያደርግላቸው ይለምናሉ፡፡

ረሰቡ ልእለ ተፈጥሮ እያንዳንዱን የህይወት እንቅስቃሴ በጥሩ ሁኔታ ያከናውንላቸው ይጋብዙታል፡፡ መውጣት መግባታቸውንም ይቆጣጠርላቸው ዘንድ ሚከተለው ይማጸኑታል፡፡

**ኦሮምኛ** **ትርጉም**

Tolaa wajiin nu olchi
Hamaan gargar nu olchi
Darbataa Eboo qajelchi
Barataa qubee qajelchi
Murteessa murti qajeelchi
Jireenyaaf fayyaa qajeelchi
...............................

ከቸር ጋር አውለን፣
ከክፉ ለየን፣
ጦር ወርዋሪውን አቅናለት፣
የተማሪውን ፊደል አቅና፣
የፈራጁን ፍርድ አቅና፣
ለኑሮ ጤናን አቅና፣
...............................

ህ ስንኞች በእያንዳንዷ የእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ ልእለ ተፈጥሮ እንዲገባ ጠይቁ ናቸው፡፡

## 3.3.2. የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል

ገን ጨቃላ ወረዳ ዝቋላ አካባቢ በሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች አማካኝነት የተፈጠረው ምነት ውህደት በዋቄፈታ እምነት እና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መካከል ፈጠረ የእምነት ውህደት ነው፡፡ ቀደም ካሉት ንኡሳን ርእሶች መረዳት እንደሚቻለው ውህደት ሊከሰት የቻለው በመጀመሪያ የአምልኮ ስፍራን፣ በመቀጠል ደግሞ የአምልኮ ትን በመጋራታቸው ነው፡፡ ይህ ውህደት ከሚገለጽባቸው ክዋኔዎች መካከል የመስዋእት ራረብ (የሙዳ) ስርአትን እና የልእለ ሰብእና የመላእክት ረድኤትን እንደሚከተለው ርዝር ተንትኜ አቅርቤያለሁ፡፡

### 3.3.2.1. የአምልኮ ስፍራንና እለትን መጋራት

ም ባሉት ንኡሳን ርእሶች እንደተመለከትነው የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች ክዋኔው ካሔደበት ስፍራ ላይ ከ"ረጅም ዓመታት" ጀምሮ የአምልኮ ስርአት ይፈጽሙ ነበር፣ ህይቁ ዳርቻ በመሄድም እሬቻ ያደርጉ ነበር፡፡ ወደ አካባቢው ዘግይተው የተቀላቀሉት ርስትና ሃይማኖት ተከታዮችም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ህይቁን ባርከው ወደ ነት እንደቀየሩት ስለሚያምኑ በጸበልነት ይጠቀሙበታል፡፡

ቄፈታ እምነት ተከታዮቹ በጥቅምት ወር ውስጥ ካሉት ቀናት መካከል በአንዱ ወደ ራው በመውጣት ክረምቱን አሳልፎ ብርሀንን ላሳያቸው አምላክ የምስጋና ስርአት ርቡ ነበር፡፡ በግንቦት ወር ውስጥ ካሉ ቀናት መካከልም እንዲሁ በአንዱ ቀን የበጋው ይ አልፎ ዝናብ ይዘንብላቸው ዘንድ ለመለመን በዚሁ ስፍራ የአምልኮ ስርአት ጽሙ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድርቅ ከተከሰተ፣ ሰላም ከጠፋ፣ ወዘተ. በማንኛውም ት ቢሆን ወደ ተራራው በመውጣት ዛፎቹ ውስጥ እና በህይቁ ዳርቻ በመገኘት ላክን እንደሚማጸኑ አቶ ፍቃዱ አረርቲ ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005)፡፡

ርስትና ሃይማኖት ተከታዮቹ ደግሞ እዛው ተራራው አናት ላይ የአቡነ ገብረመንፈስ ስ ገዳም ስላላቸው ዘወትር ይጸልያሉ፡፡ ጥቅምት 5 አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ወደ ዮጵያ የመጡበት፣ መቶ ዓመት ከጸለዩ በኋላ ከአምላክ ቃል ኪዳን ተቀብለው ከህይቁ ጡበት እና ዝቋላ ተራራ ላይ የተሰራው ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት የተከበረበት እለት ደሆን ይናገራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በየዓመቱ ጥቅምት 5 ከዘወትሩ በተለየ ሁኔታ

ቱን በማውጣት እና "ጸበሉን" (ሀይቁን) በመዞር የንግስ ስርአት ይፈጽማሉ፡፡ መጋቢት ግሞ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ያረፉበት ቀን በመሆኑ ልክ እንደ ጥቅምት 5 ሞቀት እንደሚያከብሩት የገዳሙ አበምኔት አባ ተስፋ ማርያም ደበሳይ ይገልጻሉ (ቃለ ይቅ፣ መጋቢት 5/2005)፡፡

ስትና ሃይማኖት ተከታዮች ወደ አካባቢው ከመጡ በኋላ ግን የክርስትና ሃይማኖትን ከተሉ "ስለተገደዱ" ለሦስት ተከፈሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የቀደመ እምነታቸውን ሳይለቁ ቲያን ሆኑ፡፡ የተወሰኑት ሙሉ በሙሉ ክርስቲያን ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ በዋቄፈታ ታቸው ብቻ ጸኑ፡፡ አብዛኛዎቹ የእምነቱ ተከታዮች ሁለቱንም አጣምረው መከተል መሩና "ሁለቱም ቦታ የሚመሰገነው እና የሚለመነው አንድ እግዚአብሄር ስለሆነ ሁም ጥቅምት 5 እና መጋቢት 5 ብዙ ህዝብ በተራራው ላይ ስለሚገኝ" በማለት ልኮ ቀናቸውን ከክርስቲያኖቹ ጋር አንድ ቀን እንዳደረጉት አባ ገዳ ለገሰ ይናገራሉ መጠይቅ፣ ታህሳስ 23/2005)፡፡ መጋቢት 5 ሁሌም ጾም ላይ ስለሆነ ከብት ማረዱን ተውትም ይገልጻሉ፡፡

ዚህ ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው በመጀመርያ ደረጃ ሁለቱ እምነቶች ሊቀላቀሉ ት የአምልኮ ስፍራን በመጋራታቸው የተነሳ ነው፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ፈታዎቹ የአምልኮ ስፍራ ተራራ፣ ወንዝ (ሀይቅ) እና ዛፍ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የዝቋላ ራ እና ሀይቅ ከነቤ ጋር ተያይዞ የሚነገር ሚት ስላለው ምንም ያህል ተጽዕኖ ረግባቸው በስፍራው ከማምለክ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ ክርስቲያኖቹ በበኩላቸው ስፍራው ው ከ/ዘ በቅዱስ ያሬድ እንዲሁም በ12ኛው ክፍለ ዘመን በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባረከ፣ ስለተገደመ፣ ሀይቁ ወደ "ጸበልነት ስለተቀየረ" ወዘተ. ስለሆነ ስፍራውን መልቀቅ ፈልጉም፡፡

ምክንያት የሁለቱም እምነቶች ተከታይ እንደሆኑ የሚገልጹት አካላት ለረጅም ታት በስፍራዎቹ ላይ በአንድ ቀን ውስጥ በተለያየ ሰዓት የተለያየ አምልኮ ሲፈጽሙ የከበራ ስርአት ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ የተለያየ በማለት ሀሳቤን እንድገልጽ ካስቻሉኝ ዎች መካከል ጥቂቶቹ በጾም ቀን ከብት አርዶ መብላት፣ ወተት መጠጣት፣ ሲዳውን መቀባት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ኹለተኛው ምክንያቴ ደግሞ የከበራ ሰበባቸው ፡ በአንድ በኩል ልእለ ተፈጥሮ ዝናብ እንዲያዘንብ ይማጸናሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ

ኑ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ታቦትን በማንገስ ልእለ ተፈጥሮ ስለ አቡዬ እና መሰል ሳን ብሎ እንዲምራቸው ይጸልያሉ ፡፡

ፄ ፈታ ስርዓትን ሙሉ በሙሉ እየፈጸሙ ስርዓቱ ሲጠናቀቅ ወደ አቡነ ገብረ መንፈስ ስ ንግስ በሚሄዱበት ወቅት የማኅበረሰቡ አባላት (ሁለቱንም እምነቶች አዋህደው ከተሉት) እምነቶቹን አቀላቅለው ይሄዱ እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ የእምነት ነቶቹን ቀላቅሎ በማክበሩ ሂደት ግን ለዋቄፈታ ስርአቶች የበለጠ ትኩረት ይሰጡ ደነበር በቡድን ውይይት ወቅት ከቀረቡ ሐሳቦች ለመረዳት ችያለሁ (የቡድን ውይይት፣ ቢት 8/2005 ዓ.ም)፡፡ በዚህም የተነሳ የዋቄፈታ እምነት የአምልኮ ስርአቱ ጠይቃቸውን የከበራ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ እያሟሉ ነበር የክርስቲያኖቹን ታቦት እመኑ ጋር አንግሰው፣ የራሳቸውን መዝሙር ዘምረው፣ የንግስ ስርአቱ ሲጠናቀቅ ባቸውን በልተው ወደ ቤታቸው ይሄዱ የነበረው፡፡

ሬ በኋላ ግን የአከባበር ስርአታቸው እየተቀየረ መጥቶ በዚህ ዓመት መጋቢት 5/2005 የታየውን አይነት የአምልኮ ስርአት ሊፈጽሙ ችለዋል፡፡ ስርአቱ ሁለቱ እምነቶች ደተዋሀዱ ያሚያሳዩ ገጽታዎች ይታዩበት ነበር፡፡ ይህንን ሐሳብ የበለጠ ግልጽ ያደርገው ስለመስዋእት አቀራረባቸው የሚያስረዳው ቀጣዩ ትንተና ነው፡፡

### 3.3.2.2. **የመስዋዕት አቀራረብ**

ለ ተፈጥሮን ኖር ለማለት በዋናነት የቀረቡት መስዋዕቶች ጠላ እና ቅቤ ናቸው፡፡ በዚህ ት ከበራ ላይ እነዚህ መስዋዕቶች ይቅረቡ እንጂ ቀደም ባለው ጊዜ ወተት እና ጠጅም ደ መስዋዕት ይቀርቡ እንደነበረ እና ጠላ ግን እንዳልነበረ የበዓሉ ተሳታፊዎች ልጻሉ፡፡ ለዛፉ ሙዳ አድርገው ከጨረሱ በኋላ አረፍ በማለት ዝማሬ እያቀረቡ ቡና እና ሲጠጡ፣ ዳቦ እና ቆሎም ሲበሉ የነበረ ቢሆንም ከብት ግን አልታረደም፡፡

ዚህ አይነት ለውጦች ሊመጡ የቻሉት አንድም በአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ሲሆን አንድም ም በሁለቱ እምነቶች ውህደት የተነሳ ነው፤ ማለት ይቻላል፡፡ ቀደም ባሉት ንኡሳን ኖች ደጋግሜ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ማህበረሰቡ የነበረው የአርብቶ አደርነት ኗኗር ዘይቤው ህይወቱ ከወተት፣ ከቅቤ፣ ከማር እና ከስጋ ጋር የተቆራኘ እንዲሆን ርጎት ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዋቄፈታ እምነት ውስጥ ጾም አለመኖሩ እነዚህን ቦች ያለገደብ እንዲጠቀም እና በማንኛውም ወቀት ቢሆን በመስዋዕትነት እንዲያቀርብ

ስችሎት ነበር፡፡ የአኗኗር ዘይቤው ወደ አርሶ አደርነት ሲቀየር ግን ሙሉ በሙሉ ረተዋል ባንልም የጠጁን ቦታ ጠላ፣ የስጋውን ቦታም ዳቦ እና ቆሎ ተክተውት መመልከት ችያለሁ፡፡

እርግጥ ለውጦቹ በአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ብቻ የመጡ አይደሉም፡፡ አባ ገዳ ለገሰ ይህን ዳይ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ "ወተቱ እና ከብቱ እንደድሮው እንደልብ ባይገኝም ለዚህ ን ገዝተንም ቢሆን እናመጣ ነበር፡፡ ግን መጋቢት 5 ሁልጊዜም በፋሲካ ጾም ላይ ለሚውል ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትተነዋል" (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 08/2005)፡፡ በዚህ መት በተካሄደው ከበራ ላይ ከብት አይታረድ እንጂ ዛፉን ቅቤ ቀብተዋል፡፡ ይህ ድርጊት ግሞ ለፋሲካ ጾም መጾም ምክንያት ከሆነው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት አስተምህሮ እጅጉ የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም የበዓሉ ተሳታፊዎች ጾመኛ ከሆኑና በዚህ ወቅት ላስፈላጊ መሆኑን ካመኑ የእግዚአብሄር መንፈስ ማደርያ ነው ተብሎ የሚታመነው ዛፍም የነ መንፈሱ እራሱ ቅቤውን ሊቀበሉት መቻላቸው አጠያያቂ ይሆናል የሚል እምነት ለኝ፡፡

ዋቄፋታ እምነት መሰረት ጾም እንደሌለ የስርአቱ ተሳታፊ የነበሩት የማህበረሰቡ አባላት ናገራሉ፡፡ በተለይ ደግሞ አባገዳ ለገሰ "እግዚአብሄር ጹሙ አላለንም፣ አፋችሁ ባዶ ይሁን ላለንም፡፡ መጾም ማለት ጥሩ ሥራ መሥራት ማለት ነው እንጂ ምግብ አለመብላት ማለት አይደለም" በማለት ሀሳባቸውን ያስረዳሉ፡፡ ይህንን የእምነት ፍልስፍና በመያዝ ለዘመናት ቢቆዩም መጋቢት 5 ጾም ስለሆነ በማለት ከብት አርዶ መብላቱን እና ወተት መጠጣቱን በመተው ዳቦ እና ቆሎ ሲበሉ ጠላ ሲጠጡ ለመመልከት ችያለሁ፡፡

ጾም ወቅት ስጋ አለመብላቱም ሆነ ወተት አለመጠጣቱ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ርስቲያን አስተምህሮ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያኗ የምግቡን አይነት ብቻ ሳይሆን የመመገቢያ ሰዓቱንም ትደነግጋለች፡፡ የዚህ ፎክ ቡድን አባላት ግን የመጀመርያውን የምርቃት ስርአት አጠናቀው "ኖር ዋቀዮ" የሚለውን ዝማሬ ሲያቀርቡ (በግምት ከጠዋቱ 2፡15 ሰዓት አካባቢ ጀምሮ) እየበሉ እና እየጠጡ ነበር፡፡ የከበራ ስርአቱ ከሁለቱ እምነቶች የተውጣጣ እና የተለየ መልክ ያለው ነው፡፡ እዚህ ጋ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ሆነው በጠዋት የሚበሉ የሉም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን አንድ የንግስ ስርአት እየተከበረ እያለ የጾምም ሆነ የፍስክ ምግብ መበላት የለበትም፡፡ በከበራ

ፈደት ውስጥ እያሉ መብላት እና መጠጣቱ ከዋቄፈታ እምነት የተወሰደ ሲሆን ምግብና መጠጡ የጾም መሆኑ ደግሞ ከክርስትና እምነት የተወሰደ ነው፡፡

እነዚህ ከሁለቱም እምነቶች ተውጣጥተው የተወሰዱ የመስዋእት አይነቶች ተዛንቀው በመቅረብ አንድ ልዩ የሆነ ስርዓት መፍጠራቸው ነው ሁለቱ እምነቶች ተዋህደዋል ማለት ያስቻለው፡፡ የሁለቱ እምነቶች የአምልኮ ስፍራ እና እለት መጋራት የፈጠረው ተጽእኖ ውህደቱን ፈጥሮታል ማለት ይቻላል፡፡

## 3.1.1.1. የልእለ ሰብእ እና የመላእክት ረድኤት

የማኅበረሰቡ አባላት ይህን ስርአት እየፈጸሙ እያለ ሲያቀርቡት በነበረው ዝማሬ ውስጥ እንደ ሚካኤልና ገብርኤል ያሉ መላእክት[23]ና ማርያም[24] ከአቴቴ ጋር እየተጠሩ ሲወደሱ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል ገብርኤል እና አቴቴ የሚወደሱባቸውን የሚከተሉትን ስንኞች እንመልከት፡-

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
| --- | --- |
| Ya gabri'eela abbaa nafsee hoo | ገብርኤል የነፍስ አባታችን፣ |
| Yoom dhuftee geese hoo | ከመቼው መጥተህ ደረስክልን፣ |
| Aayyoleen, cirracha mootee | አቴቴ በጠጠር አሸነፈች፣ |
| Cilaaloo moo gaboo biyya oolte | ከጭላሎ ወይስ ከጀቦ ነበርሽ፣ |
| Cuqqaalaa moo gaboo biyya oolte | ከጩቃላ ወይስ ከጀቦ ነበርሽ፣ |
| Hora arsaadee moo gaboo biyya oolte | ሆራ አረሰዲ ወይስ ከጩቄ ነበርሽ፣ |
| Dhaltiin okolee guutee | የወተታችን ማለቢያ ሞላልን፣ |
| Hara Arusii buutee | ወደ አርሲ ሀይቅ ሞልቶ ፈሰሰ፣ |
| ........................... | ................................. |

[23] ስለ ዝቋላ ሀይቅ አፈጣጠር ባቀረብኩበት ንኡስ ርእስ ላይ በዋቄፈታ እምነት ነቢን መላእክት ገድለውታል ተብሎ እንደሚታመን የገለጽኩትን እዚህ ጋ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

[24] በኦሮሞ ዘንድ ኹለት ማርያሞች አሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ እግዚአብሄር ሁለት ማርያሞችን በብረት መዝጊያ የተሠራ ክፍል ውስጥ አስቀመጣቸው እና እኔ መጥቼ እስከ ምከፍትላችሁ ድረስ ከዚህ እንዳትንቀሳቀሱ ብሎ ቆልፎባቸው ሄደ፡፡ ትንሽ ከጠበቁት በኋላ አንዷ ማርያም ስላልቻለች በሩን በመክፈት ወጥታ ሄደች፡፡ ኹለተኛዋ ግን ቁጭ ብላ እግዚአብሄርን ጠበቀችው፡፡ እግዚአብሄር ከሄደበት ሲመለስ የወጣችዋን ስላላገኛት ስትመለስ ጠብቆ እንደወጣሽ በዛው በየ ገጠሩ፣ በየ መንደሩ... እየዞርሽ እያሰገድሽ ብይ፣ አላት፡፡ እንደዚህ የተባለችው አሁን አቴቴ የምትባል ሲሆን የሰውን ልጅ የምታንቀሳቅስ እና የምታዘዋውር እሷ ነች፡፡ ቁጭ ብላ የጠበቀችውን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ቁጭ በይ እንዳላት አባገዳ ለገሰ ይተርካሉ (ቃለ መጠይቅ፡፡ መጋቢት 15 /2005)፡፡

ከእነዚህ ስንኞች መረዳት እንደሚቻለው ጸሎታቸው ስለተሰማላቸው በፍጥነት ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ምላሹን ይዘው የመጡት ደግሞ ገብርኤል እና አቴቴ ናቸው፡፡ በክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ መሰረት ገብርኤል[25] በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሄርን ቃል ለመተርጎም እና የሚመጣውን ለመግለጥ (ዳን 8፥15-26፤ 9፥21-27) እንደመጣ በሀዲስ ኪዳን ደግሞ ለዘካርያስ ስለ ዮሀንስ ለማርያም ስለ ክርስቶስ ልደት የምስራችን ቃል ያቀረበ መልአክ ነው (ሉቃስ 1፥11-38)፡፡ መጋቢት 5/2005ዓ.ም በተከበረው በዚህ በዓል ላይ ገብርኤል የነፍስ አባት ተብሎ የተገለጸ ሲሆን በፍጥነቱም የተገረመ ይመስላል፡፡

በዚሁ ቃል ግጥም ውስጥ ማርያም እና ሚካኤልም በረዳትነት ይጠቀሳሉ፡፡ የሚከተሉት ስንኞች ይህንን ሐሳብ የበለጠ ግልጽ ያደርጉታል፡፡

| ኦሮምኛ | ትርጉም |
|---|---|
| Yaa maariyaam loon galani hoo | ማርያም ሆይ ከብቶቸቻን ገቡልን፤ |
| Situ haadha caffeeti, sireeti | አንቺ ነሽ ባለ ቄጠማ፤ |
| Situ haadha bakkeeti | የማስማርያቸው ቦታ ባለቤት አንቺ ነሽና፤ |
| ............................ | ........................... |
| Guraalee gur'uu darsaa | ጥቋቁር ባለ ትልልቅ ግቶች፤ |
| Loon galan hoo yee | ከብቶቻችን ገቡልን፤ |
| Dachaa haadha coomaayee | ጥንድ ባለ ሙማዎች፤ |
| Loon galanihee | ከብቶቻችን ገቡልን፤ |
| Galee waatiyyoo maarsahee | ገብተው ጥጆቻቸውን ከበጧቸው፤ |
| Mikaayela jaadaa of na ga'ee | ታላቁ ሚካኤል ራሴን አስቻለኝ፤ |
| Safaareeffa fuulee of na ga'ee | ለሰውና ለከብት ያስባል፤ |
| Mikaa'elli duulee nubira ga'ee | ሚካኤል ዘምቶ ደረሰልን፤ |
| Safaareeffa fuulee of na ga'ee | ገደሉን እየሞላ ደረሰልን፤ |
| ......................................... | ............................... |

በዋቄፈታ እምነት መሰረት እንደ ገብርኤል እና ሚካኤል ያሉ መላእክት በሰው ልጅ ረዳትነት አይታወቁም፡፡ ቢታወቁም እንኳን ቀደም ብየ በዚህ ምእራፍ የጠቀስኩትንና እንደ ነብይ የሚቆጠረውን "ነቤ"ን "በመግደላቸው" ነው፡፡ በዚህ ፈንታ የእግዚአብሄሔርን ሀሳብ እና መልእክት ወደ ሰው ልጆች የሚያደርሱት ለወንዶች አያንቱዎች (ቃሉዎች)

[25] ገብርኤል የስሙ ትርጓሜ የእግዚአብሄር ሰው ማለት እንደሆነ እና በሰው ምሳሌ ለሰዎች የሚገለጥ መልአክ መሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፣ 240) ያስረዳል፡፡

ናቸው፡፡ ለሴቶች ልመናና ችግር የምትደርሰው ደግሞ አቴቴ[26] ነች፡፡ የዋቄፈታ እምነትን ና የክርስትና ሃይማኖትን አዋህደው በሚከተሉት ማህበረሰቦች ክዋኔ ላይ ግን እነዚህ ሁለት የተራራቁ አካላት በአንድ ላይ የልእለ ተፈጥሮ መልእክተኛ ሆነው መጥተዋል፡፡

የሙዳ ስርአቱም እንደተጠናቀቀ አቴቴ መጥታ የወተት ማለቢያቸውን እንደሞላችላቸው ከመሙላትም አልፎ ወተቱ አርሲ ሀይቅ እንደተቀላቀለ ገልጸዋል፡፡ ይህ ነገር የእምነታቸውን ጽናት ያሳያል፡፡

አቴቴ በተለያዩ የኦሮሞ ግዛቶች እየተዘዋወረች ሴቶች በሰላም እንዲወልዱ፣ ጓዳቸው እንዲሞላ፣ ጤናቸው እንዲስተካከል ወዘተ. ታደርጋለች፡፡ በክዋኔው ወቅት ዝናብ እንዲዘንብ፣ ከብቶች እንዲሰማሩ፣ አገሩ ሰላም እንዲሆን እና ሌሎች ብዙ ችግሮች ተጠቅሰው እንዲፈቱላቸው ልመና አቅርበው ነበር፡፡ ገብርኤልም በፍጥነት እንደደረሰላቸው ገልጸዋል፡፡ የተወገደላቸውን ችግር በዝርዝር አልገለጹም፡፡ ከዛ ይልቅ በፍጥነቱ መደመምን መርጠዋል፡፡ ወደ አቴቴ ስንመጣ ግን የወተታቸውን ማለቢያ ስትሞላ እናያለን፡፡ ወተት ማለብ የሴቶቹ ሚና ነው፡፡ አቴቴ ሴቶቹ ሲያልቡ መጥታ ማለቢያቸውን ትሞላላቸዋለች፡፡

የገብርኤል ፍጥነት የሚገለጽልን የወተቱን ነገር ስንሰማ ነው፡፡ ምክንያቱም ወተቱ ታልቦ ከመሙላቱ በፊት ወቅቱ በጋ እንደመሆኑ መጠን መሬቱ ደረቅ ነው፤ ከብቶች የሚበሉት ሳር የለም፡፡ በዚህ እለት ወደ እግዚአሄር በመጸለያቸው እና የሙዳ ስርአት በመፈጸማቸው ዝናብ ይዘንባል፤ መስኩም አረንጓዴ ይሆናል፤ ከብቶችም ሳሩን በልተው ከውሃውም ጠጥተው ይጠግባሉ፤ ላሞችም ይወልዳሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ወተቱ በማለቢያው ይሞላል፡፡ ይህን ሁሉ ያደረገው ልእለ ተፈጥሮ ቢሆንም ፈቃዱን የፈጸመው ገብርኤል ነው፡፡

ከዋኞቹ "ከመቼው መጥተህ ደረስክልን፣" በማለት ፍጥነቱን ያደነቁት በአንድ ቀን ሳይሆን በወራት ውስጥ ሊፈጸሙ የሚችሉ ተግባራትን በእንዴ እንደፈጸመላቸው ስላመኑ ነው፡፡ ከዚህ ስንኝ አስቀድመው "ገብርኤል የነፍስ አባታችን፣" ብለዋል፡፡ በዋቄፈታ እምነት

[26] አቴቴ፡- በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ሴቶች ምጥ ሲይዛቸው ማርያም ማርያም እየተባለ ማርያም እንደምትለመነው ሁሉ በዋቄፈታ እምነት ምጥ የመጣባት ሴት በሰላም እንድትወልድ አቴቴ ትለመናለች፡፡ ሴቶች ጓዳቸው ሙሉ እንዲሆን የምታደርግ እሷ እንደሆነች ወይዘሮ ሚልክ ደቻሳ ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 8/2005)፡፡

መሰረት የነፍስ አባት የለም፡፡ የተጣላ ካለ አያንቲ[27] ዘንድ በመሄድ ይታረቃል፡፡ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ የነፍስ አባት የንስሀ አባት እየተባለም ይጠራል፡፡ ከነፍስ አባት የሚደበቅ ነገር ስለሌለ በስጋም በመንፈስም የደከሙበትን እና ያጋጠማቸውን ችግር ይናገራሉ፡፡ ሀጢአታቸው ይሰረይላቸው ዘንድ የተለያዩ (የጾም፣ የገንዘብ፣ የምጽዋት…) መስዋእት እንዲያቀርቡ ይታዘዛሉ፡፡ ይህን ከፈጸሙ በኋላ ችግራቸው እንደሚፈታላቸው ያምናሉ በማለት የዝቋላ ገዳም አበምኔት አባ ተስፋ ማርያም ደበሳይ ይናገራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ መጋቢት 5/2005)፡፡

መጋቢት 5/2005 ዓ.ም የከበራ ስርአት በፈጸሙት እነዚህ አማኞች የነፍስ አባት ተብሎ የተገለጸው ግን ሰው ሳይሆን መልአኩ ገብርኤል ነው፡፡ የነፍስ አባታቸው አላሳፈራቸውም ከልእለ ተፈጥሮ ዘንድ በረከትን ይዞላቸው መጣ፡፡ ሚካኤልም "ለሰውና ለከብት ስለሚያስብ" እራሳቸውን እንዳስቻላቸው አመኑ፡፡ ራስን መቻል የተገለጸው ከሚታለቡ እና ከባለጮማ ከብቶች ቀጥሎ ነው፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከብቶቹ ለዚህ የሚበቁት ዝናብ ዘንቦ መስኩ ለምለም ከሆነ በኋላ ነው፡፡ የለምለሙ መስክ ባለቤት ደግሞ ማርያም እንደሆነች ይገልጻሉ፡፡ በማርያም ፈቃድ ከብቶቹ ከሳሩ ከበሉ በኋላ በመወፈራቸው እና በመውለዳቸው የሌላ ሰው ጥገኛ ስለማይሆኑ ሚካኤል ራሳቸውን እንዳስቻላቸው ያምናሉ፡፡

በክዋኔው ላይ የተጠቀሱት መላእክት በዋቄፈታ እምነት መሰረት የእግዚአብሄርን መልእክት ይዘው በማምጣት አይፈጽሙም፡፡ መልእክቱን ሊያመጡ የሚችሉት ነቤ፣ ቃሉ እና አቴቴ ናቸው፡፡ በአንጻሩ በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ዳሩ ግን መልእክቱን ይዘው የሚመጡት እንደዚህ አይነት መስዋእት በማቅረብ ሳይሆን በጾም እና በጸሎት እግዚአብሔርን በመለመን ነው፡፡

---

[27] አያንቲ ሰው ተቸግሮ እነሱ ጋ ሲሄድ መንፈስ የገለጸላቸውን ለችግረኛው ይነግራሉ፡፡ የተጣላ ያስታርቃሉ፣ የሰረቀ ሰው አያንቲዎች ዘንድ ሄዶ አይክድም፡፡ ሲታረቁም በውሸት ወይም ደግሞ አስመስለው ሳይሆን እውነቱን አውጥተው ከልባቸው ይታረቃሉ፡፡ በማንኛውም ሰዎች ተጣልተው አንዱ ሌላውን በሀይል ሊደበድበው እንዲሁም ሊገድለው ቢያስብ እንኳን የአያንቲውን ስም ጠርቶ አትንካኝ ካለው ከቁጣው ረገብ በማለት ይተዋል፡፡ ተለምኖ እያለ እምቢ በማለት ከተደባደበ ወይም ከገደለ አያንቲው መንፈስ ስለሚነግረው እሱ ጋ እንዲሄድ ይጠራዋል፡፡ አስፈላጊው ቅጣትም ይፈጸምበታል፡፡

## ምእራፍ አራት

### 4. ማጠቃለያ

መጋቢት 5/2005 ዓ.ም የዋቄፈታ እምነትን እና የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖትን በአንድ ላይ የሚከተሉት የማህበረሰብ ክፍሎች ስርአት የፈጸሙት ልእለ ተፈጥሮ የበልግ ዝናብ እንዲሰጣቸው ለመማጸን ነው፡፡ የቃልግጥም ክዋኔን በመጠቀም በእጃቸው ሊዳስሱት ያልቻሉትን ልእለ ተፈጥሮ እንደ ተራራ፣ ኦዳ እና ሀይቅ (ወንዝ) ባሉ ፍጡሮቹ ላይ አድሮ መስዋእታቸውን እንደሚቀበል እና ወድያውኑ ለልመናቸው መልስ እንደሚሰጥ ይገልጻሉ፡፡ ይህን እምነታቸውን ጸንቶ እንዲቀጥል የሚያደርጉት ደግሞ በሚተርኳቸው ቃላዊ ዝርው ታሪኮቻቸው አማካይነት ነው፡፡

ኹለቱን እምነቶች አዋህደው የሚከተሉት የማህበረሰብ ክፍሎች ሁለቱም እምነቶች በሚጋሩት የአምልኮ ስፍራ ተገኝተው ከሁለቱም እምነቶች ተውጣጥቶ በተገኘ ልዩ ስርዓት ልእለ ተፈጥሮን ተማጽነዋል፡፡ ልእለ ተፈጥሮውም ከሁለቱ እምነቶች በተውጣጡ መልእክተኞቹ አማካይነት ምላሹን ሰጥቷቸዋል፡፡

የሁሉ ፈጣሪ፣ እድሜው የማይቆጠር እና ሁሉን ማድረግ የሚችል እንደሆነ የሚገልጹት ልእለ ተፈጥሮ አንድ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ይህን አንድ ልእለ ተፈጥሮ በቤተ ክርስቲያን በጾም እና በጸሎትም ሆነ በዛፍ ስር ሙዳ በማድረግ ሊማጸኑት ይችላሉ፡፡ በመስዋእቱ አይነት እና አቀራረብ መካከል ያለው ልዩነት ልእለ ተፈጥሮው መስዋእቱን ከመቀበል አያግደውም፤ ወይም ደግሞ ምላሽ እንዳይሰጥ አያደርገውም፣ የሚል እምነት እንዳላቸው ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ይህንን እምነታቸውን በግልጽ የሚያሳየው ደግሞ የልእለ ተፈጥሮው ምላሽ ለማኅበረሰቡ የሚደርስበት መንገድ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ነው ሁለቱንም እምነቶች የሚከተሉት የማኅበረሰብ ክፍሎች ለተማጽኗቸው ምላሽ የሚያገኙት ከሁለቱም እምነቶች በተውጣጡት መላእክት፣ ማርያም እና አቴቴ አማካይነት የሆነው ፡፡

በመጨረሻም በዋቄፈታ እምነት እና በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሃይማኖት መካከል ያለውን የእምነት ውህደት ከዚህ በተሻለ በማኅበረሰቡ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ አብሮ በመቆየት፣ ቋንቋውን እና ባህሉን ይበልጥ በመረዳት እና በመተንተን የማኅበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምልአት መረዳት ይቻላል፤ የሚል እምነት አለኝ፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


መሶብ ወረቅ ቅጣው፡፡ "የገና ክብረ በዓል በላሊበላ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 1997 ዓ.ም፡፡

ሙሉቀን ዘውዱ፡፡ "በባህርዳር አካባቢ ወንዞች ዳር የሚፈጸሙ የአምልኮ ስርአቶችና ክዋኔያቸው፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 2001 ዓ.ም፡፡

ሙሉጌታ ነጋሳ፡፡ "በአደአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴርጉማ ከግጭት አፈታት አንጻር፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 1997 ዓ.ም፡፡

ማሞ ተፈራ፡፡ "በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ የአምልኮ ስርአቶች በዳንግላ ወረዳ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 2002 ዓ.ም፡፡

ምንዳ ገብሬ፡፡ "የጌዲዮ ልማዳዊ ስርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ሰለሞን ደርቤ፡፡ "የዝቋላ አቦ ክብረ በአል አከባበር፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ብጹእ አቡነ ገሪማ (ዶ/ር) እና ሌሎች፡፡ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም</u>፣ አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤት አልተጠቀሰም)፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1961ዓ.ም፡፡

ታደሰ አይችለህም፡፡ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ስርአት እና የገዳማውያን የእለት ከእለት ህይወት ከትእምርታዊነቱ አንጻር፡- በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ኃይማኖት ገዳማት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 1999ዓ.ም፡፡

ኃሮ ቢያንሳ፡፡ ኦሮሚያ፣ የኦሮሞ ህዝብ ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1985 ዓ.ም፡፡

ዘላለም ቻላቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኦረቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እና እምነት አጭር ዳሰሳ፡፡ አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤት አልተጠቀሰም) 2001 ዓ.ም፡፡

ዳንኤል ክብረት፡፡ የቤተክርስቲያን መረጃዎች፡፡ አዲስ አበባ፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፡ 1999 ዓ.ም፡፡

ጌታቸው ኃይሌ፡፡ የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፣ ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ፡፡ ሚኒሶታ፣ (ማተሚያ ቤት አልተጠቀሰም)፣ 1995ዓ.ም፡፡

ግርማ ቡኬ፡፡ "የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር እና እምነት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ 2003 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማትሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡ ባናዊ ማትሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም፡፡

Barnard, Alan and Jonathan Spencer (eds). Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology. New York: Routledge, 2002 (3rd edition).

Bauman, Richard. "The field study of folklore in context," In A Handbook of American Folklore. Dorson, Richard. (ed), Bloomington: Indiana University Press, 1983, pp. 362-67.

Bell, Cathrine. Ritual Perspectives and Dimenssions. New York: Oxford University Press, 1997.

Dorson, Richard. (Ed). Folklore and Folklife: an Introduction. Chicago: Chicago Uninersity press, 1972.

Ernest Suttner. "The Value to Missiology and Ecumenism of Studies of the Semitic - African Christian Culture of Ethiopia," In "Journal of the Capuchin Franciscan Institute of Philosophy and Theology." Addis Ababa, 1993, Vol. iii:2, pp. 1-16.

Finnegan, Ruth. Oral Traditions and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices. New York: Routledge, 1992.

Goldstein, Kenneth. A Guide For Field Workers in Folklore. London: Folklore Associates, Inc., 1964.

Leopold, Anita and Jeppe, Sinding (eds). Syncretism in Religion: a Reader. New York: Routledge, 2004.

Lopez, Mellie. A Handbook of Philipine Folklore. Quezon: University of Philipine Press, 2006.

Maroney, Eric. Religious Syncretism. London: NI ONX, SCM Press, 2006.

Liban Chukkala Werda Culture and Tourism Office. "Liban Chukkala Socio Economic Profile for the year 2001 E.C." (unpublished), Adulala, 2001.

Scoot, Vandaerstoep and Deirdre, Ohnston. Research Method for Every Day Life. Sanfransisco, Joss bass, 2009.

Sims, Martha and Marthine, Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions. United States of America, Utah University Press, 2005.

Stewart, Charles and Roslind, Shaw (eds). Syncretism/Anti-Syncretism: the Politics of Religious Synthesis. London: Routledge, 1994.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

| Faaruu | ዝማሬ |
|---|---|
| Ohoo yaa mare hoo | አሆ! ዞሮ መጣ ሆ....፣ |
| Yaa waaqa hunda uumtee | ሁሉን የፈጠረህ አምላክ ሆይ፣ |
| maree hoo | ዞሮ መጣ ሆ....፣ |
| Waaqa hunda keenya | የሁላችን ፈጣሪ፣ |
| maree hoo | ዞሮ መጣ ሆ....፣ |
| Mee nu ilaali waaqni | ወደ እኛ ተመልከት ፈጣሪ፣ |
| maree hoo | ዞሮ መጣ ሆ....፣ |
| Dhagahi maaf diddaa | ስማን ለምን እምቢ ትለናለህ፣ |
| maree hoo | ዞሮ መጣ ሆ....፣ |
| Nuyaadadhu jenna | አስታውሰን እንልሃለን ፈጣሪ፣ |
| maree hoo | ዞሮ መጣ ሆ....፣ |
| Uumaa kee hin dagattu | የፈጠርከውን አትረሳም፣ |
| maree hoo | ዞሮ መጣ ሆ....፣ |
| Fardi irraan gadee kaata | ፈረስ ቁልቁል ይሮጣል |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| irraa gadis dhaadata | ላይ ታችም ይጋልባል |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| Waaqa shanan giddaa | የአምስቱ ጊዳ አምላክ |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| Guyyaan torbaniin sokka | ቀን በሳምንት ይሄዳል |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| Bade warri siin morke | አንተን የተሟገቱ ጠፉ |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| Ilaali kan gootu ati | ምታደርገውን እይ |

| | |
|---|---|
| Situ waaqa hundaati | አንተ ነህ የሁሉ ፈጣሪ |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| Galaan kan bule goota | ጀግና በስንቁ ያድራል |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| Afaan banatti aayyoleen | አቴቴዋ አፏን ትናገራለች |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |
| Afaan babbanaa deemti | እየተናገረች ትሂዳለች |
| maree hoo | መሬ ሆ.... |

## Faaruu / ዝማሬ

| | |
|---|---|
| Ohoo,ohoo ohooyee gama roobee hoo | ኦሆ... ማዶ ዘነበ ኦሆ... |
| Adiiyyoohoo, hoo hoo gama roobee | አዲዮ ሆ ፣ ሆ... ፣ማዶ ዘነበ ኦሆ... |
| Adiyyoohoo hoo,hoo bara baraan hoo hoo | አዲዮ ሆ ፣ ሆ... ፣ በየ ዓመቱ ሆ... |
| Seerri ilmoorra marara, hee | ህግ ከልጅ ይበልጣል ሆ... |
| Gabbataa, kan gabbataa dhalche | ወፍራም ወፍራም የወለደ፣ |
| Seera oromoo kan mirga nuuf galche | መብታችንን የመለሰልን የኦሮሞ ሕግ |
| Gabbisayyoo hoo hoo | የሚያወፍር ሆ.... |
| Roobee,roobee dimbiliixee hee | ዘነበ ዘነበ ምድሩ ለመለመ ሄ--- |

## Ebisaa tokkoffaa / የመጀመርያው መራቂ

| | |
|---|---|
| Na ofkolchaa, | ደፋር አትበሉኝ፣ ሳይገባኝ ስለምናገር ይቅናህ በሉኝ፣ |
| Ganami nu haa ofkolchu | ንጋቱ ይቅናን፣ |
| Galgalli nu haa ofkolchu | ምሽቱም ይቅናን ብሩህ ሁን፣ |
| Hayyee waaqi (2) | አቤቱ ዓምላክ ሆይ፣ (2 ጊዜ) |
| Waaqa uumaa | ፈጣሪ አምላክ፣ |
| Waaqa uumamaa | የፍጥረታት ፈጣሪ፣ |
| Waqaa jechuun kan hundaa | አምላክ ማለት የሁሉም ነው፣ |
| Lafa jechuun kan hundaa | መሬት ማለት የሁሉም ነው፣ |

| | |
|---|---|
| Sagaltama Gabraa | ዘጠናው አገልጋዮች፣ |
| Saglan Booranaa | ዘጠኙ ቦራናዎች፣ |
| Torban Baarentummaa | ሰባቱ ባሬንቱዎች፣ |
| Waaqa Gurraachaa garaa garbaa | ሆደ ሰፊው ጥቁር አምላክ |
| Waaqayyo mil-lama bobbaasne | እግዚአብሔር ሁለት እግር አሰማራን፣ |
| Waaqayyoo mil-afur bobbaasne | እግዚአብሔር አራት እግር አሰማራን፣ |
| Bobbaa bobbaasii | ያሰማራነውን አሰማራ፡፡ |
| Tiksee xinxalaa godhi | እረኛውን ብልህ አድርገው፣ |
| Hidda dhalaadduu godhi- | ስሩን ሳር አድርግላቸው፣ |
| Malkaa fitisa godhi- | ወንዙን ተጠጥቶ የሚያረካ፣ |
| Luuxxuu ijabaa godhi- | ሊባን አይኑን ጨለማ አርግልን፣ |
| Biyyaa Maccaaf Tuulamaa- | የመጫና ቱለማ አገር፣ |
| Biyyaa fincaan Tulamaa sadeeni | የሶስቱ የቱለማ ልጆች ሀገር |
| Biyyaa Odaa Nabee | የኦዳ ነቤ ሀገር |
| Biyyaa Odaa shanani | የአምስቱ ኦዳዎች ሀገር |
| Biyyaa Caffee Shanani | የአምስቱ የጨፌ ሀገር |
| Biyyaa Tulluu Shanani | የአምስቱ የቱሉ ሀገር |
| Biyyaa waraana shanani | የአምስቱ የጦር ሀገር |
| Biyyaa Gadaa shanani | የአምስቱ የገዳ ሀገር |
| Waaqa qamaa shananin nu uumte | አምስቱን የስሜት ህዋሳት የፈጠርከ |
| Kan nagaan nubulchitee nagaaan nu olchi | በሰላም ያሳደርከን በሰላም አውለን |
| Tolaa wajiin nu olchi | ከቸር ጋር አውለን፣ |
| Hamaan gargar nu olchi | ከክፉ ለየን፣ |
| Darbataa Eboo qajelchi | ጦር ወር ዋሪውን አቅናለት፣ |
| Barataa qubee qajelchi | የተማሪውን ፊደል አቅና፣ |
| Taa'aa Gaaddisa qajeelchi | የተቀማጨን ጥላ አቅና፣ |
| Murteessa murti qajeelchi | የፈራጁን ፍርድ አቅና፣ |
| Jireenyaaf fayyaa qajeelchi | ለኑሮ ጤናን አቅና፣ |
| Irreecha Kan nagaa nuf godhi | ይሄንን እሬቻ የሰላም አድርግልን፣ |

Yaa'ii kana Yaa'ii nagaa nuuf godhi ይሄንን ጉባኤ የሰላም አድርግልን፤
Walga'ii kana wal ga'i nagaa nuf godhi ይሄንን ስብሰባ የሰላም አድርግልን፤
Marii Kana marii nagaa nuuf godhi ይሄንን ውይይት የሰላም አድርግልን፤
Kadhaa kana kadhaa nagaa nuuf godhi ይሄንን ጸሎት ለሰላም አድርግልን፤
Walii galtee nuuf kennii ስምምነትን ስጠን፤
Nugargaari! nu danaansi! እርዳን! ባርከን!

Jireenyaaf fayyaa qajeelchi ለኑሯችን ጤና ስጠን (አቅናልን)
Yaa waaqayyo irkoo cuqqaalaa አንተ የጨቃላ ደጋፊ አምላክ፤
Yaa waaqa lamaa liiban የኹለቱ ሊበን አምላክ፤
Yaawaaga shanan giddaa የአምስቱ ጂዳ አምላክ፤
Biyya biyya nagaa nuuf godhi ሀገራችንን ሰላም አድርግልን፤
Giddaa biyya nagaa nuuf godhni ጂዳን ሰላም ሀገር አድርግልን፤
Ada'aa biyya nagaa nuuf godli አድኣን ሰላም ሀገር አድርግልን፤
Liibaniin nagaaa nuuf godhi ሊበንን ሰላም አድርግልን፤
Nagaa dhugaa nuuf godlni ሰላሙንም የእውነት አድርግልን፡፡

Muudaa kana muudaa nagaa nuuf godhi ይህን ሹመት የሰላም ሹመት አድርግልን፤
Gadaa keenna gadaa nagaa nuuf godli ገዳችንንም የሰላም አድርግልን፤
Kan dubbanne dhugaa nuuf godhi የምንናገረውን እውን አድርግልን፤
Elaa bakkeen kun ulfaataadha iddoo itti ይህ ቦታ የተከበረ ነውና
Aadaa guddifatan ባህላችንን የምናሳድግበት፤
Biyya fardi itti garmaamu ፈረስ የምንጋልብበት፤
Biyya itti muudan ሹመት የምንሾምበት፤
Biyya dadhaa nuuf haa ta'u የቅቤ ሀገር ይሁንልን፤ (የተመቸ ለማለት ነው)
Biyya kana biyya aannanii nuuf godhi ይህን ሀገር የወተት ሀገር ያድርግልን፤
Biyyaa kana biyya dammaa nuuf godhi ይህን ሀገር የማር ሀገር ያድርግልን፤
Biyya kana biyya wal jaalattu nuuf godhi ይህን ሀገር የሚዋደድ ሀገር ያድርግልን፤
Nama wal jibbu nuyirraa haa qabu የማይዋደድን ሰው ከእኛ ያርቅ፤

| | |
|---|---|
| Kan wal dhibu nuyirraa haa qaba | የማይስማማን ሰው ከእኛ ያርቅ፣ |
| Biyya kana wal nuhaa jaalachiisu | ሀገራችንን እንድንወድ ያድርገን፣ |
| Kana fudhadaa | ይህ ምርቃት ይደረግላችሁ፡፡/ተቀበሉ/ |

| | |
|---|---|
| **Jaarsa lamaffaa** | **ኹለተኛው ሽማግሌ** |
| hayyee,waaqa (2) | አቤቱ አምላክ ሆይ (2 ጊዜ) |
| Sagaltama Gabraa | ዘጠናው አገልጋዮች፣ |
| Saglan Booranaa | ዘጠኙ ቦረና |
| Waaqa Gurraachaa garaa garbaa- | ሆደ ሰፊው ጥቁር አምላክ |
| Waaqayyo galtee fi gantee nu lagi | አምላክ ሆይ ከስደትና ከቃላባይነት ሰውረን፣ |
| Waaqayyo kunoo siidaa kana kadhanna | አምላክ ሆይ ይህን ሲዳ እንለምንዋለን፣ |
| Sammuu cuqqaalaatti garagallee | ወደ ጨቃላ አናት ዙረን፣ |
| Atihu milkeesi | አንተ አሳካልን፣ |
| Waaqayyo milkee ittiin nu galchi | አምላክ ሆይ በስኬት መልሰን፣ |
| Waaqayyo barahaa kana nuuf qabbaneessi | አምላክ ሆይ በረሀውን አቀዝቅዝልን፣ |
| Waaqayyo sa'aaf toli | አምላክ ሆይ ለከብቶቻችን ራራ፣ |
| Waaqayyo namaaf toli | አምላክ ሆይ ለሰዎቻችን ራራ፡፡ |
| Waaqayyo liibaniin nagaa godhi | አምላክ ሆይ ሊበንን ሰላም አድርግልን፣ |
| Xinnaa guddaa nagaanuuf godhi | ታናሽ ታላቁን ሰላም አድርግልን፣ |
| Bobbaa bobbaafna sa'a bobbafanna | ያሰማራናቸውን ከብቶች አሰማራልን፣ |
| nama bobbafanna si haa mararu | ሰዎችን እናሰማራለን፣ ደስ የሚያሰኝህ ይሁን |
| Marartee kee nuuf fidi | መውደደህን አምጣልን |
| Waaqayyo naqaa nuuf roobi | አምላክ ሆይ የሰላም ዝናብ አዝንብልን፣ |
| rooba ija garaa nu lagi | በረዷማ ዝናብን አጥፋልን፣ |
| roobii doroolloo baasi | ዝነብና ለምለም ሳር አብቅል፣ |
| Sa'aa namaan nuuf nahi | ለከብቶቻችንና ለሰዎቻችን ራራልን፣ |
| Nahii fiixaan nuuf gahi | ራርተህም ለስኬት አብቃን፡፡ |

| | |
|---|---|
| Kan deema fiixaan nuuf ga'i | ተጓገሮችን በሰላም አድርሳቸው፡ |
| Hattuu aadaan nuuf qabi | የሌባን እግር ቂጤማ አድርግልን፡ |
| Waaqayyoo kunoo garaa fayyaan sikadhanna | አምላክ ሆይ በንጹህ ልባችን |
| | እንለምንሀለን |
| Saani si haa mararu | ከብቶቻችን ደስ ያሰኙህ፡ |
| Sanyiin si haa mararu | የእህል ዘራችን ደስ ያሰኝህ፡ |
| Elaa sanyiin suramfee jirti | እነሆ የእህል ዘራችን ተበጥሯል፡ |
| Sagaan camadamee jira | በሬዎቻችንም ተጠምደዋል፡ |
| Mee ati uumaa nuuf deebisi | ፈጣሪ ሆይ እስኪ ፊትህን መልስልን፡ |
| Waan hin dhageenye | ያልሰማነውን |
| Kan hin agarre | ያላየነውን |
| Kan nutti deemu ati nurraa qabi | የሚሄድብንን ያዝልን /አርቅልን/። |
| Mootummaa nagaan nuuf bulchi | መንግስትን በሰላም በመንበሩ አቆይልን፡ |
| Nuun jalatti nu bulchi | እኛንም በእርሱ ሥር አስተዳድረን፡ |
| Gadaattin nu bulchi | በገዳ አሳድረን፡ |
| Kan nu ganu nu lagi | ከከሀዲዎች ሰውረን፡ |
| Jaarsatti nu bulchi | በሽማግሌ አሳድረን፡ |
| Biyya nagaa nuuf godhi | የሰላም አገር አድርግልን። |

### Jaarsa sadaffaa — ሦስተኛው ሽማግሌ

| | |
|---|---|
| Waaqni nagaan nu bulche | በሰላም ያሳደረን |
| nagaan nuu haa oolchu | በሰላም ያውለን፡ |
| Hundee oromiyaa rabbi nuuf haa guddisu- | የኦሮሞን መሠረት ያስፋልን፡ |
| Biyya keenya biyya nagaa nuuf godhi- | ሀገራችን ሰላም ያድርግልን፡ |
| Nagaa dhugaa rabbi nuuf haa godhu- | ሰላሙንም የእውነት ያድርግልን፡ |
| Waaqni namaaf nama walitti haa araarsu- | የተጣሉትን ሰዎች ፈጣሪ |
| | ያስታርቅልን፡ |
| Waaqni uumaa nu haa jaalatu- | ፈጣሪ አምላክ ይውደደን፡ |
| Nagaatti nu haa jiraachisu- | በሰላም ያኑረን፡ |

Gadadoo rabbi nu haa oolchu-
Biyya keenya biyya nagaa haa godhu-
Rabbi dhugaa nuuf haa ba'u-
Rabbi nutti haa araaramu-
Rabbi namaan nutti haa araaramu-
Kan dubbanne dhugaa haa godhu
Waaqni cuqqaalaatii nuuf haa dubbatu-
Waaqni awaashii fi nabee nuuf haa dubbatu፣
Hara dambalii nuuf haa dubbatu-
Dhalli keenya nuuf qara haa ba'u-
Kan daldaluuf fixaan haa ba'u-
qotee bulaaf fixaan isaaf haa ba'u-
Dachee fi samii walitti nu haa araarsu-
Barri kan nagaa nuuf haa ta'u-
Itti guutaan waaqa haa ta'u-

ከድህነት ያውጣን፣
ሀገራችንን ሰላም ያድርግልን፣
እግዚአብሄር እውነትን ይግለጥልን፣
እግዘአብሄር ይታረቀን፣
እግዘአብሄር በሰው ይታረቀን፣
የምንናገረውን እውነት ያድርግልን፣
አምላክ በጩቃላ ይናገርልን፣
የአዋሽና የነቢ አምላክ ይናገርልን፣
ከደምበል ሀይቅ ይናገርልን፣
የልጆቻችንን ምኞት ያሳካልን፣
ለሚነግደው ይሳካለት፣
ለገበሬውም ይሳካለት፣
ሰማይና ምድርን ያስታርቃቸው፣
ዘመኑን የሰላም ያድርግልን፣
የቀረውን ፈጣሪ ይሙላ፡፡

## Ebisaa Afraffaa

Waaqni hundaa galanni siif ha
Bobbaa bobbaaffanna
mootummaan kee nuuf Haa bulu
Miila lama bobbaafna
Mila afur bobbaafna
Bobbaa bobbaate nagaan nuuf haa deebisu
Hangaa fi guxisuu walitti haa bulchu
Giddi hangafummaan haa bulu
Nu illee miila isaanii Jaalatti nu haa bulchi
Uumaan keenya uumaa durii haa taatuu
Rabbi uumaa keenya nuuf haa qajeelchu

## አራተኛው ሽማግሌ

የሁሉ ፈጣሪ ምስጋና ይድረስህ፣
እኛ እናሰማራለን፣
መንግስትህ ይደርልን፣
ኹለት እግር እናሰማራለን፣
አራት እግር እናሰማራለን፣
ያሰማራነውን በሰላምይመልስልን፡፡
ታናሽና ታላቅን ያዋዳቸው፣
ጂዳ በታላቅነቱ ይደር፣
ከጂዳ ስር ያሳድረን፣
ፈጣሪአችን የዱሮው ይኹንልን፣
ፈጣሪ ፍጥረታችንን ያቅናልን፣

| | |
|---|---|
| Waaqni kan bobba'e nagaan nuuf haa galchu | የተሰማራውን በሰላም ይመልስልን፣ |
| Kan maseentu nuuf haa dhaltu | መካን ትውለድልን፣ |
| Ilmi afaan abbaa haa beeku | ልጅ የአባቱን ቃል ይወቅ፣ |
| Abbaan afaan ilmaa haa beeku | አባትም የልጁን ቃል ይወቅ፣ |
| Niitiin afaan dhirsaa haa beektu | ሚስት የባሏን ቃል ትወቅ፣ |
| Uumaan keenya uumaan oromoon | ፈጣሪያችን የኦሮሞ ፈጠሪ፣ |
| Akkuma nudagaagaasaa deemtutti | እያሳደግሽን እንደምትሄድ፣ |
| Ammallee guddachaa haa deemnuu | አሁንም እያደግን እንሂድ፣ |
| Namichi uumaa oromoon nutti deemullee | በኦሮሞ አምላክ የሚመጣብንንም፣ |
| Haa guddatu | ያሳድግልን፣ |
| Gadaan quufa haa ta'u | ገዳ ጥጋብ ይኹንልን፡፡ |

## Jaarsa shanaffaa / አምስተኛው ሽማግሌ

| | |
|---|---|
| Yaa waaq ati nu dhagahi | ፈጣሪ ሆይ ስማን፣ |
| Muuda keetin deemna | በቸርነትህ እንሄዳለን፣ |
| Ammallee hu muudi | የተገባን አድርገን፣ |
| Dhiifaama nuuf godhi- | ይቅርታ አድርግልን፣ |
| Dhugaa nuuf haadeebisu | እውነትን መልስልን፣ |
| Dhugaan bade haa galtu | የጠፋች እውነት ካለች ትመለስ፣ |
| Bakkeen kun Bakkee nagaa haa ta'u | ይህ ቦታ የሰላም ይኹን፣ |
| Ammallee kan waliin cooma nyaatee | ጮማ ምንቆርጥበት ይኹን፣ |
| waliinDaadhii dhugu nu haa godhu | ጠጅ ምንጠጣበት ይኹን፣ |
| Bakkeen kun bakka irreechaa haa taatu | ይህ ቦታ የእሬቻ ቦታ ይኹን፣ |
| Bakkeen kun bakka kabajaa haa taatu | ይህ ቦታ የክብር ይኹን፣ |

## Faruu / ዝማሬ

| | |
|---|---|
| Warri waaqayyoohee noorii beeka hee | የእግዚአብሄር ልጆች ኖር ያውቃሉ፣ |
| Noori yaa waaqayyohee | ኖር እግዚአብሄር፣ |

| | |
|---|---|
| Har'i sagaleekeetikaa yee | ዛሬ የድምፅህ ቀን ነው፡፡ |
| Waaqayyo noorii jaalatahee | እግዚአብሄር ኖር ይወዳል፣ |
| noori yaaa waaqayyohee | እግዚአብሄር ሆይ ኖር፣ |
| Warri waaqayyo hee | የእግዚአብሄር ሰዎች፣ |
| nooriidhaan bulahee | እንግዳን መቀበል ልማዳቸው ነው፣ |
| Kan nagaan bobba'e nagaan nuu galehee | በሰላም የተሰማራው በሰላም |
| | ይመለስልን፣ |
| Gooftaatu kana nuuf godhehee | ፈጣሪ ነው ይሄን ያደረገልን፣ |
| noori yaa waaqayyohee | እግዚአብሄር ኖር፣ |
| Oromoon nagaan bulehee | ኦሮሞ በሰላም አደረ፣ |
| Waaqatu mala nuuf male | ፈጣሪ ነው ብልሃት ያስተማረን፣ |
| noori yaa waaqayyohee | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Jaarsatu burqaa baase | ሽማግሌ አፈለቀ፣ |
| Biyya koo burqaan baate | ለሀገሬ ምንጭ ፈለቀ፣ |
| Oromoof aadaan taate | ለኦሮሞ ባህል ሆነ፣ |
| Gabareen qotuuf kaate | ገበሬ ለእረሻ ተነሳ፣ |
| Biiyyi koo nagaa taate | ለሀገሬ ሰላም ሆነ፣ |
| Galanni sii ta'u | ምስጋና ይሁንልህ ኖር ዋቀዮ፣ |
| noori yaa waaqayyo | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Nanni iddootti bule | ሰው በቦታው አደረ፣ |
| Hundumtuu nagaa ta'e | ኹሉም ሰላም ሆነ፣ |
| Maseena iyyoo fure | የመካናን ማኅፀን ፈታ፣ |
| Biyyallee nagaa ta'e | ሀገሩም ሰላም ሆነ፣ |
| Galaanni isa haa ga'u | ምስጋና ይድረስህ፣ |
| Ayyaanni oromoo ifa ba'e hee Noori | የኦሮሞ አያና ጸጋው ታወቀ |
| yaa waaqayyoo hee | ኖር ዋቀዮ፣ |
| Oromoon aadaan bula | ኦሮሞ በባህል ይኖራል፣ |
| Oromoon kaayyoon bula | ኦሮሞ በእቅድ ይኖራል፣ |
| Kaayyoo kana waaqatu kaye | እቅዱም በፈጣሪ የተቀመጠ ነው፣ |

| | |
|---|---|
| Noorii yaa waaqayyohee | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Maalkaa fi Tulluutti baanaan | ወደ ወንዝ እና ተራራ ሲወጣ |
| Noori beekaa haa | ኖር ያውቃል፣ |
| Noorii yaa waaqayyohee | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Maaloo adaraa tokko taana | አደራ አንድ እንሁን፣ |
| Maaloo adaraa maaliif addaan baanayee | አደራ ለምን እንለያያለን፣ |
| Noori yaa waaqayyo | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Malkaan yoo dhabne roobaan | ወንዝ ካጣን በዝናብ፣ |
| Malee kan dhugaa taati- | የእውነት ይሆናል፡፡ |
| Galanni haa isaa gahu, Noori beekaa | ምስጋና ይድረሰው፣ |
| noori yaa waaqayyo | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Oromoon roobaan bulaa | ኦሮሞ በዝናብ ያድራል፣ |
| Rooba nagaa hasaasaa | ዝናብ ሰላምን ይገልጻል፣ |
| Malkaa odaa fi caaccuu | ወንዝ፣ ኦዳ እና ጫጬ፣ |
| Maqaa odaan hasaasa | የኦዳን ስም ይገልጻሉ፡፡ |
| maaloo Gurraacha malkaatu | የወንዝ ፈጣሪ ጥቁር፣ |
| Nama koo maqaa baasaa | ሰዎችን ተዋቂ አደረጋቸው፣ |
| Oromoon noorii beeka | ኦሮሞ ኖር ያውቃል፣ |
| nooriyaa waaqayoo | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Koottuutii nu milkeessi | ና እና አሳካልን፣ |
| Maquma keetiln Lallabee | በአንተ ስም እናገራለሁ፣ |
| nooriyaa waaqayoo | ኖር እግዚአብሄር፣ |
| Awaash gubbaa ejjetee | ከአዋሽ በላይ ቆሞ፣ |
| Waabeetti tarkaanfatee | ወደ ዋቤ ተራምዶ፣ |
| Oromon ofii dhufee | ኦሮሞ ራሱ ተሰብስቦ፣ |
| Walitti dachafatee | አንድነትንም መሥርቶ፣ |
| Rabbuma guddankana | ይህንን ትልቅ አምላክ፣ |
| Maalqaba yoo kadhate | ምናለ ቢለምነው፣ |
| Rabbi alamiin kana | ይህንን የዓለም ጌታ፣ |

| | |
|---|---|
| maalqaba yoo gaafate | ምናለ ቢጠይቀው፡፡ |

## ከዝማሬ በኋላ የተደረገው ምርቃት

| | |
|---|---|
| Mee rabbi nuf haa owwaatu | ፈጣሪ አቤት ይበለን፣ |
| Biyya kenya nagaa naa godhu | ሀገራችንን ሰላም ያድርገው፣ |
| Nagaa dhugaa nuuf haa godhu | ሰላሙንም የእውነት ያድርግልን፣ |
| Afaan kun kan booranaa haa ta'u | ይህ ንግግራችን የቦረና ይሁን፣ |
| Har'aaf kaleessa rabbi nuuf haa dubbatu | እንደ ትላንቱ ዛሬም ፈጣሪ ይናገርልን፣ |
| Meerabbi roobaan nu haa qaqqabu | ፈጣሪ በዝናብ ይድረስልን፣ |
| Kan namni wal nyaatu nutti haa aaraaramu | ሰዎች እንዳይጣሉ ይታረቀን፣ |
| Hamaa rabbi nurraa haa qabu | ክፋትን ያስወግድልን፣ |
| Kan barate ifatti nuu haa ba'u | የተማረ ይሳካለት፣ |
| Kan qotu maasaatti nuuf haa ba'u | አራሽ በማሳው ይሳካለት፣ |
| Biyya keeyya salaami nuuf haa ta'u | ሀገራችንን ሰላም ያድርገው፣ |
| Jaalalli waaqarraa nuuf haa bu'u | ፍቅር ከሰማይ ይውረድልን፣ |
| Malkaaf tulluun tole nuuf haa jedhu | ወንዙ ተራራው እሺ ይበለን፣ |
| Nama malkaatti ba'ee argatu rabbinu haa godhu | ወንዝ ሄደን የምንለምነው የሚሰማ ይሁንልን፣ |
| Mee robaan rabbi nu haa qaqqabu | ፈጣሪ በዝናብ ይድረስልን፣ |
| Qabbanaan nu haa ga'u | በጥላ ይድረስልን፣ |
| Oromoon sanyin tokkicha haa godhu | ኦሮሞን በዘር አንድ ያድርግልን፣ |
| Kan ani hin jedhiin waaqni itti haa guutu | የጎደለውን ፈጣሪ ይሙላበት፡፡ |
| Itti guutaan waaqaaf lafa haa ta'u | ጎዶሎን የሚሞላ እሱ ይሁን፡፡ |

## ዳቦ ሊቆረስ ሲል የተካሄደ ጭፈራ

| | |
|---|---|
| Yaa waaqayyo hee | እግዚአብሄር ሆይ፣ |
| Nagaan oolteen galata kee | በሰላም ውሎ መግባት ባንተ ነው፣ |
| Gurracha urjiin kumaa hee | ጥቁር ባለ ሺህ ከዋክብት፣ |

| | |
|---|---|
| Yaa waaqayyoo hee uumaahee | እግዚአብሔር፣ ፈጣሪ ሆይ፣ |
| Suma hiyyeessaaf galata kee | የድሆች አምላክ ነህና እናመሰግንሀለን፣ |
| Kan kee tolli suutumaahee | በጎነትህ ዘግይቶ ነው፣ |
| Kaleessa kalee keetii, yaa waaqayyoo | አምላክ ሆይ ትላንት ያንተ ቀን ነበር፣ |
| Har'i sagalee keetii | ዛሬም ያንተው ቀን ነው፡፡ |
| Urjii samirraa gugsee | ሰማዩን በከዋክብት አስጌጠ፣ |
| Kan dhugaa qabu tumsee- | ለእውነተኛው አገዘ፣ ፈረደ፣ |
| Yaa waqaayyoo hee, gungumaakoohee | አስገምጋሚው ፈጣሪዬ፣ |
| Raagiyyoohoo akkana yaanaa hee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን እንዲህ እንወጣልሃለን |
| Raagiyyoohoo amma dachaanaahee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን አሁን እንመለሳለን፣ |
| Raagiyyoohoo cuqqala gumaahee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን ጨቃላ ያንተ ፍሬ ነው፣ |
| Raagiyyoohoo dhaaba dukkanniihee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን ጨለማን ያመጣል፣ |
| Raagiyyoohoo yoo tole ibsaahoo | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን ፈቃዱ ሲሆን ብርሀን ያደርገዋል፣ |
| Raagiyyoohoo gowwaa dheesisee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን ፈሪን አባረረልን፣ |
| Raagiyyoohoo akkana yaanahee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን እነሆ እንዲህ፣ እንወጣልሃለን፣ |
| Raagiyyoohoo amma dachaanahee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን አሁን እንመለሳለን፣ |
| Boovanaa bahee | ፈጣሪ ከቦቫና ወጣ፣ |
| Boovanaa bahee | ፈጣሪ ከቦቫና ወጣ፣ |
| Gaangota isaa Sassa kaallatee | በቅሎዎቹን እግራቸውን ያዛቸው፣ |
| Cuqqee bahee, cuqqinnoo bahee | የመከራውን ሜዳ አለፈው፣ |
| Xabala fingaa natu waraabbatee | የፊንጋን ጠበል የቀዳሁት እኔ ነኝ፣ |
| Hawoo bu'ee, Awash bu'ee | ፈጣሪ ወደ ሀዎ ወረደ፣ አዋሽም ወረደ፣ |
| Daaroo billee irra dhaa hee | ዳሮቢሌ ላይ ቆመ፣ |
| Ohee hee ofumaan bulaa hee | በራሱ ይመራል፣ |
| Doonii obaasaa booka bulbulaa hee | የሚጣፍጠውን የማር ጠጅ በጥብጣችሁ አዘጋጁት፣ |

| | |
|---|---|
| Hayyoolee obaasaahee bulbulaa hee | እቴቴን አጠጧት፡ |
| Raagunnlee hee | ፈጣሪ ሆይ ቆይልን፡ |
| Cuqqaalaa gubbaa hee | በጨቃላ ተራራ ላይ፡ |
| Gariinn dabeessa hoo | ግማሹ ፈሪ ነው፡ |
| Yoo tole iddoon hee | ሁኔታው ከተመቻቸ፡ |
| Raaga oddeessa hee | ረጅም ዕድሜ ማግኘትን ያወራል፡ |
| Yaa maariyaam loon galanmi hoo | ማርያም ሆይ ከብቶቻችን ገቡልን፡ |
| Yaa maariyaam loon galanmi hoo | ማርያም ሆይ ከብቶቻችን ገቡልን፡ |
| Situ haadha caffeeti, sireeti | አንቺ ነሽ ባለ ቁጠማ፡ |
| Siif haa horan loon | ከብቶች ይርቡልሽ፡ |
| Situ haadha bakkeeti | የማሰማርያቸው ቦታ ባለቤት አንቺ ነሽና፡ |
| Siif haa horan loon | ከብቶች ይርቡልሽ፡ |
| Yaa maar iyaam loon galanihoo | ማርያም ሆይ ከብቶቻችን ገቡልን፡ |
| Guraalee gur'uu darsaa | ጥቋቁር ባለ ትልልቅ ግቶች፡ |
| Loon galan hoo yee | ከብቶቻችን ገቡልን፡ |
| Dachaa haadha coomaayee | ጥንድ ባለ ሎማዎች፡ |
| Loon galanihee | ከብቶቻችን ገቡልን፡ |
| Galee waatiyyoo maarsahee | ገብተው ጥጆቻቸውን ከበቧቸው፡ |
| Mikaayela of nag a'ee | ሚካኤል ራሴን አስቻለኝ፡ |
| Mikaayela jaadaa of na ga'ee | ታላቁ ሚካኤል ራሴን አስቻለኝ፡ |
| Safaareeffa fuulee of na ga'ee | ለሰውና ለከብት ያስባል፡ |
| Mikaa'elli duulee nubira ga'ee | ሚካኤል ዘምቶ ደረሰልን፡(2) |
| Safaareeffa fuulee of na ga'ee | ገደሉን እየሞላ ደረሰልን፡ |

| | |
|---|---|
| Ya abbaayyee | አባታችን ሆይ |
| Ya abbaayyee koo maaloo | አባታችን ሆይ አደራ፡ |
| Kan sodaatan miila hee | የሚፈራ እግር ነው፡ |
| Gooftaa dursaa dhiiraa hee | ፈጣሪ የወንድ መሪ፡ |
| Muka boojun raadaa | የምናሽንፍበት ብትራችን፡ |

| | |
|---|---|
| Ya abbaa booraa yaa dhuma kee | የቦራ አባት ፈጣሪ ሆይ፣ |
| Ya gambeela daarii caffee | የጨፌ ዳር ጋምቤላ (የእንጨት ስም)፣ |
| Ya gabri'eela abbaa nafsee hoo | ገብርኤል የነፍስ አባታችን፣ |
| Yoom dhuftee geese hoo | ከመቼው መጥተህ ደረስክልን፣ |
| Aayyoleen, cirracha mootee | አቴቴ በጠጠር አሸነፈች፣ |
| Cilaaloo moo gaboo biyya oolte | ከጭላሎ ወይስ ከጀቦ (ሀገር) ነበርሽ፣ |
| Cuqqaalaa moo gaboo biyya oolte | ከጩቃላ ወይስ ከጀቦ (ሀገር) ነበርሽ፣ |
| Hora arsaadee moo gaboo biyya oolte | ሆራ አረሰዲ ወይስ ከጩቂ (ሀገር) ነበርሽ፣ |
| Dhaltiin okolee guutee | የወተታችን ማለቢያ ሞላልን፣ |
| Hara Arusii buutee | ወደ አርሲ ሀይቅ ሞልቶ ፈሰሰ፣ |

## ምርቃት

| | |
|---|---|
| Ohuu klaaqaa | አምላክ ሆይ፣ |
| Kaadhima keeaya waaqaa | እጮኛዎቻችንን፣ |
| Daa'ima keeaya waaqaa | ልጆቻችንን፣ |
| Nagaa nuuf gadhi waaqa | ሰላም አድርግልን፣ |
| Farad keenya collee nuuf godhi waaqae | ፈረሶቻችንን ፈጭ አድርግልን፣ |
| Ayyaan tuu nugodhi waaqa | እድላም (አያንቱ) አድርገን፣ |
| Wal jaalachuu nuuf fidi | መዋደድን ፍጠርልን (ሰጠን)፣ |
| Figirii waaqamaa nuuf fidi waaqaa | ፍቅርን ከሰማይ አድለን፣ |
| Nama eebbaan gale nugodhi waaqaa | የተመረቁ ሰዎች አድርገን፣ |
| Afaa waaqaafiin nuuf dubbadhu waqqaa | የሰላም ንግግር አናግረን፣ |
| Jaarsi eebbisee waaqaarraa hin dhabiin | ሽማግሌ የመረቀው ይድርስለት፣ |
| Gimbii fi waabeen kan abbaa fi waaqaa | ጊንቢን እና ዋቤን የኛ አድርግልን፣ |
| Daa'immi keenya haa ta'u waaqaa | ሕጻናቱ ይጥኑ፣ |
| Ilmoon afaan haadhaa haa beeku waaqaa | ልጅ የእናቱን ቋንቋ ይወቅ፣ |
| Ilmoon afaan abbaa haa beeku waaqaa | ልጅ የአባቱን ቋንቋ ይወቅ፣ |
| Abaarsa jalaa nuuf haa baatu waaqaa | ልጆቻችንን እርግማን አያግኛቸው፣ |
| Koola rabbi numa haa gabn waaqaa | በጥላህ ጋርደን፣ |

| | |
|---|---|
| kaa nama hin tuffanne | ሰውን የማትንቅ ፈጣሪ ሆይ |
| biyyi keenya salamii haa ta'uu | አገራችን ሰላም ይሁንልን፣ |
| Igoolleen Barattee haogii haa argath, rabbi | ልጆቻችን ተምረው ባለ ስራ ይሁኑልን፣ |
| isniif haa ta'u | ይህ ይሁንላችሁ፣ |

## ሌላ መራቂ

| | |
|---|---|
| oromoon waaqffataa waqqaan bula haa ta'uu | ኦሮሞ በፈጣሪ የሚያድር ዋቄፋታ ይሁን፣ |
| Oromoon kan waaqni itti dhiyaale haa ta'uu | ኦሮሞ ፈጣሪ የቀረበው ይሁን፣ |
| Gabareef biiffuun haa ba'u- | ለገበሬ ፀሐይ ይውጣለት፣ |
| Kan gabareef hin tolle nurraa lafa haa dhahu | ለገበሬ የማይበጀውን ከመሬት ይደባልቅልን፣ |
| Bakka malkaan girtuth' | ወንዝ ባለበት ቦታ፣ |
| Bakka dhugaan jirfutti | እውነት ባለበት ቦታ፣ |
| Kan kadhatee argatu nu haa godu | ለምኖ የሚያገኝ ያድርገን፣ |
| Diina nurraa haa qabu | ከጠላት ይሰውረን፣ |
| Qaaliin kan rabbi haa ta'uu | ቃል የፈጣሪ ይሁን፣ |
| Itiguutaan Waaqa Haa ta'u | የጎደለውን የሚሞላ ፈጣሪ ይሁን፣ |
| Abbaan lafaa nuf haa dhufu | መሬትን የፈጠረ አባት ይምጣልን፣ |
| Abbaan Hundaa nuth haa dhufu | የሁሉ አባት ይምጣልን፣ |
| Kan lamaan liibaan nuuuf haa dhufu | የሁለቱ ሊበን ፈጣሪ ይምጣልን፣ |
| Kan iddoo cuggaalaa nuuuf haa dhufu | የጨቃላ ሊበን ፈጣሪ ይምጣልን፣ |
| Abbaan Nama uume nuuuf haa dhufu | ሰውን የፈጠረ አባት ይምጣልን፣ |
| Abbaan Muka uume nuuuf haa dhufu | ዛፉን የፈጠረ አባት ይምጣልን፣ |
| Abbaan sa'a uume nuuuf haa dhufu | ከብትን የፈጠረ አባት ይምጣልን፣ |
| Abbaan bineensa uume nuuuf haa dhufu | አራዊትን የፈጠረ አባት ይምጣልን፣ |

| | |
|---|---|
| Abbaan dhugaa kana uume nuuuf haa dhufu | የዚህ እምነት አባት ይምጣልን፡ |
| Caffee Dambal irraa nuuuf haa dhufu | ከደምበል ወንዝ ይምጣልን፡ |
| Caffee Qooqaa irraa nuuuf haa dhufu | ከቆቃ ሐይቅ ይምጣልን፡ |
| Gaaddidduun isaa nunf haa desssi'n | ቸርነቱ ይደረግልን፡ |
| Kan nu ballessn nurraa haa badu | ጠላታችን ከኛ ይጥፋ፡ |
| Kan nudhnibe haa dhibamn | እኛን ያስቸገረ ይቸገር፡ |
| Kan nu cabse haa cabu | የሚሰብረን ይሰበር፡ |
| Kan siidaa keenya cabse haa cabu | ሲዳችንን የሚያጠፋ ይጥፋ፡ |
| Kan aadaa keenya cabse haa cabu | ባህላችንን የሚያጠፋ ይጥፋ፡ |
| Kan nu miidhe haa miidhamu | የሚጎዳን ይጎዳ፡ |
| Kan sa'a Keenya ujiidhe haa miidhamu | ከብቶቻችንን የሚጎዳ ይጎዳ፡ |
| Kan dhugaa keenye irriite haa rivriitu | እውነታችንን የረገጠ ይጥፋ፡ |
| Gooftaan keenya natt haa dhufan | ፈጠሪያችን ይምጣልን፡ |
| Nuyi hin morru, hin fallu | እኛ አንጠነቁልም ከፉም አናስብም፡ |
| Wallaquma kadhamna | የምንለምነው ፈጣሪን ነው፡ |
| Dhugaaf dubbanna | የምንናገረው እውነት ነው፡ |
| Gadaatti bulla, Gadadoo nu lagi | የምናድረው በገዳ ነው፡ ከድህነት አውጣን፡ |
| Jenneti gadaatti bulla- | ብለን ነው ከገዳ የምናድረው፡ |
| Nama hin minu aadaa' namaa hin miinu | ሰውን እንንጎዳም፡ የሰውን ባህልም እንንጎዳም፡ |
| Safuu namaa hin sukkuumnu | የሰውን እሴት እንረግጥም ፡ |
| Waaqayyo kan safun keenya | ፈጣሪሆይ ልማዳችንን፡ ባህላችንን፡ |
| Aadaa keenya | የሚረጋግጠውን አጥፋልን፡ |
| Nilyirraa haa qabin | ፈጣሪ ሆይ ፡ |
| Uummata liiban | የሊበንን ህዝብ፡ |
| Uummata Giddaa | የጊዳን ህዝብ፡ |

| | |
|---|---|
| Uummata biyya kanaa | የዚህችን ሀገር፣ |
| Uummata aanaa Liiban cuqqaalaa | የሊበን ጩቃላ ወረዳን ህዝብ |
| Wal nn haa jaa lachiisu | በፍቅር ያኑረን፣ |
| Hasa'aaa kanya keemyuma huy haa gudhu | የተናገርነውን ፈጽምልን |
| Nama nu baraadu | ነገር ከሚፈልገን ሰው፣ |
| Nama duudahaa keenya barbaadu | ባህላችንን ሊያጠፋ ከሚፈልግ |
| | ሰው፣ |
| Nama aadaa keehya dhiibu | ባህላችንን የሚገፋን ሰው፣ |
| Nama humrraan nudhiiba | በጉልበት የሚገፋን ሰው፣ |
| Waaqayyo isa haa dhiibu | እግዚአብሔር ይግፋው፡፡ |
| Wanti siidaa mudunu fa waaqa | ለሲዳ ስልጣን የምንሰጥበት |
| | ምክንያት፣ |
| harkaan qaqqabun dadhabneeti | ፈጣሪን በእጅ እንዳስሰውም፣ |
| Ijaan hin agaruu | በዐይን አናየውም፣ |
| Itti hin dubbannu | ልናናግረውም አንችልም፣ |
| Itti hin haasofnu | ልናጫውተው አንችልም፣ |
| Qilleensa nuuf uumee | አየርን ፈጠረልን፣ |
| Bishaan nuuf kennee | ውሃ ሰጠን፣ |
| Dhagaa nuuf kennee | ድንጋይ ሰጠን፣ |
| Maka nuuf kennee | እንጨትን ሰጠን፣ |
| Sala nuuf kennee | ከብትን ሰጠን፣ |
| Ilmoo nuuf kennee | ልጅን ሰጠን፣ |
| Eaga nuuf kennee | መሬትን ሰጠን፣ |
| Irra bobbaanee, iruma qalea | ተሰማርተንበት፣ |
| | እንመላለስበታለን፡፡ |
| Waaqn odaa uume nuuf haa dhagahu | ኦዳን የፈጠረው ይስማን፣ |
| Waaqn malkaa uume nuuf haa dhagahu | ወንዝን የፈጠረው ይስማን፣ |
| Waaqn tulluu uume nuuf haa dhagahu | ተራራን የፈጠረው ይስማን፣ |
| Liibanin nagaa haa godhu | ሊበንን ሰላም ያድርግልን፣ |

| | |
|---|---|
| Hangafaan nu haabulchu | በሽማግሌዎች ያስተዳድረን፣ |
| Giddichaan nu haa bulchu | በጊዳ ያስተዳድረን፣ |
| Liibanin nu haa bulchu | በሊበን ያስተዳድረን፣ |
| Yoo hin roobne haa roobsu | ካልዘነበ ያዝንብልን፣ |
| Kalaan nu soor'atu nu irraa haa qabu | ከጠላት ይሰውረን፣ |
| Seerri oromn, uumaan oromoo haa guddatu | የኦሮሞ ህግ ፤የኦሮሞ ዘር ይደግ፣ |
| Mangistii teessoorra nuf haa bulchu | መንግስትን በዙፋኑ ያቆይልን፣ |
| Waaqayyo jechunn dhugaa dubbachundha | ፈጣሪ ማለት እውነት መናገር ነው፤ |
| Seexana jechuun dhara dubbachuu dha | ሰይጣን ማለት ውሸት መናገር ነው፤ |
| Oromoon Waaqa kadhata | ኦሮሞ እግዚአብሔርን ይለምናል፣ |
| Allaatin illee gad jettee | ወፎች እንኳን ጎንበስ ብለው |
| Bishaan dhugdeeti | ውሃ ጠጥተው፣ |
| Oljettee waaqa kadhatti | ቀና ብለው ያመሰግኑሃል፣ |
| Afaan waaqa kadhatan | ሁሉም በራሱ ቋንቋ ፈጣሪን ይለምናል፣ |
| Bakkeen kan bakka kadhata haa taatu | ይህ ቦታ የጸሎት ይሁን፡፡ |

# አባሪ ሁለት

## ሁሉቱንም እምነቶች ለሚከተሉ ሰዎች የቀረበ ቃለ መጠይቅ

1. በመጀመርያ ስምዎን፣ የሚኖሩበትን አካባቢ፣ እድሜዎትን እና ሥራዎን ቢገልጹልኝ?
2. የኦሮሞ ህዝብ ዝቋላ አካባቢ መስፈር የጀመረው መቼ ነው ተብሎ ይታመናል?
3. የዋቄፈናው ስርዓት የተጀመረው መቼ? እና እንዴት ነው?
4. በመጋቢት ወር ዝቋላ ተራራ ላይ የሚደረገው የሙዳ ስርዓት በምን ቀን ይፈጸም ነበር?
5. ወደ ተራራው ሲወጣ ምን ምን ተይዞ ይወጣል?
6. ከበራው ላይ የሚገኙት እነማን ናቸው? አባ ገዳዎች? የሃይማኖት አባቶች (ቃሉ)? ሽማግሌዎች? ወንዶች? ሴቶች? ወጣቶች? ህጻናት?
7. ፕሮግራሙን የሚመራው ማን ነው? የተሳታፊዎች አስተዋጽኦስ ምንድን ነው?
8. ተራራው አናት ላይ ለመውጣት ስንት ሰዓት በእግር መውጣት ያስፈልጋል?
9. የሙዳ ስርአቱ ስንት ሰዓት ይጀመራል? ክዋኔው የሚጀመረው ምን በማድረግ ነው?
10. ቀጣይ ፕሮግራሞችስ ምን ምን ናቸው? ከበራው እስኪጠናቀቅ ያሉትን ክንውኖች በቅደም ተከተል ቢገልጹልኝ?
11. በዝቋላ ተራራ ላይ በሚፈጸመው የሙዳ ስርአት በጊዜ ሂደት (መንግስታት ሲቀያየሩ) ተለውጠዋል፡፡ በፊት እንዲህ አልነበረም የሚሏቸው ክንውኖች ምን ምን ናቸው?
12. እነዚህ ለውጦች ለምን መጡ ብለው ያምናሉ?
13. ዝቋላ ተራራ ላይ የነበረው ሲዳ ከተሰበረ በኋላ በከበራ ስርአቱ ላይ የተከሰተው ለውጥ ምንድን ነው? (በአክባሪው ብዛት? በከበራው አይነት?)
14. ክርስትና ወደ ዝቋላ አካባቢ በምን መልኩ ገባ?
15. የኦሮሞ ህዝብ በተለይም ደግሞ የዝቋላ አካባቢ ማህበረሰብ ክርስትናን እንዴት ተቀበለ?

አመሰግናለሁ!

## አባሪ ሦስት

### በከበራው ላይ ከዋኝ ለነበሩ ሰዎች የቀረበ ቃለ መጠይቅ

1. በመጀመርያ ስምዎን፣ የሚኖሩበትን አካባቢ፣ እድሜዎትን እና ሥራዎን ቢገልጹልኝ?
2. በኦሮሞ ባህል መሰረት ምርቃት ምንድን ነው? በምርቃት ምን ይገኛል ብላችሁ ታምናላችሁ?
3. ስንት አይነት ምረቃቶች አሉ? ምን አይነት ስልጣን ያለውና ከየትኛው ጎሳ የመጣ ሰው ቀድሞ እንዲመርቅ እድል ይሰጠዋል?
4. መራቂዎቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ምን አይነት ቦታ ይሰጣቸዋል? ግጥም አውራጆችስ?
5. በምረቃት ጊዜ የታዳሚዎች ሚና ምንድን ነው?
6. ከቀደሙ አባቶች የሚወልዷቸው ልጆች በሙሉ ወንዶች ከነበሩ ከየትኞቹ ሴቶች እየተጋቡ ነው ልጆችን ይወልዱ የነበረው?
7. ኹለቱንም እምነቶች በአንድላይ እንድትከተሉ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ማለት ይቻላል? ከሆኑ እንዴት?
8. የዋቄፈናው ሥርአት ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ንግስ ይሄዳሉ? ከሄዱ ለየትኛው የበለጠ ትኩረት ይሰጣሉ?
9. የከበራ ስርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ታዳሚያኑ ወደ መጡበት የሚመለሱት በምን መልኩ ነው?
10. በዋቄፈታ እምነት መሰረት ጾም አለ? ካለ መቼ እና እንዴት ይጾማል?

አመሰግናለሁ!

## አባሪ አራት

### ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም አባቶች የቀረበ ቃል መጠይቅ

1. በመጀመርያ ስምዎን፣ በዚህ ገዳም ውስጥ ያለዎትን ሀላፊነትና በዝቋላ ገዳም ውስጥ በአገልግሎት የቆዩበትን ጊዜ ቢገልጹልኝ?
2. የዝቋላ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም በዚህ ቦታ የተመሰረተበትን ጊዜና የአመሰራረት ሂደቱ ምን ይመስል እንደነበር ቢገልጹልኝ?
3. ገዳሙን በገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም መሰየም ለምን አስፈለገ?
4. አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ያረፉበትና ጽላቱ በስማቸው የተቀረጸበት ጊዜ ምን ያህል ይቀራረባል?
5. የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዓመታዊ በዓል ቀናት ለምን ጥቅምት 5 እና መጋቢት 5 ሆኑ?
6. ክርስትና ወደዚህ አካባቢ የገባው መቼ እና እንዴት ነው ተብሎ ይታመናል?
7. ገዳማዊ ህይወት በዚህ ስፍራ መቼ እንደተጀመረ እና መስራቹ ማን እንደነበሩ ቢገልጹልኝ?
8. ከአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክብረ በዓል ጎን ለጎን የሚከበር የዋቄፈና ክብረ በዓል አለ፡፡ ይህ ክብረ በዓል በዚህ ቦታ እንዴት ሊጀመር ቻለ?
9. ከኹለቱ እምነቶች መካከል ቀድሞ በዝቋላ ሀይቅ ዙርያ ማምለክ የጀመረው የትኛው ነው? አሁን ያለበት ኹኔታስ ምን ይመስላል?
10. የዝቋላ ሀይቅ እንዴት ወደ ጸበልነት ሊቀየር ቻለ? በጸበሉ (ዝቋላ ሀይቅ) ማጥመቅ የተጀመረውስ መቼ ነው?
11. ሀይቁን የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች የኛ ነው፣ ሀይቁ የተፈጠረውም የነቢ መቃብር ላይ ነው፣ይላሉ ስለዚህ ሀሳብ ምን የሚሉት ነገር አለ?
12. የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ "አቦ" የሚለውን ስም ያወጣንላቸው እኛ ነን፣ በአከባቢውም ቀድመን እንኖር ነበር ይላሉ፣ ስሊህስ እርስዎ ምን ይላሉ?
13. በዚህ ስፍራ በሚካሄዱት የክርስትና እና የዋቄፈታ እምነት ሥርአቶች መካከል ያለው ልዩነትና ተመሳስሎ ምንድን ነው?

እመሰግናለሁ!

# አባሪ አምስት

## የመረጃ ሰጭዎች መረጃ

| ስም | እድሜ | ጾታ | መረጃውን የሰጡበት ቀን | ሙያ | መረጃውን የሰጡበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| አባ ገዳ ለገሰ ነገዎ | 63 | ወንድ | መጋቢት8 እና 15/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አባ ሙዳ ደበበ ግርማ | 47 | ወንድ | መጋቢት 15/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ ደምሴ ዳዲ | 63 | ወንድ | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ መልካ ፎሌ | 65 | ወንድ | መጋቢት 5/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ አያና መስቀሉ | 66 | ወንድ | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ ፍቃዱ አረርቲ | 70 | ወንድ | መጋቢት8 እና 15/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ ዮዮ ቡታ | 72 | ወንድ | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ ዶሪ ሲዳ ቡታ | 67 | ወንድ | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አዴ ሚልኮ ደቻሳ | 45 | ሴት | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ ኤቢሳ ባቲ | 39 | ወንድ | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አቦ ሶምቤ ቃቻ | 55 | ወንድ | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አባ ተስፋ ማርያም ደበሳይ | 47 | ወንድ | መጋቢት 5/2005 ዓ.ም | ግብርና | ዝቋላ ገዳም |
| አባ ወልደ ሩፋኤል አበበ | 47 | ወንድ | መጋቢት 5/2005 ዓ.ም | ግብርና | ዝቋላ ገዳም |
| አቦ ጫላ ሶሪ | 55 | ወንድ | መጋቢት 15/2005 ዓ.ም | የቢሸፍቱ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የሥራ ሂደት ባለቤት | ዱከም |
| አዴ በሻዱ ሮበሌ | 50 | ሴት | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |
| አዴ ብሪቱ ገመዳ | 39 | ሴት | መጋቢት 8/2005 ዓ.ም | ግብርና | አዱላላ |

97